# የገቢዉ ዘርፍ የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ



አዲስ አበባ

ነሃሴ 2015 ዓ.ም.

# ማውጫ

1 መግቢያ ... 1

2 የ2015 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ... 2

2.1 ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት ... 2
2.2 ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የቀረጥና ታክስ አስተዳደር ስርዓትን ማጎልበት ... 11
2.3 የታክስና የጉምሩክ ህግ ተገዥነት ማረጋገጥ ... 14
2.4 ዘላቂ የመንግስት ገቢ ዕድገት ማረጋገጥ ... 18

3 የገቢው ዘርፍ የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ እንድምታዎችና የሚጠበቁ ውጤቶች ... 20

3.1 የተጠቃለለ የተቋም ርዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዕሴቶች፣ ግቦች እና ዋና ዋና ተግባራት ... 20
3.2 የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ታሳቢዎች ... 21
3.3 ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች ... 23
3.4 ታክስ በፈቃደኝነት የመክፈል ባህል ማሳደግ ... 23
3.5 ዲጂታል የቀረጥና ታክስ ገቢ አስተዳደር ስርዓትን መገንባት ... 24
3.6 የቀረጥና ታክስ አስተዳደር ፍትሀዊነትን ማረጋገጥ ... 24
3.7 የውስጥ እና የውጭ ስትራቴጂክ አጋርነትን ማጠናከር ... 24
3.8 የዳበረ የስራ ባህል ማምጣት ... 24

4 የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ግቦች፣ ዒላማዎችና የድርጊት መርሃ-ግብር ... 25

4.1 ግብ-1. ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን ማጎልበት ... 25
4.2 ግብ-2 ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስ አስተዳደር ስርዓትን ማጎልበት ... 31
4.3 ግብ-3 የታክስና የጉምሩክ ህግ ተገዥነት ማረጋገጥ ... 33
4.4 ግብ-4 ዘላቂ የመንግስት ገቢ ዕድገትን ማረጋገጥ ... 35
4.5 ለ2016 በጀት ዓመት የተቀመጡ ግቦች፣ ዒላማዎች እና የድርጊት መርሃ-ግብር ... 38

5 ስጋቶችና የመፍትሄ ሀሳቦች ... 46

6 የዓመቱን ዕቅድ ለማሳካት የሚተገበሩ የዕቅድ ማስፈጸሚያዎች ... 48

6.1 ዕቅዱን ለማሳካት በልዩ ትኩረት የሚሰሩ ስራዎች ... 48

7 የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ... 51

7.1 የሪፖርት አቀራረብና የግንኙነት አግባብ ... 51
7.2 የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ... 52
7.3 የግብረ- መልስ ሥርዓት ... 53

## ሰንጠረዦች

ሰንጠረዥ 1፡ የተቋማዊ የማስፈጸም አቅም ግብ የተጠቃለለ አፈጻጸም ........ 9
ሰንጠረዥ 2፡ ቀልጣፋና ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ሥርዓት ማጎልበት ግብ የተጠቃለለ አፈጻጸም ........ 13
ሰንጠረዥ 3 የግብር ከፋዮች የህግ ተገዥነት ማሻሻል ግብ የተጠቃለለ አፈጻጸም ........ 18
ሰንጠረዥ 4 የዘላቂ የመንግስት ገቢ ዕድገት ማረጋገጥ ግብ የተጠቃለለ አፈጻጸም ........ 19
ሰንጠረዥ 5 የተጠቃለለ ርዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዕሴቶች፣ ዓላማዎችና ዋና ዋና ተግባራት ........ 20
ሰንጠረዥ 6 የሃገር ውስጥ ታክስ የ2016 በጀት ዓመት የገቢ ዕቅድ ........ 35
ሰንጠረዥ 7 የወጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ የ2016 በጀት ዓመት የገቢ ዕቅድ ........ 36
ሰንጠረዥ 8 የሃገር ውስጥና የወጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ የ2016 በጀት ዓመት የገቢ ዕቅድ ........ 36
ሰንጠረዥ 9 ስጋቶችና የመፍትሄ ሀሳቦች ........ 46

# 1 መግቢያ

መንግስት የነደፋቸውን የኢኮኖሚና ማህበራዊ የልማት ዕቅዶች ፋይናንስ ለማድረግ የሚያስችል የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ከ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ እና የመካከለኛው ዘመን (2016-2018) የልማትና ኢንቨስትመንት ዕቅድ ጋር ተጣጥሞ እንዲሁም የአንድ እቅድ የአንድ ሪፖርት መርህን ተከትሎ የተዘጋጀ ሲሆን ዕቅዱ በ2022 ዘመናዊ የታክስ እና የጉምሩክ አስተዳደር ስርዓት ተገንብቶ ሀገራዊ ወጪ በቀረጥና ታክስ ገቢ ተሸፍና የማየት ርዕይ ላይ ለመድረስ ጉልህ ሚና የሚኖረው ይሆናል፡፡ ወደ ርዕዩ የሚያደርሰው ተልዕኮም ብቃት ያለው የሰው ኃይል በማፍራት፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም፣ ፍትሀዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው የታክስና ጉምሩክ አገልግሎት በመስጠት፣ ቀረጥና ታክስን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን በማዳበር፣ የጉምሩክና ታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድን በመከላከልና በመቆጣጠር ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ መሰብሰብ ነው፡፡ ይህንኑ ተልዕኮ ለማሳካት አገልጋይነት፣ መሰጠት፣ ሙያዊ ብቃት፣ ታማኝነት እና በቡድን የመስራት እሴቶችን መላበስ ይገባል፡፡

መ/ቤቱ በዋናነት ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን የሚያጎለብቱ፣ ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ሥርዓትን የሚያሻሽሉ፣ የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነት የሚያመጡ እና ዘላቂ የመንግስት ገቢ ዕድገት አስተማማኝ እና ቀጣይነቱን የሚያረጋግጡ አራት ስትራቴጂክ ግቦችንና በስራቸው ዋና ዋና የሆኑ ዝርዝር ተግባራትን በማስቀመጥ እንዲሁም ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾችን በመቅረጽ የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ስኬት ጉልህ ድርሻ የሚኖራቸው የቀረጥና ታክስ በፈቃደኝነት መክፈል ባህል ማሳደግ፣ ዲጂታል የገቢ አስተዳደር ስርዓትን መገንባት፣ የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ፣ የውስጥ እና የውጭ ስትራቴጂክ አጋርነትን ማጠናከር እና የዳበረ የስራ ባህል መፍጠር የሚሉትን ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎችን ተከትሎ የሚሰራ ይሆናል፡፡ የተቋሙ ዋና ተልዕኮ የመንግስትን የልማት ወጪ ለመሸፈን የሚያስችል ገቢ መሰብሰብ እንደመሆኑ መጠን በ2016 በጀት ዓመት ከታክስና ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች ከሀገር ውስጥ ታክስ ብር 319.33 ቢሊዮን እና ከውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ ብር 210.00 ቢሊዮን በድምሩ ብር 529.33 ቢሊዮን ለመሰብሰብ የሚያስችሉ እና በጥረት ተደራሽ የሚፈጸሙ ዝርዝር የገቢ ፊስካል ስራዎችን ለመፈጸም አቅዷል፡፡

በመጨረሻም ዓመታዊ ዕቅዱ በክፍል አንድ መግቢያ፣ በክፍል ሁለት የ2015 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ፣ በክፍል ሶስት የገቢው ዘርፍ የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ እንድምታዎች እና የሚጠበቁ ውጤቶች፣ በክፍል አራት የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ግቦች፣ ዒላማዎችና የድርጊት መርሃ ግብር ፣ በክፍል አምስት ስጋቶችና የመፍትሄ ሃሳቦች፣ በክፍል ስድስት የዓመቱን ዕቅድ ለማሳካት የሚተገበሩ የዕቅድ ማስፈጸሚያዎች እና በመጨረሻው ክፍል የክትትልና ግምገማ አሰራርና ስርዓትን በማካተት የዕቅድ ሰነዱ በሰባት ክፍሎች ተደራጅቶ ተዘጋጅቷል፡፡

# 2 የ2015 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ

## 2.1 ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት

### 2.1.1 የዕቅድ ዝግጅት፣ የክትትልና ግምገማና የስታቲስቲክስ መረጃ አስተዳደር አሰራር ማሻሻል

የገቢው ዘርፍ ከዕቅድ ዝግጅት አኳያ የአስር ዓመቱን የልማት ዕቅድ መነሻ በማድረግ ከ2013 በጀት ዓመት ጀምሮ ሲሳራ የቆየ ቢሆንም በተለይ ደግሞ በ2015 በጀት ዓመት በልዩ ሁኔታ የአንድ ዕቅድ አንድ ሪፖርት መርህን በመከተል ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በዕቅድ ዝግጅቱም የጉምሩክ ኮሚሽንን ጨምሮ ከዋናው መ/ቤት እስከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ድረስ ያሉትን አመራሮችንና መላውን ሰራተኛ በማወያየት፣ በዕቅድ ዝግጅቱ ዙሪያ የጋራ መግባባት በመፍጠር እና ዕቅዱን እስከ ፈጻሚ ድረስ ማውረድ ተችሏል፡፡ በዋናው መ/ቤት የስራ ዘርፎችና ዳይሬክቶሬቶች እንዲሁም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ የአፈጻጸም ግብረ መልስ በመስጠት መስተካከል በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ የጋራ ውይይት እየተደረገ ተግዳሮቶች ከስር ከስር እንዲፈቱ የማድረግ ስራዎች ተፈጽመዋል፡፡ ከዕቅድ ዝግጅቱ ጎን ለጎን ለክትትልና ግምገማ የሚያግዙ የታክስ እና ቀረጥ መረጃዎችን በማጠናቀር የበጀት ዓመቱ የገቢ ዕቅድ ግብ በተሻለ ሁኔታ እንዲፈጸም ከፍተኛ የሆነ የክትትል፣ የድጋፋዊ አካላዊ ምልከታ፣ የግምገማ እና የግብረ-መልስ አሰጣጥ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

የገቢው ዘርፍ ለ2015 በጀት ዓመት ያስቀመጣቸውን ግቦች ለማሳካት የሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብቶች ወሳኝ ሚና ያላቸው በመሆኑ የሰው ኃይሉ በክህሎቱ፣ በአመለካከቱ፣ በስነ-ምግባሩ፣ በአገልጋይነቱ የተመሰከረለት እንዲሆን እና በዚህም የዳበረ የስራ ባህልን የተላበሰ ምስጉን ሰራተኛ ለመፍጠር ጥረት ተደርጓል፡፡ ከግብዓት ዝግጅት አኳያም በየዓመቱ ስራ ሊያሰራ የሚችል የደመወዝና ስራ ማስኬጃ በጀት እና የፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ በጀት ከመንግስት ግምጃ ቤት እየተደገፈ በጀትን ከውጤት ጋር በማስተሳሰር የፕሮግራም በጀት አተገባበር ስርዓትን በመዘርጋት የመንግስትን ሃበት በቁጠባ ለመጠቀም ጥረት ተደርጓል፡፡

በ2015 በጀት ዓመት ባለድርሻ አካላትንና ግብር ከፋዩን ከማዘጋጀት አኳያ የግብር ከፋዩንና ባለድርሻ አካላትን በዕቅድ እና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር እንዲሁም በህግ ተገዥነት ደረጃቸው የተሻለ አስተዋጽዖ የነበራቸውን 724(400 በአገር አቀፍ ደረጃ እና 324 በቅርንጫፎች ደረጃ) ግብር ከፋዮች እና አስመጪዎች የዕውቅናና የማበረታቻ ሽልማት እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡ ተቋሙ በዚሁ በጀት ዓመት ውስጣዊ አቅሙን በማጠናከርና ለአሰራር ማነቆ የሆኑ ችግሮችን በመለየት የማሻሻያ ስራዎችን በመስራት፣ ከአጋር አካላት ጋር ማለትም ከንግዱ ማህበረሰብ፣ ከተቆጣጣሪ እና ተባባሪ አካላት ጋር የተጠናከረ የስራ ግንኙነት በመፍጠር በቴክኖሎጂ የታገዘ ዘመናዊ የቀረጥና ታክስ አስተዳደር ስርዓት ለመገንባት ጥረት ተደርጓል፡፡

እንደ አጠቃላይ በ2015 በጀት ዓመት ከዕቅድ ዝግጅት አኳያ ከላይ የተጠቀሱት ዋና ዋና ተግባራት የተፈጸሙ እና የተሳኩ ቢሆንም በሌላ በኩል ለግብር ከፋዩ ቀላልና ቀልጣፋ የሆነ

አገልግሎት ከመስጠት፣ የግብር ከፋዩን ማህበረሰብ የእርካታ ደረጃ ከፍ ከማድረግ፣ የቀረጥና ታክስ ስርዓቱን ከማዘመን፣ ተደራሽ የሆነ አገልግሎት ከመስጠት፣ ለአገልግሎት አሰጣጥ ማነቆ የሆኑ የህግ ማዕቀፎችን እየፈተሹ ከማስተካከል እንዲሁም የተገልጋዩን ወጪ የሚቀንሱ አሰራሮችን ከመዘርጋት አኳያ የነበሩትን ክፍተቶች የበለጠ በማስተካከል በ2016 በጀት ዓመት እነዚህ ክፍተቶች ታርመው የንግዱ ማህበረሰብ የቀረጥና ታክስ ግዴታውን በፈቃደኝነት እንዲወጣ የሚያስችሉ መደላድሎች እንዲፈጠሩ በትጋትና በልዩ ትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡

### 2.1.2 የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርንና ውጤታማነት ማሻሻል

የጾታ ስብጥርን እና የክልሎችን ስብጥር ማዕከል ባደረገ አግባብ ትኩረት ተደርጎ የሰው ኃይል ሙሌት ላይ በመሰራቱ የሰው ኃይል ቁጥሩ በ2015 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ 13,861 (ወንድ 7,456 እና ሴት 6,405) ማድረስ ተችሏል፡፡ የሰው ኃይሉ በስትራቴጂክ እቅዱ መሰረት ባይሟላም ያለውን የሰው ኃይል ውጤታማ በሆነ አግባብ ስምሪት እየሰጡ በመመራቱ በ2015 በጀት ዓመት የተፈጸመው የገቢ አፈጻጸም ከባለፉት ዓመታት ሁሉ በእጅጉ የተሻለ ሆኖ በመገኘቱ በሰው ኃይል ስምሪት ላይ የተሰራው ስራ ውጤታማ መሆኑን አመላካችና የሰራተኛው ምርታማነትም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣ መሆኑን አመላካች ነው፡፡

በተቋሙ ውስጥ ያለውን የሰው ኃይል ተነሳሽነቱን በማሳደግ እና ማቆየት እንዲቻል አቅም በፈቀደ መጠን የሰራተኛ ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ማሻሻል እና ምቹ የሆነ የስራ ከባቢ መፍጠር አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡ በዚህም ለሰራተኛው የሰርቪስ አገልግሎት እንዲቀርብ መደረጉ፣ የተሻሻለ የካፌቴሪያ አገልግሎት እንዲያገኝ መደረጉ፣ የሰራተኞች የደመወዝ ዕርከን ጭማሪ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 182/2015 ተዘጋጅቶና ጸድቆ በ2015 በጀት ዓመት የአራት ዕርከን የደመወዝ ጭማሪ መፈቀዱ፣ በየጊዜው የደረጃ ዕድገት መሰጠቱ፣ የሰራተኛውን ችግር ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የውስጥና የውጭ ዝውውሮች ተግባራዊ መደረጋቸው እንዲሁም አነስተኛ ደመወዝ ለሚከፈላቸው ሰራተኞች በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ድጋፎችን የማድረግ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

ይሁን እንጂ የተቋሙ የደመወዝ እስኬል ከስድስት ዓመት በፊት በ2009 ዓ.ም ከተደረገለት መጠነኛ ማሻሻያ በስተቀር ቀጣይነት ባለው መልኩ ክለሳ ያልተደረገበት በመሆኑ በአሁኑ ወቅት ካለው የኑሮ ውድነት አንጻር ሰራተኛው ላይ ከፍተኛ ጫና ከመፍጠሩም በላይ ተቋሙን በሰው ኃይል ገበያው ውስጥ ተወዳዳሪ ከማድረግ አንጻር በእጅጉ አናሳ መሆኑን መረዳት የሚቻል ሲሆን በዚህም በ2015 በጀት ዓመት 468 በርካታ ልምድ ያላቸው አመራሮችና ባለሙያዎች በራሳቸው ፈቃድ ተቋሙን ሊለቁ በመቻላቸው የተቋሙ የፍልሰት መጣኔ 3.7 በመቶ ላይ በመድረሱ በተቋሙ የ2016 በጀት ዓመት የገቢ አሰባሰብ ላይ የራሱን የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል መሆኑን ከወዲሁ ተገንዝቦ መፍትሄ ሊፈለግለት ይገባል፡፡

የሰው ኃይል ምርታማነትን ለማሳደግ የታክስ እና ጉምሩክ ስልጠና ማዕከል በማደራጀት በርካታ የአቅም ግንባታ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በዚህም ከሚሰሩ ስራዎች ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ያላቸው በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ በ2015 በጀት ዓመት ለ6,974 ሰራተኞች የተለያዩ ስልጠናዎችን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል ከረዥም ጊዜ ስልጠና አኳያም ቢሆን በመጀመሪያና በሁለተኛ ድግሪ፣ በዶክትሬት ድግሪ እንዲሁም የውጪ ትምህርት ዕድል

እንዲያገኙ እየተደረጉ ያሉ አመራሮችና ባለሙያዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ የተቋሙን ስራ በዕውቀት ላይ ተመስርቶ እንዲመራ ከማድረግ አኳያ ለሰራተኛ አቅም ግንባታ በየአመቱ እየተሰጠ ያለው ትኩረት ከፍተኛ መሆኑን አመላካች ነው።

በመሆኑም ተቋሙ ለ2016 በጀት ዓመት ያስቀመጣቸውን ግቦች ማሳካት እንዲችል የሰው ኃይሉ ያለውን ቁልፍ ሚና ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሰራተኛውን ሊያቆዩና ተነሳሽነቱን ሊያሳድጉ የሚችሉ የሰው ኃይል ገበያ መሰረት በማድረግ የደመወዝና ጥቅማጥቅም ማሻሻያ በማድረግ፣ መብቱ የተከበረ፣ ነጻ ሆኖ የሚያገለግል፣ ጥቅሞቹ የተከበሩለት፣ አምራች የሆነ እና በስነ-ምግባር የታነጸ ሰራተኛ ለመፍጠር እንዲሁም የሰራተኛውን ዕርካታ በማረጋገጥ ምርታማነቱን የሚያሳድጉ ስትራቴጂክ ስራዎችን በከፍተኛ ትኩረት የዕቅዱ አካል አድርጎ መስራት ይጠበቅበታል።

### 2.1.3 የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል

ተቋሙ ለ2015 በጀት ዓመት የተመደበለትን የተስተካከለ የደመወዝና ስራ ማስኬጃ በጀት ብር 8.1 ቢሊዮን ውስጥ ብር 7.9 ቢሊዮን ወይም የዕቅዱን 97 በመቶ በአግባቡ ስራ ላይ በማዋል ለበጀት ዓመቱ የተያዙ ግቦችን ውጤታማ በሆኑ አፈጻጸሞች አጠናቋል። በዚህም ለስራ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን በወቅቱ ግዥ በመፈጸም ለተጠቃሚዎች በማሰራጨት የገቢ አሰባሰቡን በአግባቡ የመደገፍ ስራዎች ተከናውነዋል። ከኦዲት ግኝት ማስተካከያ ጋር በተያያዘ ከዚህ በፊት በተቋሙ ላይ በፌደራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት በተደጋጋሚ የአድቨርስ ግኝት ሲቀርብበት የነበረ ቢሆንም በየጊዜው በተሰሩ የክትትልና የግኝት ማስተካከያ ስራዎች የተነሳ የፌዴራል ዋና ኦዲተር ኦዲት አስተያየት ከተወሰኑ የአሰራር ጥሰቶች በስተቀር የወጪ፣ የበጀት እና የሂሳብ ምዝገባ ሥርዓቱ የመንግስት ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ተከትሎ የተሰራ መሆኑን አስተያየት እንዲሰጥ ለማድረግ ተችሏል። በ2016 በጀት ዓመትም ይህንኑ በማስቀጠል እና የተሻለ ውጤት በማምጣት ከግኝት የጸዳ ተቋም ለመፍጠር በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

በበጀት ዓመቱ በመንግስት ልዩ ትኩረት የተሰጠው የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ እና ክፍያን በልዩ ትኩረት በስራ ላይ እንዲውል የሚደረግ ይሆናል። መንግስት ያለበትን የሃብት ውስንነት ግምት ውስጥ በማስገባት ከዚህ በፊት ወጥቶ የነበረውን የወጪ ቅነሳ መመሪያ በ2016 በጀት ዓመትም በስራ ላይ በማዋል የመንግስትን ወጪ ለመቀነስ በልዩ ትኩረት የሚሰራ ይሆናል። ለሰራተኞች ሰርቪስ ኪራይ በየዓመቱ በአማካይ ከ257 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የሚደረግ መሆኑ፣ የጉምሩክ ዋና መ/ቤትን ጨምሮ በርካታ የሀገር ውስጥ ታክስ እና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የራሳቸው ቢሮ የሌላቸው በመሆኑ በየዓመቱ ለቢሮና መጋዘን ኪራይ በአማካይ ከ536 ሚሊዮን ብር በላይ ለኪራይ የሚከፈል በመሆኑና ይህም ከፍተኛ ሀብት በመሆኑ ተቋሙ የነባሮቹንም ሆነ አዳዲስ የቢሮ ግንባታ ስራዎችን በማፋጠን እንዲሁም ለሰራተኛ ሰርቪስ አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር የሚገኙበትን ሁኔታ በማመቻቸት በ2016 በጀት ዓመት የመንግስት ወጪን ለመቀነስ በልዩ ትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

ከፕሮጀክቶች አፈጻጸም ጋር በተያያዘ አፈጻጸሙን የበለጠ ለማሻሻል የሚረዱ ማለትም ቅድመ ሁኔታዎች ሳይሟሉ የካፒታል በጀት አለማስያዝ፣ በአንዳንድ አካባቢዎች በሚስተዋለው

የጸጥታ ችግር ምክንያት የፕሮጀክቶች ማስፈጸሚ ጊዜ እንዳይራዘም ጥረት በማድረግ እና አማራጭ መፍትሄዎችን በማስቀመጥ መንቀሳቀስ፣ በግዥዎች ላይ የሚስተዋሉ አላስፈላጊ መጓተቶችን በመቀነስ፣ ስራ ተቋራጮች ከዋጋ ንረት ጋር በተያያዘ በመንግስት የተፈቀደውን መመሪያ በመተግበር እንዲሁም ወቅታዊ የግብዓት አቅርቦት የሚያገኙበትን ሁኔታ በማመቻቸት፣ የስራ ተቋራጮች የአቅም ውስንነቶችን በሶስትዮሽ ውይይትና በግምገማ ክስር ክስር እያስተካከሉ በመምራት እንዲሁም የተቋሙ የማስፈጸም አቅም ውስንነቶችን በመቅረፍ በ2015 በጀት ዓመት የታየው የፕሮጀክቶች የአፈጻጸም መሻሻልና ውጤታማነት በ2016 በጀት ዓመትም ይህንኑ ልምድ እና ተመክሮ አጠናክሮ በማስቀጠል የፕሮጀክት አስተዳደር ስራዎች በልዩ ሁኔታ እንዲመሩ እና ውጤቶች እነዲመዘገቡ በልዩ ትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡

### 2.1.4 የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል

በተቋሙ የወረቀት አልባ አገልግሎት መተግበርና ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ዕውን ከማድረግ አንጻር የመረጃ ቴክኖሎጂ ስትራቴጂ ጸድቆ መተግበሩ፣ የጉምሩክ ስራ አመራር አስተዳደር ስርዓት (eCMS) ተግባራዊ መደረጉ፣ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትን አገልግሎት አሰጣጥ በአንድ ማዕከል ለማድረግ ያስቻለ የኤሌክትሮኒክስ አንድ መስኮት አገልግሎት (eSW) በስራ ላይ መዋሉ፣ የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ለመወሰን የሚያስችል የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ስርዓት (ECVS_G2) በስራ ላይ መዋሉ፣ በትራንዚት ላይ ያሉ ዕቃዎችን ደህንነት ለማረጋገጥ የዕቃ መፈተሻ ስካኒንግ ማሽን (Cargo Scanning Machine) ስራ ላይ መዋሉ በጥንካሬ ሊነሱ የሚችሉ የቴክኖሎጂ ስራዎች አፈጻጸም ናቸው፡፡

በተጨማሪነት የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ስርዓቱን ለማቀላጠፍ በስራ ላይ ውሎ የነበረውን የተቀናጀ የመንግስት ታክስ አስተዳደር ሥርዓት (SIGTAS) የኢ-ማሳወቅና የኢ-ክፍያ ስርዓቶችን በማቀናጀትና በማስፋት አዳዲስ የወጡ እንደ ኤክሳይዝ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ አዋጅና ደንቦችን መሰረት በማድረግ የቴክኖሎጂ ማሻሻያ መደረጉ፣ በስራ ላይ ለታክስ አወሳሰን ግብዓት የሚያገለግሉ የሶስተኛ ወገን መረጃ መሰብሰቢያ(TASS) ማሻሻያ መደረጉ፣ በስራ ላይ የነበረውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ስርዓት ከቀድሞው በተሻለ መልኩ መረጃ እነዲቀበል የማሻሻያ ሰራዎች መሰራታቸው፣ የግብር ከፋዮች አጠቃላይ መረጃ በማሰባሰብ ማለትም የጉምሩክና የሶስተኛ ወገን መረጃ በያዘ መልኩ ከአንድ ቦታ ለስራ ክፍሎች ተደራሽ የሚያደርግ የዳታ ዌርሃውስ ለምቶ በስራ ላይ እንዲውል መደረጉ፣ የክልል ገቢ ትልልፍ ስርዓት ላይ መሰረታዊ ማሻሻያ መደረጉ፣ ግብር ከፋዮች በወረቀት አልባ ከየትኛውም ቦታ ሆነው ግብርና ታክሳቸውን የሚያሳውቁበት (E-Filing) ከበፊቱ በተሻለ የሲስተም ማሻሻያ ተደርጎለት የክልል ግብር ከፋዮችን ጨምሮ በርካታ ግብር ከፋዮችን ማስተናገድ እንዲችል የማሻሻያ ስራ መሰራቱ፣ የካሽ አልባ የግብር ክፍያ ሥርዓት (E-Payment) የነበሩበትን የቴክኖሎጂ ውስንነቶች በመቅረፍ ሁሉንም ባንኮች ተሳታፊ ያደረገ ከደራሽ በተጨማሪ በቴሌብር አማራጭ እንዲከፍሉ የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋቱ የአገልግሎት አሰጣጡን፣ የገቢ አሰባሰቡን እና የህግ ተገዥነት ስራዎችን በማጠናከር የቀረጥና ታክስ ከፋዩን ጊዜና ወጪ በመቆጠብ ረገድ ውጤታማ ሊባሉ የሚችሉ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

ደጋፊ ስራዎችንም በቴክኖሎጂ እንዲመሩ ከማድረግ አንጻርም የጉምሩክ የሪከርድና ማህደር ዶክመንት ማኔጅመንት ሲስተም ተግባራዊ መደረጉ፣ የሰው ሀይል አስተዳደር ስራን ለማቀላጠፍ የሚያግዘው የኤሌክትሮኒክ የሰው ሀብት መረጃ አስተዳደር (HRM System) ተግባራዊ መደረጉ እና የቢሮ ደህንነት መቆጣጠሪያ ሲሲቲቪ ካሜራ መዘርጋቱ ተጠቃሽ ስራዎች ናቸው፡፡

የገቢውን ዘርፍ ወረቀት አልባ ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎች በአውሮፓ ህብረት፣ በእንግሊዝ መንግስት፣ በዓለም ገንዘብ ድርጅት እና በዓለም ባንክ ድጋፍ በተቀጠሩና በውስጥ ባለሙያዎች የተከናወኑ ቢሆንም ለሲግታስ ስርዓት ከአልሚው ድርጅት ጋር የነበረው የቴክኒክ ድጋፍ ውል በመቋረጡ እና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች በመልቀቃቸው በሲስተሙ ላይ መሰረታዊ ማሻሻያ ሳይደረግ መቆየቱ፣ በቂ የሆነ የመረጃ ማከማቻ አለመኖሩ እና የኔትወርክ እና የኤሌክትሪክ መቆራረጥ በዳታ ማዕከል ውስጥ ባሉ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ላይ ጉዳት ማድረሱና ለአገልግሎት አሰጣጡና ገቢ አሰባሰቡ ተግዳሮት መሆኑ ዋና ዋና ተጠቃሽ ተግዳሮቶች ሲሆኑ በ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ውጤታማነትን በማረጋገጥ የታክስና የጉምሩክ አሰራሮችን በተሟላ ሁኔታ በመደገፍ ዲጅታል የሆነ የገቢ አስተዳደር ለመፍጠር የሚያስችሉ ስትራቴጂክ ስራዎች መስራት ይጠበቃል፡፡

### 2.1.5 የአጋርነት እና የህዝብ ግንኙነት አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል

የሀገር ውስጥ አጋር አካላት አጋርነትና ትብብር ከማሻሻል አኳያ የታክስና የጉምሩክ አስተዳደር ኃላፊነቱን በሚገባ እንዲወጣ ከማድረግ አንጻር በ2015 በጀት ዓመት ቀጥተኛ ተጽዕኖ ያላቸው ዋና ዋና የአገር ውስጥ ባለድርሻ አካላትን በመለየትና ስትራቴጂክ አጋርነታቸውን በማሻሻል በታክስና በጉምሩክ አገልግሎት አሰጣጥ፣ በህግ ተገዥነት ስራዎች፣ በቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት፣ በመረጃ ልውውጥ እና በአቅም ግንባታ ስራዎችን በቅንጅት በመስራት ውጤት ለማስመዝገብ ተችሏል፡፡

ይሁንና ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር በቅንጅት ለመስራት የተደረገው እንቅስቃሴ ከውጤት አኳያ ሲመዘን የተቀላጠፈ የታክስና የጉምሩክ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲኖር ከማድረግ እና የንግድ ማጭበርበርን ከመከላከል አንጻር በሚፈለገው ደረጃ አለመሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ከመንግስት ተቋማት ጋር ያሉት ቅንጅታዊ አሰራሮች አስገዳጅነት የሌላቸው እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ የማያስችሉ በመሆናቸው ንግድን ከማሳለጥ እና ኮንትሮባንድን ከመከላከል አንጻር ውስንነቶች ተንጸባርቀዋል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ተግዳሮቶች በ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ የአገር ውስጥ አጋር አካላት ትብብር በአገልግሎት አሰጣጥና በህግ ተገዥነት ስራዎች ላይ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት በሚያስችሉ ስትራቴጂክ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

በሌላ በኩል በ2015 በጀት ዓመት የውጭ አገራትና ድርጅቶች አጋርነትና ትብብርን ከማሻሻል አኳያ የታክስና የጉምሩክ አስተዳደርን ከማዘመን አንጻር ከውጭ አገር ተቋማት ጋር ማለትም የዓለም ጉምሩኮች ድርጅት (WCO)፣ የዓለም ገንዘብ ድርጅት (IMF) ፣ የዓለም ባንክ ፣ የእንግሊዝ የገቢና ቀረጥ ተቋም (HMRC) የአፍሪካ ነጻ ንግድ ቀጠና ጽ/ቤት (ACFTA)፣

የምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ ኮሜሳ (COMESA)፣ የምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ ቀጠና ጽ/ቤት ፣ የኮሪያ አለም አቀፍ ተራዶ ድርጅት (KOICA) ፣ የጃፓን ተራዶ ድርጅት (JICA) ፣ የቻይና የታክስ እና ጉምሩክ ተቋም (BRITACOM) ፣ ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የታክስና ጉምሩክ አስተዳደሮች እና ሌሎች ተቋማት ጋር በቅንጅት በመስራት በአቅም ግንባታ፣ በመረጃ ፣ በተሞክሮ ልውውጥ እና የቴክኖሎጂ ድጋፍ ለማግኘት ጥረት ተደርጎ አዎንታዊ ውጤቶች ተገኝተዋል።

ይሁንና የአጋርነትና ትብብር ስራውን በአሰራር የተደገፈ በማድረግ ለታክስና ለጉምሩክ አስተዳደሩ ዘላቂ ጥቅም በሚያስገኝ ደረጃ ትኩረት ሰጥቶ ከመስራት አንጻር የተስተዋሉትን ክፍተቶች በ2016 በጀት ዓመት እንዲታረሙ የሚሰራ ይሆናል። በመሆኑም በ2016 በጀት ዓመት ከውጭ አገራትና ድርጅቶች ጋር በስትራቴጂ የሚመራ አሰራር በመቅረጽና የታክስና የጉምሩክ አስተዳደሩን ከማዘመን አንጻር ዘላቂ ጥቅሞች ሊያስገኙ የሚችሉ ስትራቴጂክ ጉዳዮችን የዕቅድ አካል አድርጎ መስራትን ይጠይቃል።

### 2.1.6 ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልሎች የሚደረገውን ድጋፍና ክትትል ማሻሻል

በ2015 በጀት ዓመት ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በዕቅድ ዝግጅት፣ በግምገማ፣ በሪፖርት፣ በግብረ መልስ አሰጣጥ፣ የተናበበ እና የተቀናጀ ስራ በመስራት የጋራ ተቋማዊ ውጤት እንዲመጣ ጥረት ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪ በአቅም ግንባታ ስራዎች እና በቴክኖሎጂ ትስስር፣ በጥናትና ልማት በጋራ እየተሰራ ይገኛል። ክልሎችንና ከተማ አስተዳደሮችን ከመደገፍና ከማብቃት አንጻር የታክስ ስርዓቱ እንዲጣጣም፣ በስልጠና አቅማቸው እንዲጎለብት፣ የቴክኖሎጂ ድጋፎች እና የተለያዩ የግብዓት ድጋፍ ስራዎች ተሰርተዋል። የታክስ ስርዓቱን ከማጣጣም አንጻር አዲስ የወጡ የኤክሳይስ ታክስ፣ ተ.እ.ታ ማሻሻያዎች እንዲሁም መመሪያዎችን በተጣጣመ መልኩ እንዲተገበሩ የድጋፍ ስራዎች ተሰርተዋል። ከዚህ በተጨማሪም በዘርፉ ያሉ ችግሮችን እና ዕቅዶችን ለማጣጣም እንዲያስችል የፌደራል፣ ክልል እና ከተማ መስተዳደር ገቢ ተቋማት የጋራ መድረክ ተፈጥሮ በየጊዜው የግንኙነት መድረኮች በመካሄድ ላይ ይገኛሉ።

ከአቅም ግንባታ አኳያ በ2015 በጀት ዓመት ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለተውጣጡ ለ1560 የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በ18 የስልጠና ርዕስ ጉዳዮች ዙሪያ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪ ከክልል የገቢ ሰብሳቢና የፋይናንስ ዘርፍ ተቋማት ጋር ቋሚ የግንኙነት ስርዓት (የምክክር መድረኮችን) በማካሄድ የታክስ ፖሊሲና አስተዳደር አፈጻጸሞችን በጋራ በመገምገም የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ችግሮችን በጋራ የመፍታት ስራ ተሰርቷል። በዚህም በክልሎች፣ ከተማ መስተዳድሮች እና በፌደራል ደረጃ ከምን ጊዜውም በተሻለ በገቢ ትልልፍና ድጋፍ ላይ ተዓማኒነት ያለው ግንኙነት እንዲፈጠር አስተዋጽዎ አድርጓል።

ይሁን እንጂ የታክስ ህጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎች በሚጠበቀው ደረጃ ከማጣጣም አንጻር ቀሪ ስራዎች መኖራቸው፣ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚደረገው የቴክኖሎጂ ድጋፍ ውስንነት መኖሩ በእጥረት የሚታይ በመሆኑ በ2016 በጀተ ዓመት የጋራ የምክክር መድረኮችን

በማጠናከር የሚጠበቁ ድጋፎችን በማድረግ የክልሎችን አቅም መገንባትና የታክስ ስርዓቱን በሚፈለገው ደረጃ የተጣጣመ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### 2.1.7 የስነ-ምግባርና ፀረ ሙስና የክትትል ስራዎችን ማሻሻል

በ2015 በጀት ዓመት ተቋማዊ የስጋት ስራ አመራር አፈጻጸም ለማሻሻል እንዲያስችል ስጋቶችን የመለየት፣ የመተንተን እና የስጋት ስትራቴጂ የመቅረጽ፣ ለብልሹ አሰራር ተጋላጭ የሆኑ አሰራሮችን የመፈተሽና የማስተካከል እና የስነ-ምግባር ችግር በሚታይባቸው አመራሮችና ፈጻሚዎች ላይ ባለው ህጋዊ አሰራር መሠረት እርምጃ በመውሰድ ተቋማዊ ጤንነትን ለማረጋገጥ ጥረት ተደርጓል፡፡ ይሁንና የተቀረጸውን ስትራቴጂ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ከማድረግና የስነ- ምግባር ችግሮችን በሚፈለገው ደረጃ እንዲስተካከሉ ከማድረግ አንጻር ውስንነቶች ተስተውለዋል፡፡ በመሆኑም በ2016 በጀት ዓመት የታክስና የጉምሩክ አስተዳደር የስራ ባህርይ እና ሁኔታ ያለውን የስጋት ተጋላጭነት ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ ሁኔታ የተቋማዊ የስጋት ስራ አመራር ስትራቴጂ ከወቅታዊ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ በማድረግ ተቋማዊ ስጋትን በመቀነስ የገቢ ሴክተሩን ጤንነት ለመጠበቅ የሚያስችል ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡

### 2.1.8 የሴቶችና ማህበራዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ማሻሻል

በበጀት ዓመቱ ለ2,310 ሴት አመራሮችና ሰራተኞች በአስተሳሰብ ለውጥ፣ በራስ መተማመን፣ በመግባባት ችሎታ እና በደንበኞች አያያዝ ዙሪያ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በተቋሙ ለሚገኙ 214 ሴት አመራሮች (Ethical Leadership, Decision Making and Team Work) ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በስልጠና ማዕከሉ በሚሰጡ ስልጠናዎች ሴቶችና ወጣቶች የተሳትፎ ድርሻን ቢያንስ 40 ከመቶ ለማድረስ ታቅዶ፣ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ስልጠና ከተሠጣቸው 6,974 አመራሮችና ባለሙያዎች መካከል 2,779 ወይም 40 በመቶ ሴት አመራሮችና ባለሙያዎች ሲሆኑ ከአመራሮች አኳያ ስልጠና ከተካፈሉ 1,566 አመራሮች መካከል 493ቱ ሰልጣኞች ሴት አመራሮች ናቸው፡፡ የአፈጻጸም ድርሻቸው ደግሞ 32 በመቶ ይዟል፡፡

በዘርፉ የሴቶች ተሳትፎን ከማረጋገጥ አንጻር በቅጥር የሴቶችና ወንዶችን ቁጥር በማመጣጠን የሴት ሰራተኞችን ቁጥር ለማሳደግ በተሰራው ስራ የሴት ሰራተኞች ድርሻን 46 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡ በ2015 በጀት ዓመት የሴት ሰራተኞችን በልዩ ሁኔታ በማብቃት እና ሴት ተኮር የሆኑ ተጨማሪ ስራዎችን በመስራት በስትራቴጂክ ዕቅዱ የሴት ሰራተኞች አመራር ድርሻን 50 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሎ የነበረ ቢሆንም አፈጻጸሙ ሲገመገም በ2015 በጀት ዓመት ማድረስ የተቻለው 30 በመቶ ነው፡፡ በዘርፉ 22 የህጻናት ማቆያ ማዕከላትን በማመቻቸት ለ398 ህጻናት አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

አካል ጉዳተኞችን ከመደገፍ አንጻር ተቋሙ አዳዲስ በሚያስገነባቸውና በሚከራያቸው ህንጻዎች ላይ አካል ጉዳተኞችን ግምት ውስጥ ያስገቡ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በልዩ ሁኔታ የተለያዩ ፋሲሊቲዎችም እንዲሟሉላቸው ተደርጓል፡፡ አካል ጉዳተኛ ሰራተኞቻችን ለአካል ጉዳተኞች አመቺ በሆኑ የቢሮ ወለሎች ላይ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ አካል ጉዳተኛ ደንበኞች ቅድሚያ አግኝተው እንዲስተናገዱ እንዲሁም መስተንግዶውን ምድር ቤት ላይ በተመቻቸ ልዩ ቢሮ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ የወጣቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ከማሳደግ አኳያ በስፖርታዊ

ውድድር፣ ወጣት ሰራተኞች ለታክስ ያላቸው ሚና፣ በህይወት ተመክሮ፣ በስሜት ብልህነት ዙሪያ የማነቃቂያ ስልጠናዎች በልዩ ሁኔታ እንዲያገኙ ተደርጓል። በዚህም በ2016 በጀት ዓመት ለየት ያለ ስትራቴጂ በመንደፍና የሴት ሰራተኞችን በማብቃት በሸፋኑ ላይ የተመዘገበውን ውጤት እንደ ምርጥ ተመክሮ በመውሰድ ሴቶችን ወደ አመራር እርከን ከማምጣት አኳያ ከፍተኛ ስራዎችን መስራት ይገባዋል። እንዲሁም በህጻናት፣ በወጣቶች እና በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚሰራው ስራ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።

### 2.1.9 የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎችን ማሻሻል

የገቢው ዘርፍ ከማህበራዊ አገልግሎት አንጻር በኤች.አይ. ቪ. ለተጎዱ ሰራተኞችና ቤተሰቦቻቸው ድጋፍ በማድረግ፣ በአረንጓዴ አሻራ እና ገበታ ለሀገር መርሃ ግብር ላይ ጠንካራ ተሳትፎ በማድረግ እንዲሁም በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋ ለተጎዱ የህብረሰተብ ክፍሎች ፈጥኖ በመድረስ ተቋሙ ማህበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ የሚገኝ ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት ከ1.1 ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት በገንዘብና በዓይነት ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲደርስ አድርጓል። በዚህም ከተለያዩ የመንግስት የስራ ኃላፊዎች፣ ከህብረተሰብ ተወካዮች እንዲሁም ከተለያዩ ተቋማት አበረታች ዕውቅናዎችን ያገኘ ሲሆን ይህም ተቋሙ ገቢ ከመሰብሰብ ኃላፊነቱ በተጨማሪ ይሄንን በጎ ተግባር ማከናወን በመቻሉ ለሌሎች ተቋማት ተምሳሌት መሆን ከመቻሉም በላይ የተቋሙ ገጽታ እንዲሻሻል አድርጓል።

ከዚህ በተጨማሪ እንደ ተቋም ቦታ በመውሰድ የአረንጓዴ አሻራ ተግባራትን በማካሄድ/ችግኞችን የመትከል እና የመንከባከብ ስራዎች፣ የአቅመ ደካማ ማህበረሰቦች መኖሪያ ቤቶችን የማደስ፣ የአቅመ ደካማ ቤተሰብ ተማሪዎችን የመደገፍ፣ በየጊዜው ደም በመለገስ እና ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናትን በቋሚነት የማስተማር ስራዎች በ2015 በጀት ዓመት በስፋት ተከናውነዋል። በ2016 በጀት ዓመትም የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎችን ውጤታማ ከማድረግ አንጻር የበለጠ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል።

ሰንጠረዥ 1፡ የተቋማዊ የማስፈጸም አቅም ግብ የተጠቃለለ አፈጻጸም

| ዋና ዋና ተግባራት / ቁልፍ አመላካቾች / | ክብደት(ግብ) | ዒላማ | ክንውን | ክንውን በክብደት | አፈጻጸም (%) |
|---|---|---|---|---|---|
| **የዕቅድ ዝግጅት፣ የክትትልና ግምገማ እና የስታቲስቲክስ መረጃ አስተዳደር አሰራር ማሻሻል (ክብደት=1)** | 1 | | | 1 | 100 |
| ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ ዕቅድና ሪፖርት ሰነድ ማዘጋጀት | 0.4 | 4 | 4 | 0.4 | 100 |
| የክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት | 0.3 | 1 | 1 | 0.3 | 100 |
| የዘርፉን መረጃ አያያዝ በቴክኖሎጂ በመደገፍ ማደራጀት | 0.3 | 25 | 25 | 0.3 | 100 |
| **የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል (ክብደት=2)** | **2** | | | **2.2** | **110** |
| ግልጽነት የሰፈነበት የሰው ኃይል ስምሪት ማካሄድ | 0.5 | 100 | 88.5 | 0.4 | 88 |
| ለአመራር እና ለሰራተኞች የሚሰጡ ሥልጠናዎችን ማሳደግ | 0.5 | 4800 | 6974 | 0.7 | 145 |
| የውስጥ የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት | 0.5 | 1 | 1 | 0.5 | 100 |
| የሰራተኛ እርካታን በማሳደግ ፍልሰትን መቀነስ | 0.5 | 4 | 3.7 | 0.5 | 108 |
| **የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል (ክብደት=3)** | **3** | | | **3.1** | **103** |
| የተመደበ በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል (ድርሻ) | 0.6 | 100 | 97 | 0.6 | 97 |
| ነቀፌታ ያለበትን የኦዲት ግኝት መቀነስ | 0.6 | 93.5 | 71.5 | 0.5 | 76 |

| ዋና ዋና ተግባራት / ቁልፍ አመላካቾች / | ክብደት(ግብ) | ዒላማ | ክንውን | ክንውን በክብደት | አፈጻጸም (%) |
|---|---|---|---|---|---|
| የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ክፍያን ድርሻ ማሳደግ | 0.6 | 77.5 | 72 | 0.6 | 93 |
| የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዢን ድርሻ ማሳደግ | 0.6 | 55 | 48 | 0.5 | 87 |
| የንብረት አያያዝ እና የጥገና ወጪዎችን መቀነስ (ሚሊዮን ብር) | 0.6 | 122.8 | 191.5 | 0.9 | 156 |
| **የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል (ክብደት=2)** | **2** | | | **1.9** | **95** |
| መረጃ ቋት ማደራጀት | 0.4 | 50 | 50 | 0.4 | 100 |
| በተቋሙ ወረቀት አልባ አሰራርን መተግበር | 0.3 | 100 | 75 | 0.2 | 75 |
| በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶችን አቶሜት ማድረግ | 0.3 | 33 | 27.5 | 0.3 | 83 |
| የተገልጋዮችን እርካታ ደረጃ ማሳደግ | 1 | 87.5 | 85.8 | 1 | 98 |
| **የአጋርነት እና የህዝብ ግንኙነት አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል (ክብደት=1)** | 1 | | | **1** | **100** |
| መረጃዎችን በተለያዩ የተግባቦት ዘዴዎች ተደራሽ ማድረግ | 1 | 100 | 100 | 1 | 100 |
| **ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልሎች የሚደረገውን ድጋፍና ክትትል ማሻሻል (ክብደት=2)** | **2** | | | **2.2** | **110** |
| ለክልሎች ወቅታዊ የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት | 0.5 | 1,200 | 1,560 | 0.7 | 130 |
| በየሩብ ዓመት ከክልሎች ጋር የዘርፍ አፈጻጸም በጋራ መገምገም | 0.5 | 4 | 4 | 0.5 | 100 |
| የተጠሪ ተቋማት ዕቅድን ከዘርፍ ዕቅድ ጋር ማናበብና ማጣጣም | 0.25 | 2 | 2 | 0.3 | 100 |
| የክልሎችን ዕቅድ ከዘርፍ ዕቅድ ጋር ማናበብና ማጣጣም | 0.5 | 1 | 1 | 0.5 | 100 |
| የየሩብ ዓመት የተጠሪ ተቋማት ሪፖርት መገምገም | 0.25 | 4 | 4 | 0.3 | 100 |
| **የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና የክትትል ሥራዎችን ማሻሻል (ክብደት=1)** | **1** | | | **0.8** | **80** |
| ለብልሹ አሰራር የተጋለጡ አሰራሮች በጥናት በመለየት የማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብ | 0.25 | 130 | 133 | 0.3 | 102 |
| በብልሹ አሰራር ዙርያ ጥቆማ ከተደረገባቸው ውስጥ ማስተካከያ የተደረገባቸው | 0.25 | 100 | 96 | 0.3 | 104 |
| የሀብት ምዝገባ ያካሄዱ አመራሮች እና ባለሞያዎች ድርሻ ማሳደግ (በዲጂታል) | 0.5 | 100 | 53 | 0.3 | 53 |
| **የሴቶችና ማህበራዊ ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነትን ማሻሻል (ክብደት=1)** | **1** | | | **1.1** | **110** |
| ለአካል ጉዳተኛ ሰራተኞችና ተገልጋዮች ምቹ የስራ ሁኔታና ቦታ መፍጠር | 0.25 | 85 | 85 | 0.3 | 100 |
| ሥልጠና ያገኙ ሴት ሰራተኞች ድርሻ ማሳደግ | 0.25 | 1,969 | 2,524 | 0.3 | 128 |
| ወደ አመራር የመጡ ሴት ሰራተኞች ብዛት ማሳደግ (በመቶኛ) | 0.25 | 40 | 30 | 0.2 | 75 |
| የህጻናት ማቆያ አገልግሎት ተጠቃሚ ሴት ሰራተኞች ብዛት ማሳደግ | 0.25 | 340 | 398 | 0.3 | 117 |
| **የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎችን ማሻሻል (ክብደት=2)** | **1.85** | | | **2** | **108** |
| የአረንጓዴ አሻራ ተግባራትን ማካሄድ/ችግኞችን መትከል | 0.5 | 120,000 | 180,000 | 0.8 | 150 |
| የአቅመ ደካማ ማህበረሰቦች የመኖሪያ ቤቶች መገንባት በቁጥር | 0.15 | 35 | 35 | 0.2 | 100 |
| የአቅመ ደካማ ማህበረሰቦች የመኖሪያ ቤቶች መገንባት በሚሊዮን ብር | 0.15 | 30 | 30 | 0.2 | 100 |
| የአቅመ ደካማ ቤተሰብ ተማሪዎች ድጋፍ በቁጥር | 0.15 | 1,000 | 1,000 | 0.2 | 100 |
| የአቅመ ደካማ ቤተሰብ ተማሪዎች ድጋፍ በሚሊዮን ብር | 0.15 | 3 | 3 | 0.2 | 100 |
| ለተለያዩ ማህበራዊ ቀውሶች የተደረገ ድጋፍ በሚሊዮን ብር | 0.3 | 1,268 | 1,175 | 0.3 | 93 |
| የተደረገ ደም ልገሳ (ድርሻ ከሰራተኛ ብዛት) | 0.3 | 11.5 | 2.2 | 0.1 | 19 |
| ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናትን መደገፍ | 0.3 | 226 | 218 | 0.3 | 96 |

## 2.2 ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የቀረጥና ታክስ አስተዳደር ስርዓትን ማጎልበት

በዚህ ስትራቴጂክ ግብ ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ስርዓት ከመገንባት አንጻር የህግ ማዕቀፎች እና የአሠራር ስርዓቶችን ማሻሻልን፣ አዳዲስ አሰራሮችን መቅረጽን እና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በማስደገፍ የላቀ አገልግሎት መስጠትን፣ ህግን ማስከበር እና የገቢ አሰባሰቡን ውጤታማ ማድረግን የሚያካትት ሲሆን የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ከዚህ በታች ባለው አግባብ ቀርቧል፡፡

### 2.2.1 የገቢ አሰባሰብ አሰራር ልህቀትን ለማምጣት የህግ ማዕቀፎችን እና አሰራሮችን ማሻሻል

የታክስና ጉምሩክ የህግና የአሰራር ማሻሻያ ስራዎች በማከናወን የአገልግሎት አሰጣጡ፣ የቁጥጥር ስርዓቱ እና የገቢ አሰባሰብ ስራውን ውጤታማነት ለማረጋገጥ አስችሏል፡፡ በዚሁ መሠረት በ2015 በጀት ዓመት አፈጻጸም ወቅት ከተከናወኑ ዋና ዋና የህግና አሰራር ስርዓት ማሻሻያዎች መካከል የፌዴራል ገቢ ግብር ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 520/2014፣ አምራች ድርጅቶች የናሙና አላላክ መመሪያ ቁጥር 72/2014፣ ታክስ ከፋዩ ያቀረበውን የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ እንዲሻሻል ስለሚፈቀድበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 144/2011 የማሻሻያ ሀሳብ ቀርቦ መመሪያው 181/2015 ሆነው የጸደቁና በስራ ላይ እንዲውሉ የተደረጉ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በገቢው ዘርፍ ከ28 በላይ የሚሆኑ የተለያዩ የአሰራር ስርዓት ማሻሻያዎች ተተግብረዋል፡፡

አሰራር ከመቅረጽ አንጻር ያለጥሬ ገንዘብ ክፍያ ዕቃዎች በባንክ ዋስትና የሚለቀቁበት አሰራር፣ ዕቃ ሳይደርስ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈጻጸም አሰራር፣ የአስገዳጅ የታሪፍ መረጃ አሰጣጥ ስርዓት፣ በጥቅልና በክፍልፋይ የሚመጡ ጭነቶችን የማስተናገጃ ስርዓት፣ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ማስፈጸሚያ ኮድ አሰራር፣ የጉምሩክ የዋጋ መረጃ ዳታ ቤዝ አጠቃቀም ስርዓት፣ በዕቃ አወጣጥ ስርዓት ላይ ዕሴት የማይጨምሩ ሰነዶች የሚቀነስ አሰራር እና የመሳሰሉትን ተግባራዊ በማድረግ ለንግድ ስራ አመቺነት ከማረጋገጥ እና ሎጂስቲክስን በማፍጠን እንደ ሀገር ውጤታማ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

ይሁንና የሚሻሻሉና በአዲስ መልክ የሚቀረጹ ህጎችና አሰራሮች በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ያመጡትን ውጤት በተከታተይ በዳሰሳ ጥናት ከመለየት፣ የውስጥና የውጭ ፈጻሚ አካላትን አቅም ከመገንባት እና በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የተሻለ አፈጻጸም ካላቸው ሀገራት ተሞክሮ በመውሰድ ቀጣይነት ያለው ማሻሻያ ማድረግ ይጠበቃል፡፡ በቀጣይ የታክስና የጉምሩክ አስተዳደሩን ለማዘመን ተከታታይነት ያለው የህግና የአሰራር ስርዓት ማሻሻያ ማድረግ ቁልፍ ጉዳይ በመሆኑ በአገልግሎት አሰጣጡና በገቢ አሰባሰቡ ላይ በተጨባጭ የሚታዩ ችግሮችን በጥናት በመለየት ዓለም ዓቀፍ ልምድን በማካተት የላቀ አሰራር በመዘርጋት የአገልግሎት አሰጣጡን በማሻሻል የገቢ አሰባሰቡን እና የግብር ከፋዩን የህግ ተገዥነት ወጪ መቀነስ ያስፈልጋል፡፡

### 2.2.2 የታክስና ጉምሩክ መረጃ አስተዳደር ውጤታማነቱን ማረጋገጥ

የታክስና ጉምሩክ መረጃ ለአገልግሎት አሰጣጥ፣ ለገቢ አሰባሰብ፣ ለህግ ተገዥነት ሥራዎች፣ ለተለያዩ የጥናት ስራዎችና ለፖሊሲ አውጭዎች ቁልፍ ሚና እንዳለው ይታወቃል፡፡ በዚሁ መሰረት ተቋሙ በዘረጋቸው የተለያዩ የመረጃ ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም የሚገኙ መረጃዎችን ጥቅም ላይ በማዋል ውጤታማ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በ2015 በጀት ዓመት በርካታ የሽያጭና የግዥ መረጃዎች፣ የፊዚካል መረጃ እንዲሁም የግብር ከፋይ የታክስ ማስታወቂያ መረጃዎች ለታክስ ውሳኔ ጥቅም ላይ በማዋል የገቢ አሰባሰቡ ውጤታማ ማድረግ ተችሏል፡፡ የጉምሩክ እና ሀገር ውስጥ ታክስ ድህረ ገጾችን የማሻሻል ስራዎች በመስራት ግብር ከፋዩ ወቅታዊ መረጃን በድህረ ገጽ ማግኘት በመቻሉ ግንዛቤው እንዲጨምርና ለታክስ ህግ ተገዥነት መጨመር አስተዋጽዎ አበርክቷል፡፡ በጉምሩክ ዕቃ አወጣጥ ሥነ-ስርዓት የገቢ እና የወጪ ዕቃዎች መረጃ፣ በትራንዚት ጉምሩክ ስነ-ስርዓት ወደ ሀገር የሚገቡና የሚወጡ ጭነቶች መረጃ፣ እንዲሁም በመጋዘን ጉምሩክ ስነ-ስርዓት ተከማችቶ የሚገኙ ዕቃዎች መረጃ በአግባቡ በማደራጀት ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈጻጸም የተሳለጠ እንዲሆን ለማድረግ አስችሏል፡፡

በሌላ መልኩ የአስመጪዎችን፣ የላኪዎችን፣ የጉምሩክ አስተላላፊዎችንና የዕቃ መረጃዎችን ባላቸው የስጋት ደረጃ መሠረት ወቅታዊ በማድረግ አገልግሎት አሰጣጡ እና የድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ስራዎችን በስጋት ስራ አመራር መሰረት እንዲመሩ ከማድረግ አንጻር ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከሶስተኛ ወገንና ከሲስተም የሚገኙ መረጃዎችን በመተንተን የኮንትሮባንድና ንግድ ማጭበርበርን የመከላከል ስራዎች የተጠናከሩ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ ይሁንና በተለያየ አግባብ የሚደራጁ መረጃዎችን በሚፈለገው ደረጃ ከመተንተን አንጻር የሚታዩ ክፍተቶች፣ አስተማማኝ የመረጃ ምንጭ እጥረት፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር የገቢ እና ወጪ ጭነቶች ከማስታረቅ አንጻር እንዲሁም በጉምሩክና በሀገር ውስጥ ታክስ የመረጃ ልውውጥ ክፍተት መኖሩ ከሚስተዋሉ ውስንነቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በቀጣይ በመካከለኛ ዘመን የታክስና የጉምሩክ የመረጃ አስተዳደርና አጠቃቀም ዙሪያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን አስተማማኝ የመረጃ ምንጮችን በማስፋት፣ የትልልቅ መረጃዎች ትንተና አቅምን በማሳደግ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የመረጃ ልውውጥ በማጠናከር የአገልግሎት አሰጣጡን፣ የገቢ አሰባሰቡን እና የህግ ተገዥነት ስራውን ውጤታማ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### 2.2.3 የኤሌክትሮኒክ ታክስ(E-Tax) አጠቃቀምን ማሻሻል

በ2015 በጀት ዓመት በኢ-ፋይሊንግ እና ኢ-ፔይመንት ሲስተሞች ላይ በርካታ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡ ክልሎች የኢ-ፋይሊንግ ስርዓት እንዲጠቀሙ በማስቻል ረገድ የኢ-ፋይሊንግ ስርዓት በአዲስ አበባ እንዲተገበር የተደረገ ሲሆን ኦሮሚያ፣ ሀረሪ እና አማራ ክልሎች ወደ ስርዓቱ ለመግባት በዝግጅት ላይ ናቸው፡፡ በዚህም የኢ-ፋይሊንግ ሽፋን በየዓመቱ እየተሻሻለ መጥቶ በ2015 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ሽፋኑ ወደ 93 በመቶ አድጓል፡፡ በኢ-ፔይመንት የከፈሉት ደግሞ እንደዚሁ ከጠቅላላ ግብር ከፋይ ብዛት አኳያ ሲመዘን ወደ 57 በመቶ የደረሰ ሲሆን ኢ-ፋይል ከሚያደርጉት ግብር ከፋዮች አንጻር ሲመዘን ደግሞ ሽፋኑ ከ80 በመቶ በላይ

ደርሷል፡፡ በኢ-ፔይመንት እየተሳተፉ ያሉ ባንኮች ቁጥር እያደገ መጥቶ በተለይ በ2014 በጀት ዓመት ከነበረበት 8 ባንኮች በ2015 በጀት ዓመት ወደ 19 ባንኮች አድጓል፡፡

ክፍያን በቴሌብር መክፈል እንዲቻል የቴሌብር ኢንተግሬሽን ከኮር የሀገር ውስጥ ታክስ እና ጉምሩክ ሲስተሞች ጋር ተከናውኖ ክፍያዎች በቴሌብር በመከፈል ላይ ይገኛል፡፡ በሀገር ውስጥ ታክስ 2.34 ቢሊዮን ብር፣ በጉምሩክ ደግሞ 0.66 ቢሊዮን ብር በድምሩ በቴሌብር 3 ቢሊዮን ብር የተከፈለ ሲሆን በሲስተሙ 1,647 ግብር ከፋዮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡ ኦሮሚያ ክልል የቴሌ ብር ክፍያ እንዲጀምር ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡

### 2.2.4 የቀረጥና ታክስ ከፋዮች አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ማረጋገጥ

የአገልግሎት አሰጣጡን ከማሻሻል እና የተገልጋዮችን ዕርካታ ከማረጋገጥ አንጻር የታክስና የጉምሩክ አስተዳደር ሥርዓትን ለማዘመን እንዲያስችል ተቋሙ የተለያዩ የህግ ማዕቀፎችን በማሻሻልና ተግባራዊ በማድረግ፣ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን አልምቶ በስራ ላይ በመዋል፣ የተቋሙን ሰራተኞች አቅም በመገንባት ከተገልጋዮች ጋር ተከታታይነት ያለው ግንኙነት በመፍጠርና ችግሮችን በጋራ በመፍታት፣ የዜጎች ቻርተርን በማሻሻልና ተግባራዊ በማድረግ እና በስጋት ስራ አመራር መርህ ላይ የተመሰረተ አገልግሎት በመስጠትና ተግባራዊ በማድረግ በ2015 በጀት ዓመት አገልግሎት አሰጣጡ ጊዜና ወጪ ቆጣቢ እንዲሆን በማድረግ የደንበኞች ዕርካታ ለማሻሻል ጥረት የተደረገ ሲሆን ተቋሙ በየዓመቱ የደንበኞች ዕርካታ ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ከተገልጋዮች ዕርካታ ደረጃ በመነሳት ለአገልግሎት አሰጣጥ ማነቆ የሆኑ ጉዳዮችን በመለየት የማሻሻያ ዕርምጃዎችን በመውሰድ የዕርካታ ደረጃው በ2015 በጀት ዓመት በአማካይ ወደ 86 በመቶ ማሳደግ ተችሏል፡፡

ይሁንና በዳሰሳ ጥናቶችና በተለያዩ የውይይት መድረኮች የሚለዩ ችግሮችን በፍጥነት መፍትሄ ከመስጠት፣ ከማስፈጸም አቅም ውስንነት እንዲሁም ከተዘረጉ የቴክኖሎጂ መተግበሪያዎች መቆራረጥ ጋር በተያያዘ የአገልግሎት አሰጣጡ የደንበኞች ዕርካታን በተሟላ ሁኔታ የተረጋገጠ እንዳይሆን አድርጓል፡፡ በመሆኑም በ2016 በጀት ዓመት አሰራሮችን በማዘመን እና በቴክኖሎጂ በማስደገፍ፣ ተከታታይነት ያለው የህግና የመመሪያ ማሻሻያዎችን በማድረግ፣ ከደንበኞች ጋር ስትራቴጂክ የሆኑ የግንኙነት መድረኮችን በመፍጠር እና የአመራርና የፈጻሚውን አቅም በማጎልበት የደንበኞች ዕርካታ በተጨባጭ ወደ ሚረጋገጥበት ደረጃ ላይ ማድረስ ይገባል፡፡

ሰንጠረዥ 2፡ ቀልጣፋና ዘመናዊ የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ሥርዓት ማጎልበት ግብ የተጠቃለለ አፈጻጸም

| ዋና ዋና ተግባራት / ቁልፍ አመላካቾች / | ክብደት (ግብ) | ዒላማ | ክንውን | ክንውን (በክብደት | አፈጻጸም (%) |
|---|---|---|---|---|---|
| **የገቢ አሰባሰብ አሰራር ልህቀትን ለማምጣት የህግ ማዕቀፎችን እና አሰራሮችን ማሻሻል (ክብደት=6)** | **6** | | | **6.2** | **103** |
| ለፍትህ አካላት የሚቀርቡ የፍትሃብሔር ጉዳዮች በመዝገብ የመርታት አቅምን ማሳደግ | 2 | 92.7 | 87.3 | 1.9 | 94 |
| ለአቤቱታ የሚቀርቡ የፍትሃብሔር ጉዳዮች የመዝገብ ምጣኔ መቀነስ | 1 | 5 | 5.47 | 1.1 | 109 |
| በስጋት ከተለዩ ግብር ከፋዮች የግኝት ምጣኔን ማሳደግ | 1 | 87.5 | 92.3 | 1.1 | 105 |
| የአስመጪዎች ፕሮፋይል በየጊዜው በማሻሻል የስጋት ስራ አመራር ውጤታማነት (Targeting) ማሳደግ | 1 | 66 | 76.96 | 1.2 | 117 |

| ዋና ዋና ተግባራት / ቁልፍ አመላካቾች / | ክብደት (ግብ) | ዒላማ | ክንውን | ክንውን (በክብደት | አፈጻጸም (%) |
|---|---|---|---|---|---|
| የቢዝነስ አመቺነትን ለማሻሻል በዝቅተኛና መካከለኛ ስጋት ደረጃ የሚስተናገዱትን የስጋት ሰነዶች መጨመር | 1 | 86 | 77 | 1 | 90 |
| **የታክስ መረጃ አስተዳደር ውጤታማነቱን ማረጋገጥ (ክብደት = 5)** | **5** | | | **4.9** | **99** |
| የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ በመጠቀም Z-Report የሚልኩ ድርጅቶች ምጣኔን ማሳደግ | 1.5 | 95 | 94.8 | 1.5 | 100 |
| የግዥና ሽያጭ የታክስ መረጃ ጥራትና ብዛት ማሳደግ | 2 | 100 | 94.8 | 1.9 | 95 |
| የገበያ ዋጋ መረጃ ማሰባሰብና አጠቃቀምን ማሳደግ | 1 | 100 | 99.7 | 1 | 100 |
| የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተደራሽነትን ማስፋት | 0.5 | 79 | 84 | 0.5 | 106 |
| **የኤሌክትሮኒክ ታክስ (E-Tax) አጠቃቀምን ማሻሻል (ክብደት = 4)** | 4 | | | 4.3 | 106 |
| በኤሌክትሮኒክ ታክስ የሚያሳውቁ የግብር ከፋዮች ድርሻን ማሳደግ | 2 | 82 | 93 | 2.3 | 113 |
| በኤሌክትሮኒክ የታክስ ክፍያ ሥርዓት የታቀፉ ግብር ከፋዮች ድርሻን ማሳደግ | 1 | 60 | 53 | 0.9 | 88 |
| በኤሌክትሮኒክ የታክስ ክፍያ ሥርዓት የተሰበሰበ የታክስ መጠን ከአጠቃላይ ታክስ ያለውን ድርሻ ማሳደግ | 1 | 25 | 28.66 | 1.1 | 115 |
| **የግብር ከፋዮች አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ማረጋገጥ (ክብደት = 10)** | **10** | | | **10** | **100** |
| በስታንዳርዱ በተቀመጠው ጊዜ መሰረት የተሰጠ የምዝገባ አገልግሎት ማሳደግ | 1 | 100 | 96 | 1 | 96 |
| በስታንዳርዱ በተቀመጠው ጊዜ መሰረት የተሰጠ የተመላሽ አገልግሎት ማሳደግ | 1 | 95 | 98.74 | 1 | 104 |
| በስታንዳርዱ በተቀመጠው ጊዜ መሰረት የተሰጠ የአገልግሎት ኦዲት አገልግሎት ማሳደግ | 2 | 90 | 96 | 2.1 | 107 |
| በስታንዳርዱ በተቀመጠው ጊዜ መሰረት የተሰጠ የክሊራንስ አገልግሎት ማሳደግ | 2 | 85 | 80 | 1.9 | 94 |
| በስታንዳርዱ በተቀመጠው ጊዜ መሰረት የተሰጠ የታክስ ቅሬታ ውሳኔ አገልግሎት ማሳደግ | 2 | 95 | 98 | 2.1 | 103 |
| በስታንዳርድ በተቀመጠው ጊዜ መሠረት የተሰጠ የጉምሩክ አገልግሎት ማሳደግ | 2 | 100 | 96.31 | 1.9 | 96 |

## 2.3 የታክስና የጉምሩክ ህግ ተገዥነት ማረጋገጥ

የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነት ማህበረሰቡን በማስተማር ወደ ታክስ መረቡ የሚገቡትን ከመመዝገብ ጀምሮ በንግድ እንቅስቃሴ ሂደት ውስጥ ያሉ የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ስራዎች በህግ አግባብ መፈጸማቸውን የማረጋገጥና ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ የመውሰድ ተግባር ነው፡፡ የህግ ተገዥነት ሥራዎችን በአግባቡ መፈጸም በፈቃደኝነት ታክስና ቀረጥ የመክፈል ባህልን የማዳበር፣ የንግድ ፍትሀዊነትን የማስፈን እና የማህበረሰቡን ደህንነት የማስጠበቅ ዓላማዎችን ያሳካል፡፡

### 2.3.1 የታክስ ማስታወቅና ክፍያ አቀራረብን ማጠናከር

የንግዱን ማህበረሰብ በማስተማር፣ በመከታተልና የህግ ማስከበር ስራ በመስራት በ2015 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የግብር ከፋዮች ቁጥር 56,432 ደርሷል፡፡ የንግድ ትርፍ ግብር ከማስታወቅ አንጻር በበጀት ዓመቱ 31,002 ግብር ከፋዮች የንግድ ትርፍ ማሳወቅ ከሚጠበቅባቸው ውስጥ 26,453 ወይም 85.33 በመቶ አሳውቀዋል፡፡ በ2014 በጀት ዓመት

የማስታወቅ አፈጻጸም 79 በመቶ በመሆኑ በግብር ዘመኑ ማስታወቂያ አቀራረብ መሻሻል አሳይቷል፡፡

ከሚቀርቡ የንግድ ትርፍ ግብር ማሳወቂያዎች ውስጥ ከክፍያ ጋር የሚቀርበውን ድርሻ 65 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ ከክፍያ ጋር የቀረበው ግን 41 በመቶ በመሆኑ በበጀት ዓመቱ የቀረቡ የንግድ ትርፍ ግብር ማሳወቂያዎችን ከትክክለኛው የክፍያ መጠን ጋር ስለመቅረባቸው የማረጋገጥ ስራ በስፋት መሠራት እንዳለበት ማየት ተገቢ ነው፡፡ በክፍያ የሚቀርቡ የንግድ ትርፍ ግብር ማሳወቂያዎች ቁጥር እየጨመረ እንዲመጣ በደረሰኝ ቁጥጥር ስራዎች እና የታክስ ከፋዩን ሰነዶች በወቅቱ መቆጣጠር ላይ ትኩረት በማድረግ መስራት ያስፈልጋል፡፡

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢዎች የሂሳብ ጊዜያቸው በድግግሞሽ 118,331 የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያዎች በየወሩ እና በየ3 ወራት እንደሚቀርቡ ይጠበቃል፡፡ ከዚህ ውስጥ 96,296 (81.38 በመቶ) የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያዎች ቀርበዋል፡፡ በበጀት ዓመቱ በወቅቱ ይቀርባል ተብሎ በዕቅድ ከተያዘው 85 በመቶ አኳያ ሲታይ በወቅቱ የቀረበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ 81.38 በመቶ በመሆኑ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋዮች በሂሳብ ጊዜያቸው እንዲያሳውቁ የመቀስቀስ እና የማስገንዘብ ስፊ ስራ የሚጠይቅ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ በ2014 የማስታወቅ አፈጻጸሙ 80.61 በመቶ የነበረ በመሆኑ የ2015 በጀት ዓመት አፈጻጸም መጠነኛ ማሻሻያ አሳይቷል፡፡

በክፍያ የሚቀርቡ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያዎች 41 በመቶ ለማድረስ ከታቀደው አኳያ አፈጻጸሙ 39.3 በመቶ በመሆኑ አፈጻጸሙን ለማሻሻል ለቀጣይ ዓመት ትኩረት የሚፈልግ ስራ ይሆናል፡፡ በተለይ በየሩብ ዓመቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚያሳውቁ ታክስ ከፋዮች በቁጥር በርካታ በመሆናቸው እስከሚቀጥለው የማሳወቂያ ጊዜ የቀረቡ ማሳወቂያዎችን ታክስ ከፋዩ ሰነድ እንዲያቀርብ በማድረግ ማረጋገጥ እና ተመላሽ የሚያሳውቁትን በዘርፍ በመለየት ስቶክ በአካል ቼክ እስከማድረግ ያለውን ስራ መስራት ይጠይቃል፡፡

በበጀት ዓመቱ 7,143 የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያዎች እንደሚቀርቡ የሚጠበቅ ቢሆንም 6,854 (95.95 በመቶ) ማስታወቂያዎች ቀርበዋል፡፡ የታክስ ማስታወቅ አቀራረብ 95 በመቶ ለማድረስ ከታቀደው አንጻር በእቅዱ መሠረት መፈጸሙን ማየት ይቻላል፡፡ በ2014 በጀት ዓመት የማስታወቅ አፈጻጸሙ 92.11 በመቶ የነበረ በመሆኑ የ2015 በጀት ዓመት አፈጻጸም እየተሻሻለ የመጣ መሆኑን ያሳያል፡፡

የታክስ ስሌት ስራዎች አፈጻጸም በታክስ ከፋዮች ከቀረቡት የታክስ ማስታወቂያዎች ትክክለኛነት በማረጋገጥ፣ በኢፋይል አስታውቀው ያልከፈሉትን በመለየት፣ ዘግይተው የሚያስታውቁትን ወለድና መቀጫ በመጨመር ስሌት በመስራት እንዲሁም ክፍያ ሲኖር ማስታወቅ ሲገባቸው ያላስታወቁትን የታክስ ዓይነት (ዲቪደንድ፣ ቴክኒካል ሰርቪስ፣ ሪቨርስ ታክስ ወዘተ) ለይቶ የዴስክ ኦዲት ስራዎች በታክስ ስሌት መነሻ ውሳኔ የሚወጣባቸው ስራዎች ናቸው፡፡ በበጀት ዓመቱ በመደበኛው የስሌት ስራ ለማከናወን ብር 25,873,512,823.49 ታቅዶ ብር 31,099,457,390.43 ወይም የዕቅዱን 120.20 በመቶ ተፈጽሟል፡፡ ይህ አፈጻጸም በ2015 በጀት ዓመት የገቢ አሰባሰቡን በከፍተኛ ሁኔታ ያገዘ በመሆኑ በ2016 በጀት ዓመት ስራው በይበልጥ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

### 2.3.2 የታክስ ከፋዮች ትምህርት፣ የኢንተለጀንስ ክትትል እና የኦዲት ስራዎችን ማጠናከር

የታክስና ጉምሩክ ትምህርት ከማሳደግ አንጻር የተገልጋይ ተግባቦት መድረኮችን በመፍጠር፣ ከባለድርሻና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ጋር የተለያዩ መድረኮች በማዘጋጀት፣ የታክስና ጉምሩክ ህጎችን በሬድዮና በቴሌቪዥን በማስተላለፍ፣ የፓናል ውይይቶች በማድረግ፣ በማህበራዊ ሚዲያ፣ በኤሌክትሮንክስ ሚዲያ፣ በህትመት ሚዲያ በመጠቀም መረጃዎች ተደራሽ ተደርገዋል፡፡ ስለሆነም በ2015 በጀት ዓመት በታክስ ህጎች ላይ የሞጁላር ትምህርት እና ስልጠና ለ13,900 ግብር ከፋዮች ለመስጠት ታቅዶ ለ13,704 ወይም 97.59 በመቶ ትምህርት እንዲያገኙ ተደርገዋል፡፡ በትምህርት ቤቶችም ትውልድን በግብር ሥርዓት ላይ ከመቅረጽ አንጻር የታክስና ጉምሩክ ክበቦችን በማቋቋም እና በመደበኛ ትምህርት ግንዛቤ እንዲያገኙ የማድረግ ሥራም ተከናውኗል፡፡

የስጋት ስራ አመራር አፈጻጸምን ከማሻሻል አንጻር የአገልግሎት አሰጣጥና ቁጥጥር ሚዛናዊነት ለማስጠበቅ፣ የገቢ አሰባሰብ ውጤማነትን ለማሳደግ፣ ምቹ የንግድ እንቅስቃሴ ለመፍጠርና የህግ ተገዥነትን ለማሻሻል በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በዚሁ መሠረት የህግ ተገዥነት ማሻሻያ ስትራቴጂ በመቅረጽ ተግባራዊ መደረጉ፣ የስጋት መስፈርቶች ማሻሻልና ወቅታዊ የስጋት ፕሮፋይል ማዘጋጀት መቻሉ፣ በስጋት መርህ መሠረት ኦዲት የሚደረጉ ድርጅቶችን መርጦ ማሰራጨት፣ የታክስ ከፋዮች የህግ ተገዥነት ደረጃ በመለየት ታማኝ የሆኑትን ዕውቅናና ሽልማት እንዲሰጣቸው መደረጉና ዝቅተኛ የህግ ተገዥነት ደረጃ ያላቸውን ታክስ ከፋዮች ለህዝብ ይፋ በማድረግ የስጋት ስራ አመራር ውጤታማነትን ለማሻሻል የሚያስችሉ አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡

የስጋት ስራ አመራር ስራዎች ሀገሪቱ ልታጣ የነበረውን ገቢ ከማዳን በተጨማሪ የህግ ተገዥነትን በማሳደግ ረገድ የራሱን አስተዋጽዖ ያበረከተ ቢሆንም ዓለም ከደረሰበት ደረጃ ከማድረስ አንጻር ሥርዓቱ በአመዛኙ በቴክኖሎጂ ያልተደገፈ መሆኑ፣ የመረጃ አቅርቦት እና ጥራት ችግሮች ያሉበት መሆኑ፣ የግንዛቤ ክፍተት በመኖሩ ስራዎችን በስጋት ያለመምራት የሚስተዋል በመሆኑ በቀጣይ በትኩረት ሊሰራባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ሲሆኑ የስጋት ስራ አመራር ውጤታማነትን በጥናት የሚረጋገጥበት አግባብ ሊኖር ይገባል፡፡

የህግ ተገዥነትን ለማረጋገጥ ስጋትን መሠረት ያደረጉ የተለያዩ የኦዲት ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በዚሁ መሠረት የቁጥጥርና ድጋፍ ተደራሽነትን የማስተካከል እና የኦዲት ሽፋንን ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ እርምጃዎችን በመውሰድ የኦዲት ሽፋን በየዓመቱ መሻሻሎችን እያሳየ ይገኛል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ታክስ ግብር ይገባኝ እና ፍርድ ቤት የደረሱ ጉዳዮች ላይ ለመርታት እንዲያስችል የህግ ባለሙያዎችን አቅም በማሳደግ፣ በታክስና ጉምሩክ ዙሪያ የዳኞችን ግንዛቤ በማሳደግ እና ቅንጅታዊ ስራ በማጠናከር በ2015 የበጀት ዓመት የፍርድ ቤት የመርታት አቅም በመዝገብ በአማካይ 86 በመቶ እንዲደረስ ተደርጓል፡፡

በ2015 በጀት ዓመት ከላይ የተገለጹት ስኬቶች ቢመዘገቡም ካለው ታክስ ከፋይ አንጻር የትምህርት ሽፋን በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፣ ታክስ ከፋዩ ባለበት ቦታ ሆኖ ትምህርቱን የሚያገኝበት ኢ-ለርኒንግ አሰጣጥ ያለመኖር፣ የንግድ ትርፍ ግብር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ

ከክፍያ ጋር የማስታወቅ አፈጻጸም አነስተኛ መሆኑ፣ የኦዲት ሙያዊ ስነ-ምግባር ጉድለት መኖሩ፣ የሶስተኛ ወገን መረጃ ከማደራጀት፣ ለኦዲት ከመጠቀም እና የኦዲት ጥራት ከማረጋገጥ አንጻር ውስንነቶች ተስተውለዋል፡፡

ስለሆነም በ2016 በጀት ዓመት የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነትን ለማረጋገጥ በታክስ ህጉና አሰራሮች ላይ ቀጣይነት ያለው የታክስ ከፋዮች ትምህርት በተለያዩ የትምህርት መስጫ ዘዴዎች መስጠት፣ የታክስ ክሊኒክ (Tax-Clinic) ፕሮግራም መዘርጋት፣ በኤሌክትሮኒክስ የማስተማሪያ ዘዴ (E-Learning) የሚሰጡ ትምህርቶችን በግብር ከፋዮች ዓይነትና ደረጃ ለይቶ በመተግበር የታክስ ትምህርት ሽፋኑን ማሳደግ፣ የንግድ ትርፍ ግብር ከክፍያ ጋር ማስታወቅን የሚያሳድግ አሰራርና ቴክኖሎጂ ቀርጾ መተግበር፣ የህቡዕ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከፍተኛ በመሆኑ ወደ ታክስ መረቡ የሚገቡ ታክስ ከፋዮች ቁጥር ለማሳደግ የሚያስችሉ የተለያዩ ማሻሻያዎች ተግባራዊ ማድረግ እና የኦዲት ባለሙያዎች አቅምና ሙያዊ ስነ-ምግባር በማጎልበት እንዲሁም የሶስተኛ ወገን መረጃዎችን በመጠቀም የኦዲት ጥራትን ማረጋገጥ ይጠይቃል፡፡

### 2.3.3 የታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድ መከላከል አፈጻጸምን ማሻሻል

በ2015 በጀት ዓመት የታክስና የንግድ ማጭበርበር እንዲሁም ኮንትሮባንድን በመከላከል ፍትሀዊ የቀረጥና ታክስ አከፋፈል ስርዓት ለማስፈንና የህብረተሰቡን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ የታክስ ማጭበርበርን ከመከላከል አንጻር የታክስ ኢንተለጀንስ እና ኢንቨስትጌሽን ኦዲት ውጤታማ ሥራዎች መከናወናቸው፣ የሀሰተኛ ደረሰኞች ምንጭ የሆኑ የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽኖችን ማለትም ግብይት ሳይፈጸም ደረሰኝ የሚሸጡ፣ ሃሰተኛ ደረሰኞችን አትመው የሚያሰራጩ፣ በመንግስት የተሰጡ መብቶችን ያለአግባብ የሚገለገሉ ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ ክትትልና ኦፕሬሽን በማድረግ አጥፊዎች ለፍርድ እንዲቀርቡ ለፍትህ አካላት የማስተላለፍ ሥራ ተሰርቷል፡፡

ኮንትሮባንድን ከመከላከል አንጻር በህግ የተያዙ ዕቃዎች ማከማቻና መተላለፊያ አካባቢዎችን በጥናት የመለየት፣ ከፌዴራልና ክክልል የጸጥታ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት፣ የመቆጣጠሪያ ኬላዎችን አቅም በማጠናከር በ2015 በጀት ዓመት በአጠቃላይ ግምታዊ ዋጋቸው ብር 11.66 ቢሊዮን የሆነ የገቢና ወጪ ኮንትሮባንድ እቃዎች በቁጥጥር ስራ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ የንግድ ማጭበርበር እና ኮንትሮባንድን በመቆጣጠር ብር 84.87 ቢሊዮን ውጤት ሊገኝ የተቻለ ቢሆንም የጉምሩክና ታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድን ከመከላከል አንጻር በሚፈለገው ደረጃ ማረጋገጥ አለመቻሉ፣ የግብር ከፋዩ የህግ ተገዥነት በሚጠበቀው ደረጃ አለመድረሱ፣ ህገ ወጥነትን ለመከላከል የሚያስችል የግብዓት፣ የቴክኖሎጂና የመረጃ እጥረት መኖራቸው እና የቅንጅት ስራዎች ውጤታማነት አነስተኛ መሆኑ ታይቷል፡፡

በ2016 በጀት ዓመት የጉምሩክና ታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድን ከመከላከል አንጻር ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችል የሚመለከታቸውን አካላት ያሳተፈ፣ የህግ አስገዳጅነት ያለው፣ ከጎረቤት ሀገራት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል፣ የግብዓትና የቴክኖሎጂ ችግሮችን ከመሰረቱ ሊፈታ የሚችል የኮንትሮባንድ ፍሰት ባለበት አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ የኢኮኖሚ ችግር የሚፈታና የአገሪቱን የግብይት ስርዓት ከጥሬ ገንዘብ ዝውውር ነጻ በማድረግ

በባንክ ስርዓት ብቻ እንዲሆን ሊያደርግ የሚችል የንግድ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድ መከላከል ስትራቴጂ ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ይጠይቃል፡፡

ሰንጠረዥ 3: የታክስና ጉምሩክ የህግ ተገዥነት ማረጋገጥ ግብ የተጠቃለለ አፈጻጸም

| ዋና ዋና ተግባራት / ቁልፍ አመላካቾች / | ክብደት(ግብ) | ዒላማ | ክንውን | ክንውን (በክብደት | አፈጻጸም (%) |
|---|---|---|---|---|---|
| **የታክስ ማስታወቅና ክፍያ አቀራረብን ማጠናከር (ክብደት = 5)** | **5** | | | **5.1** | **101** |
| በሁሉም የታክስ ዓይነቶች በአማካይ ግብራቸውን በወቅቱ የሚያሳውቁ ግብር ከፋዮችን ማሳደግ | 1 | 52,857 | 63,620 | 1.2 | 120 |
| በወቅቱ የንግድ ትርፍ ግብራቸውን የሚያሳውቁ የግብር ከፋዮችን ማሳደግ | 0.8 | 29775 | 26453 | 0.7 | **89** |
| በወቅቱ የተጨማሪ እሴት ታክሳቸውን የሚያሳውቁ የግብር ከፋዮችን ማሳደግ | 0.6 | 26548 | 24074 | 0.5 | 91 |
| በወቅቱ የኤክሳይዝ ታክሳቸውን የሚያሳውቁ የግብር ከፋዮችን ማሳደግ | 0.8 | 502 | 571 | 0.9 | **114** |
| በሁሉም የታክስ ዓይነቶች ግብራቸውን በወቅቱ አሳውቀው የሚከፍሉ ግብር ከፋዮችን ማሳደግ | 0.3 | 21720 | 17648 | 0.2 | 81 |
| በወቅቱ አሳወቀው የንግድ ትርፍ ግብራቸውን የሚከፍሉ የግብር ከፋዮችን ምጣኔ ማሳደግ | 0.1 | 65 | 40.5 | 0.1 | **62** |
| በወቅቱ አሳውቀው የተ/እ/ታክሳቸውን የሚከፍሉ ታክስ ከፋዮችን ምጣኔ ማሳደግ | 0.2 | 41 | 39 | 0.2 | 95 |
| በወቅቱ አሳውቀው የኤክሳይዝ ታክሳቸውን የሚከፍሉ ታክስ ከፋዮችን ምጣኔ ማሳደግ | 0.2 | 70 | 66 | 0.2 | **94** |
| ከቀረቡ የታክስ ማስታወቂያዎች ስሌት የተሰራላቸውን ምጣኔ ማሳደግ | 1 | 100 | 99.98 | 1 | 100 |
| **የንግድ ማጭበርበር እና ኮንትሮባንድ መከላከል አፈጻጸምን ማሻሻል (ክብደት = 5)** | **5** | | | **6.1** | **122** |
| የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ውጤታማነት ማሳደግ | 1 | 86 | 86.36 | 1 | 100 |
| የኢንተለጀንስ ውጤታማነት ማሳደግ | 1 | 86 | 65.84 | 0.8 | 77 |
| የኮንትሮባንድ ፍሰትን በመለየት ኮንትሮባንድ የመያዝ አቅም ማሳደግ | 1 | 6.3 | 11.66 | 1.9 | 185 |
| የኮንትሮባንድ አስከፊነትን ለማህበረሰቡ ግንዛቤ ለመስጠት የተለያዩ መድረኮችን ማዘጋጀት | 1 | 49 | 76 | 1.6 | 155 |
| በኮንትሮባንድ ወንጀል የተሳተፉ ኮንትሮባንዲስቶችን በመለየት አስተማሪ እርምጃ መውሰድ | 1 | 95 | 90.3 | 1 | 95 |
| **የታክስ ከፋዮች ትምህርት፣ የኢንተለጀንስ ክትትል እና የኦዲት ሥራዎችን ማጠናከር (ክብደት = 15)** | **10** | | | **8.8** | **88** |
| በሁሉም የታክስ ዓይነቶች በፈቃደኝነት ግብራቸውን በወቅቱ የሚከፍሉ ግብር ከፋዮች ድርሻ ማሳደግ | 3 | 41.09 | 40 | 2.9 | 97 |
| በሁሉም የታክስ ዓይነቶች በፈቃደኝነት የተሰበሰበ ግብር ከጠቅላላ የግብር ገቢ ድርሻ ማሳደግ | 7 | 85.5 | 72 | 5.9 | 84 |

## 2.4 ዘላቂ የመንግስት ገቢ ዕድገት ማረጋገጥ

### 2.4.1 የገቢ አፈጻጸም ግምገማ

የገቢው ዘርፍ በ2015 በጀት ዓመት የተቋሙን ሁለንተናዊ አቅም በመገንባት የገቢ አሰባሰቡን ውጤታማ በማድረግ የመንግስትን የወጭ ፍላጎት ለመደገፍ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ከዚህ አኳያ በ2015 በጀት ዓመት ብር 450.29 ቢሊዮን ጥቅል ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 442.03

ቢሊዮን ወይም የዕቅዱን 98.16 በመቶ ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ ይህም አፈጻጸም ከአምና ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በብር 105.32 ቢሊዮን ወይም የ31.28 በመቶ እድገት አሳይቷል፡፡ ስለሆነም በገቢ አሰባሰብ ረገድ በየዓመቱ አበረታች የሆነ ውጤት የተመዘገበበት ቢሆንም ከመንግስት የወጪ ፍላጎትና ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ገቢ አኳያ በ2016 በጀት ዓመት ገና ብዙ ስራዎችን መስራት ይጠይቃል፡፡

ሰንጠረዥ 4: የዘላቂ የመንግስት ገቢ ዕድገት ማረጋገጥ ግብ የተጠቃለለ አፈጻጸም

| ዋና ዋና ተግባራት / ቁልፍ አመላካቾች / | ክብደት(ግብ) | ዒላማ | ክንውን | ክንውን (በክብደት | አፈጻጸም (%) |
|---|---|---|---|---|---|
| ከሀገር ውስጥ ታክስ የሚሰበሰብ ገቢን ማሳደግ (ክብደት = 35) | **35** | | | **35** | **100%** |
| ከቀጥታ ታክሶች የሚሰበሰብ ገቢ ማሳደግ በሚሊዮን ብር | 15 | 326,065 | 306,108 | 14.08 | 94 |
| ቀጥታ ካልሆኑ ታክሶች የሚሰበሰብ ገቢ ማሳደግ በሚሊዮን ብር | 10 | 112,305 | 125,961 | 11.22 | 112 |
| ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች የሚሰበሰብ ገቢ ማሳደግ በሚሊዮን ብር | 5 | 11,923 | 9,958 | 4.18 | 84 |
| ከተሰበሰበው ገቢ የክልሎችን ድርሻ በወቅቱ ማስተላለፍ (በሚሊዮን ብር) | 5 | 53,323 | 58,738 | 5.51 | 110 |
| የታክስ ዕዳ አሰባሰብ አቅም ማጎልበት (ክብደት = 5) | **5** | | | **6.4** | **128** |
| ከቆየ ዕዳ የሚሰበሰብ የዕዳ መጠንን ማሳደግ በሚሊዮን ብር | 1 | 10,815 | 20,147 | 1.9 | 186 |
| ከአዲስ (60 ቀን) ካልሞላው ዕዳ የሚሰበሰብ የዕዳ መጠንን ማሳደግ በሚሊዮን ብር | 4 | 33,090 | 37,670 | 4.6 | 114 |

# 3 የገቢው ዘርፍ የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ እንድምታዎችና የሚጠበቁ ውጤቶች

የገቢው ዘርፍ የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድን ለማሳካት የሚያስችሉ የዕቅዱ ታሳቢዎች፣ ስትራቴጂያዊ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና የሚጠበቁ ቁልፍ ውጤቶች እንደሚከተለው ተተንትነው ቀርበዋል።

## 3.1 የተጠቃለለ የተቋም ርዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዕሴቶች፣ ግቦች እና ዋና ዋና ተግባራት

ሰንጠረዥ 5: የተጠቃለለ ተቋማዊ ርዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዕሴቶች፣ ዓላማዎችና ዋና ዋና ተግባራት

| ርዕይ | በ2022 ዘመናዊ የታክስ እና የጉምሩክ አስተዳደር ስርዓት ተገንብቶ ሀገራዊ ወጪ በቀረጥና ታክስ ገቢ ተሸፍኖ ማየት | |
|---|---|---|
| **ስትራቴጂያዊ ግቦች** | **ተልዕኮ** | **ዕሴቶች** |
| 1. ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን ማጎልበት<br>2. ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ስርዓት ማጎልበት<br>3. የታክስና የጉምሩክ ህግ ተገዥነት ማረጋገጥ<br>4. ዘላቂ የመንግስተ ገቢ ዕድገት ማረጋገጥ | ብቃት ያለው የሰው ኃይል በማፍራት፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም፣ ፍትሀዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው የታክስና ጉምሩክ አገልግሎት በመስጠት ቀረጥና ታክስን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን በማዳበር የጉምሩክና ታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድን በመከላከልና በመቆጣጠር ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ መሰብሰብ | 1 አገልጋይነት<br>2 መሰጠት<br>3 ሙያዊ ብቃት<br>4 ታማኝነት<br>5 በቡድን መስራት |
| **ግብ 1: ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን ማጎልበት** | | |
| • የዕቅድ ዝግጅት፣ የክትትልና ግምገማ እና የስታቲስቲክስ መረጃ አስተዳደር አሰራር ማሻሻል<br>• የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል<br>• የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል<br>• የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽነ እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል | • የአጋርነትና የህዝብ ግንኙነት አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል<br>• ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልሎች የሚደረገውን ድጋፍና ክትትል ማሻሻል፣<br>• የስነ-ምግባር እና ጸረ-ሙስና የክትትል ስራዎችን ማሻሻል<br>• የሴቶች ማህበራዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ማሻሻል<br>• የበጎ አድራጎትና የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎችን ማሻሻል | |
| **ግብ 2: ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ስርዓትን ማጎልበት** | | |
| • የገቢ አሰባሰብ አሰራር ልዕቀትን ለማምጣት የህግ ማዕቀፎችን እና አሰራሮችን ማሻሻል<br>• የቀረጥና ታክስ መረጃ አስተዳደር ውጤታማነቱን ማረጋገጥ | • የኤሌክትሮኒክ ታክስ(E-Tax) አጠቃቀምን ማሻሻል<br>• የቀረጥና ታክስ ከፋዮች አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ማረጋገጥ | |
| **ግብ 3፡ የታክስና የጉምሩክ ህግ ተገዥነት ማረጋገጥ** | | |
| • የታክስ ማስታወቅና ክፍያ አቀራረብን ማጠናከር፣<br>• የቀረጥና ታክስ ከፋዮች ትምህርት፣ የኢንተለጀንስ ክትትል እና የኦዲት ስራዎችን ማጠናከር፣ | • የቀረጥና ታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድ መከላከል አፈጻጸምን ማሻሻል | |
| **ግብ 4፡ ዘላቂ የመንግስት ገቢ ዕድገት ማረጋገጥ** | | |
| ዘላቂ የገቢ ዕድገት ማረጋገጥ | | |

## 3.2 የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ታሳቢዎች

በዚህ ክፍል ለገቢው ዘርፍ ለ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ እንደ መነሻ ሊያገለግሉ የሚችሉ ሀገራዊ የመካከለኛ ዘመን (2016-2020) የማክሮ ኢኮኖሚ እና ፊሲካል ማዕቀፍ እንደ አንድ መነሻ የተወሰደ ሲሆን የመንግስትን የፊሲካል አቋም አስተማማኝ ደረጃ ላይ ማድረስ የሚቻለው አስተማማኝ ከሆነው የመንግስት ቀረጥና ታክስ ገቢ ምንጭ የገቢ አሰባሰብ ከፍተኛ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ ከመቼውም ጊዜ በላይ አማራጭ የሌለው መሆኑ በመንግስት ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የቀረጥና ታክስ ገቢ አሰባሰብ ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲመጣ የሚያስችሉ የማሻሻያ ስራዎችን በመለየት ትኩረት ሰጥቶ ተግባራዊ ማድረግ ዋናው የፊሲካል ታሳቢ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

### 3.2.1 አጠቃላይ የኢኮኖሚ ታሳቢዎች

በበጀት ዓመቱ የሀገሪቷ አጠቃላይ ኢኮኖሚ በማክሮ ኢኮኖሚ ፊሲካል ማዕቀፍ ላይ በተገለጸው መሰረት በየዓመቱ የሚያድግ መሆኑ፣ የገቢ ዕቃዎች በየአመቱ እየጨመረ የሚሄድ መሆኑ፣ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት እየተሻሻለ እንደሚሄድ እና የቀረጥና ታክስ አሰባሰቡን እንደሚያሻሽሉ በታሳቢነት ተወስደዋል፡፡

- በማዕቀፍ ዘመኑ (2016-2018) ኢኮኖሚው ዕድገት እንደሚኖረው፣
- በአሁኑ ወቅት የዋጋ ንረቱ በተከታታይ ተጠናክሮ በሚወሰድ የፊሲካል ፖሊሲ፣ የገንዘብ ፖሊሲ፣ የዋጋ ማረጋጊያ እርምጃዎች እና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በሚሰሩ ስራዎች እየቀነሰ እንደሚመጣ፣

### 3.2.2 የታክስ ገቢ ታሳቢዎች

- **የ2015 በጀት ዓመት የታክስ ገቢ ዕቅድ አፈጻጸም፦** የፌዴራል መንግስት በ2015 በጀት ዓመት ከታክስ እና ታክስ ካልሆኑ የተጣራ የገቢ ምንጮች ብር 408.27 ቢሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 348.59 ቢሊዮን ወይም የዕቅዱን 85.38 በመቶ ማሳካት ተችሏል፡፡ በመሆኑም የ2015 በጀት ዓመት የታክስና ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች አፈጻጸም ለ2016 በጀት ዓመት የታክስና ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች እቅድ ዝግጅት እንደመነሻ ተወስዷል፡፡
- **የክልሎች የጋራ ገቢ ድርሻ ከፍተኛ እየሆነ መምጣት በሚሰበሰበው የፌዴራል ገቢ ድርሻ ላይ የሚኖረው እንደምታ፦** በ2015 በጀት ዓመት በፌዴራል መንግስት ተሰብስቦ ለክልሎች የተላለፈው የጋራ ገቢ ድርሻ ብር 48.56 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን ይህም በ2014 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ ተሰብስቦ ከተላለፈው አንጻር በ40 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ ይህም ከፌዴራል መንግስት የሚታጣው የገቢ ድርሻ ከተጠበቀው በላይ በመሆኑ የፌዴራል መንግስት ገቢ እየቀነሰ መሄዱን ያሳያል፡፡ ስለሆነም ይህ እውነታ የ2016 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት የታክስ ገቢ ዕቅድ ሲዘጋጅ እንደ አንድ ታሳቢ ተወስዷል፡፡
- **የማክሮ ኢኮኖሚ ታሳቢዎች ለታክስ ገቢ ትንበያ ያላቸው እንደምታ፦** የማክሮ ኢኮኖሚ ታሳቢዎችና ሊኖር የሚችለው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለታክስ ገቢ አቅም በየታክስ ዓይነቱ (የቀጥታ ግብርና ታክስ፣ የአገር ውስጥ ኤክሳይዝና ተጨማሪ እሴት ታክሶችና

የገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ፣ ኤክሳይዝ፣ ተ.እ.ታ. እና ሱር ታክሶች) የሚኖራቸው እንደምታ በዝርዝር ለገቢ ዕቅዱ እንደ አንድ ታሳቢ ታይቷል።

- **የታክስ ፖሊሲ ማሻሻያ ታሳቢዎች፦** ከተያዘው በጀት ዓመት ጀምሮ ለፓርላማ ቀርበው እንደሚጸድቁና ሥራ ላይ እንደሚውሉ የሚጠበቁ የታክስ ህጎች በቀጣዮቹ በጀት ዓመታት ለታክስ ገቢ አሰባሰቡ የሚኖራቸውን ተጨማሪ አቅም ከግምት ውስጥ ገብቷል። ከ2015 በጀት ዓመት ጀምሮ የቀረቡትን የታክስ ህግ ማሻሻዎች ተግባራዊ በማድረግ በ2016 በጀት ዓመት ብር 93.1 ቢሊዮን ተጨማሪ የታክስ ገቢ መሰብሰብ ይቻላል የሚል ግምት ተወስዷል። በቀጣዮቹ ዓመታት ማሻሻያዎቹን የበለጠ አጠናክሮ ተግባራዊ በማድረግም የበለጠ የታክስ ገቢ መሰብሰብ እንደሚቻል በማሰብ የተለጠጠ ዕቅድ ተይዟል። በመሆኑም እነዚህን በሥራ ላይ ለማዋል የታቀዱት ዋና ዋና የታክስ ህጎች የሚከተሉት ናቸው።
    - **የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ፡-** ታክሱ ሊጣልባቸው የሚገባ ወደ ታክስ መረቡ እንዲገቡ በማድረግ፣ እንዲሁም አዳዲስ አገልግሎቶችና ዕቃዎች እንዲካተቱ በማድረግ ከተ.እ.ታ. ምንጭ የሚሰበሰበው ከሀገር ውስጥ ምርት አንጻር 1 በመቶ ገቢውን እንደሚጨምር ታሳቢ ተደርጓል።
    - **ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ፡-** ይህ ማሻሻያ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ በቅንጦት ዕቃዎች እንዲሁም ለጤና ጥሩ ያልሆኑ ምርቶች ፍጆታ በመቀነስ በጤና ላይ ሊደርስ የሚችል አደጋ መቀነስ ነው። ታክሱ የሚጣለው በተወሰኑ ዕቃዎች፣ ተሽከርካሪዎች እና አገልግሎቶች ላይ በመሆኑ የ2016 በጀት ዓመት ገቢን በ10 ቢሊዮን ብር እንደሚጨምር ታሳቢ ተደርጓል።
    - **የኤክሳይዝ ቴምብር (Excise Stamp, and Track and Trace System) ፡-** ኤክሳይዝ የተጣለባቸው ዕቃዎች ላይ የሚሰበሰብ ገቢ ሲሆን ይህም ተግባራዊ ሲደረግ ህገ-ወጥ ንግድን በማስቀረት ወይም በመቀነስ (በሲጋራ፣ አልኮልና የአልኮል ውጤቶች በተለይ) ከኤክሳይዝ ታክስ ሊገኝ የሚችለው ገቢ በ30 ቢሊዮን ብር ሊጨምር እንዲሚችል ታሳቢ ተደርጓል።
    - **የማህበራዊ ዋስትና ልማት ቀረጥ፡-** ከፍትሐዊነት አንጻር ሲታይ በተለይ የሱር ታክስ በተወሰኑ ዕቃዎች ላይ የሚጣል ታክስ ከመሆኑም በላይ ከሌሎች ታክስች ቀጥሎ በመጨረሻ የሚጣል በመሆኑ ከፍተኛ የጉምሩክ ቀረጥ የከፈለ ይበልጥ ከፍተኛ ሱር ታክስ እንዲከፍል የሚያደርግ ሲሆን ቀረጥ የማይከፈልበት ዕቃ ሱር ታክስ እንዳይከፈልበት የሚያደርግ ነበር። በመሆኑም የማህበራዊ ዋስትና ቀረጥ በሁሉም ገቢ ዕቃዎች ላይ የሚጣል ታክስ ሲሆን ይህም ገቢውን እንደሚጨምር ታሳቢ ተደርጓል።
    - **የንብረት ታክስ (Property Tax) ህግ፡-** አዲስ የንብረት ታክስ ህግ ተግባራዊ ለማድረግ የታቀደ ሲሆን ከዚህ የሚገኘውም ገቢ ሙሉ በሙሉ የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች እንደሚሆን ተወስኗል። ለዚህም ታክስ ትግባራ ሌሎች ህጎች ጸድቀው ተግባራዊ እንደሚሆኑና ይህም የታክስ መሰረቱን እንደሚያሰፋና የታክስ ገቢ በተለይም የክልሎችን ገቢ እንደሚጨምር ግምት ተወስዷል።
- **የታክስ አስተዳደር ማሻሻያዎች፡-** የገቢ ሰብሳቢ ተቋማት የሰው ሀይልና ተቋማዊ አቅምና የአሠራር ችግሮችን እና አደረጃጀቱን በጥልቀት በመፈተሽ አስፈላጊ የሆኑ

ማሻሻያዎችን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን፣ ለዚህም በተግባር ተጨባጭ ለውጥ እንዲመጣ በመንግስት በኩል ቁርጠኝነት እንደሚኖር ታሳቢ ተደርጓል። በተጨማሪም በኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ ገቢ የሚያገኙ ነገር ግን ግብርና ታክስ የማይከፍሉ የተለያዩ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ዘርፍ ውስጥ የሚሳተፉ የኢኮኖሚ ተዋናዮችን በግብር ሥርዓቱ ማስገባት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባና ማሻሻያ ማካሄድ አስፈላጊ እንደሆነ ታሳቢ ተደርጓል።

በዚሁ መነሻ የሚወሰዱ የታክስ አስተዳደር ማሻሻያዎች ለገቢ አሰባሰቡ ዋና ቁልፍ ጉዳይ መሆናቸውን በመገንዘብ የታክስ አስተዳደሩ ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን የቀረጥና ታክስ ገቢ ለመሰበሰብ ወይም በየስትራቴጂክ ዘመኑ የተቀመጡትን ዒላማዎች ለማሳካት የሚያስችሉ የገቢ ፊሲካል ስራዎች በልዩ ትኩረትና ርብርብ መስራት የሚጠበቅበት ይሆናል።

- በታክስና ጉምሩክ አስተዳደሩ ረገድ ትኩረት ከተደረገባቸው ማሻሻያዎች መካከል የኦዲት አፈጻጸም ማሻሻያ፣ የቀረጥና ታክስ ዕዳ አሰባሰብ፣ የመረጃ አስተዳደር፣ የንግድ ማጭበርበርና የኮንትሮባንድ መከላከልና መቆጣጠር ስራዎችን አፈጻጸም ማሻሻል እንዲሁም የህግ ማስከበር ስራዎችን አጠናክሮ የማስቀጠል ማሻሻያዎች እንደሚደረጉ ይጠበቃል።
- የታክስ አሰባሰቡን ለማዘመን የተጀመሩ የጉምሩክና ታክስ አስተዳደር ስርዓት ተግበራትን ማለትም የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና አስተዳደር፣ ዜጎች ቀረጥና ታክስን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህላቸው እንዲዳብር የጉምሩክና ታክስ ትምህርትን የማስፋፋት፣ የቀረጥና ታክስ ንቅናቄ በተጠናከረ ሁኔታ ተግባራዊ በማድረግ የቀረጥና ታክስ አሰባሰቡ ላይ ለውጥ እንዲመጣ ይሰራል።

## 3.3 ስትራቴጂያዊ የትኩረት አቅጣጫዎች

በ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ዘመን የገቢው ዘርፍ የለያቸውን ግቦች ለማሳካት የሚያስችሉ ስትራቴጂክ አቅጣጫዎች የተለዩ ሲሆን በነዚህ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት የሚሰራ ይሆናል።

### 3.4 ቀረጥና ታክስ በፈቃደኝነት የመክፈል ባህል ማሳደግ

የዚህ ስትራቴጂያዊ የትኩረት አቅጣጫ ዋና ዓላማ ቀረጥና ታክሰ በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን ማዳበር ሲሆን ይህንንም ለማሳካት የህግ ተገዥነት ስትራቴጂ በመቅረጽ መተግበርን የሚያጠቃልል ነው። አቅጣጫው ቀረጥና ታክስ ከፋዩን በልዩ ልዩ የግንኙነት አግባቦች በማስተማር፣ በመደገፍ እና ዕውቅና በመስጠት አብዛኛው ቀረጥና ታክስ ከፋይ በፈቃደኝነት ግዴታውን እንዲወጣ ማስቻል ሲሆን የህግ ተገዥነት ባህሪ ለውጥ ማምጣት ባልቻሉ አካላት ላይ ተመጣጣኝ የህግ ማስከበር ተግባር ተፈጻሚ የሚደረግበት ነው።

### 3.5 ዲጂታል የቀረጥና ታክስ ገቢ አስተዳደር ስርዓትን መገንባት

ዲጂታል የቀረጥና ታገቢ አስተዳደር ስርዓት የመገንባት አቅጣጫ ታሳቢ የሚያደርገው አጠቃላይ የታክስ እና የጉምሩክ አስተዳደር ስርዓቱን ዓለም በደረሰበት የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርዓት እንዲደገፍ ማድረግን ነው፡፡ ይህ የዲጂታል የገቢ አስተዳደር ስርዓት ለአገልግሎት ተቀባዩ ግልጽ፣ ቀላል፣ ተገማች እና ተደራሽ አገልግሎት በመስጠት፣ የህግ ተገዥነትና አስተዳደራዊ ወጪ በመቀነስ እና የተገልጋዩን ዕርካታ በላቀ ደረጃ በማረጋገጥ የገቢውን ዘርፍ ተልዕኮ ማሳካት ነው፡፡

### 3.6 የቀረጥና ታክስ አስተዳደር ፍትሀዊነትን ማረጋገጥ

በኢ-መደበኛ ኢኮኖሚ፣ በህገ ወጥ ንግድ፣ በቀረጥና ታክስ ማጭበርበር እና በኮንትሮባንድ ምክንያት ከሀገሪቱ ኢኮኖሚ መሰብሰብ ያለበትን ገቢ ለመሰብሰብ አልተቻለም፡፡ በዚህ ምክንያት የንግዱ ማህበረሰብ በዕኩልነት ተወዳዳሪ እንዳይሆን እንቅፋት ሆኖ የቆየና በሀገሪቱ ያለውን የሃብት ክፍፍል ኢ-ፍትሀዊ እንዲሆን አድርጓል፡፡ በመሆኑም የገቢው ዘርፍ ይሄንን ተግዳሮት ለማስተካከል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመስራት ወደ ታክስ መረቡ ያልታቀፉትን እንዲታቀፉ በማድረግ እንዲሁም የቀረጥና ታክስ ህጎችን በሁሉም ቀረጥና ታክስ ከፋዮች ላይ በእኩል ደረጃ ተፈጻሚ በማድረግ የቀረጥና ታክስ ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ ስለሆነም በመካከለኛ ስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመኑ የህግ ማስከበር ስራዎችን በማጠናከር እንዲሁም ከአጋር እና ተባባሪ አካላት ጋር ተቀናጅቶ በመስራት ኢፍታዊነትን በመከላከል የዜጎችን የጋራ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ ለመሰብሰብ የሚሰራ ይሆናል፡፡

### 3.7 የውስጥ እና የውጭ ስትራቴጂክ አጋርነትን ማጠናከር

የገቢ አሰባሰብ ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ከሀገር ውስጥና ከውጭ አጋር እና ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ለአንድ ዓላማ በጋራ መንቀሳቀስን ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ይህ አቅጣጫ የቴክኒክ፣ የዕውቀት ሽግግር፣ የመረጃ ልውውጥ፣ ህገወጥነትን የመከላከል አሰራር መዘርጋትን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ በዚህ መሰረት አጋር አካላትን መለየት፣ ግንኙነት እና ስምምነት በመፍጠር በስምምነቱ መሰረት ለመፈጸም ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችንና ማነቆዎችን በጋራ ለይቶ በመፍታት ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ነው፡፡

### 3.8 የዳበረ የስራ ባህል ማምጣት

የታክስ ስርዓቱን ውጤታማ ለማድረግ የተቋሙን ርዕይ፣ ተልዕኮ እና ዕሴቶችን የተላበሰ እና ሁለንተናዊ አቅሙን በመገንባት የዳበረ የስራ ባህል ያለው የሰው ኃይል ማፍራትን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ ይህ አቅጣጫ የሰው ኃይል ስራ አመራር ልማት ስትራቴጂ ከመቅረጽ ጀምሮ፣ ብቃት ያለው የሰው ኃይል መሳብና ማቆየት፣ የምዘና፣ የማትጊያ እና የተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋትና መተግበር፣ ምቹ የስራ ከባቢ መፍጠር፣ ታማኝና ለስራ ተነሳሽ የሆነ አመራር እና ፈጻሚ ማፍራትን የሚያጠቃልል ነው፡፡

# 4 የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ግቦች፣ ዒላማዎችና የድርጊት መርሃ-ግብር

## 4.1 ግብ-1. ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን ማጎልበት

ይህ ስትራቴጂክ ግብ ከተቋም አቅም ግንባታ ጋር የተያያዙ ዘጠኝ (9) የሚሆኑ ዋና ዋና ተግባራትን ያካተተ ሲሆን በዋናነት የዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ፣ የሰው ሀብት መሳብ፣ ማቆየት፣ ብቃት ማሳደግን፣ የሀብት አጠቃቀም እና ውጤታማነት ማረጋገጥን፣ የመረጃ ቴክኖሎጂ የአጠቃቀም ውጤታማነትን፣ የአጋርነት እና የህዝብ ግንኙነት ስራዎች ውጤታማነትን፣ የክልሎች ድጋፍና ክትትልን፣ የስነ-ምግባር እና ፀረ ሙስና የክትትል ስራዎችን፣ የሴቶች ማህበራዊ ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ ስራዎች እና የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች ውጤታማ መሆናቸውን ማረጋገጥ የሚቻልበት ግብ ነው።

### 4.1.1 የዕቅድ ዝግጅት፣ የክትትልና ግምገማ እና የስታቲስትካል መረጃ አስተዳደር አሰራር ማሻሻል

**መግለጫ**

የገቢው ዘርፍ ዕቅድ ከሀገራዊ ዕቅድ አና ከጉምሩክ ኮሚሽን ዕቅድ ጋር ተጣጥሞ የሚዘጋጅና አፈጻጸሙንም የተደራጀ የገቢ ስታቲስቲካል መረጃዎችን በመያዝና በመተንተን በሪፖርት፣ በክትትል፣ በመስክ ምልከታ፣ በየጊዜው በሚደረጉ የአፈጻጸም ግምገማዎች እና በሚሰጡ ግብረ መልሶች መሰረት የሚፈጸም ዋና ተግባር ነው።

**ዝርዝር ተግባራት**

የገቢውን ዘርፍ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ ዕለታዊ ገቢ እየሰበሰቡ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨትን፣ የክትትል እና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት፣ ገቢ ነክ የሆኑ መረጃዎችን ማደራጀት፣ በቴክኖሎጂ ማስደገፍ፣ የገቢ መረጃዎችን መተንተን፣ በጥቅም ላይ ማዋል፣ የገቢ ትንበያ ስራዎችን ማከናወን፣ ሪፖርቶችን ማዘጋጀት እና በየጊዜው ወቅታዊ ግብረ መልስ መስጠትን የሚያጠቃልል ነው።

**ውጤት፡- የተዘጋጀ ዕቅድ፣ ተደራጅቶ የተያዘ የገቢ መረጃ**

### 4.1.2 የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል

**መግለጫ**

የሰው ኃይል ልማትና አስተዳደር ውጤታማነት ማሳደግ ማለት ሁለንተናዊ አቅሙ የተገነባና የረካ አመራርና ፈጻሚ በመፍጠር የተቋሙን ምርታማነት ማሻሻል ነው፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

ግልጽነት የተፈነበት የሰው ኃይል ስምሪት ማካሄድ፣ የአመራሩን ክህሎት ማሳደግ ፣ የሰራተኛውን ብቃት መገንባት፣ ጠንካራ የስራ ባህል መገንባት፣ የሰራተኛ ደህንነትና ጤንነት የሚጠበቅበትን የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈና ውጤታማ የመረጃ አያያዝና የምዘና ስርዓት መገንባት፣ ምቹ የስራ ከባቢ መፍጠር፣ የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት፣ ሰራተኛን በመሳብና በማቆየት እና ዕርካታውን በማረጋገጥ ምርታማነቱን ማሳደግን ያጠቃልላል፡፡

**ውጤት፡- የረካና ምርታማነቱ ያደገ ሰራተኛ**

### 4.1.3 የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል

**መግለጫ**

የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ ማለት ተቋሙ የተሰጠውን ተልዕኮ ለማሳካት አስፈላጊ ሀብት እንዲመደብ የማድረግና የተመደበውን ሀብት በውጤታማነት ማስተዳደር ነው፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነት ማረጋገጥ፣ የግዥ ፍላጎትን መለየት እና ጥራቱን የጠበቀ ግዥ መፈጸምና ውጤታማነቱን ማረጋገጥ፣ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ክፍያ እና ግዥን በተሟላ ሁኔታ በስራ ላይ ማዋል፣ የንብረት አያያዝ እና የጥገና ወጪዎችን መቀነስ፣ የቋሚ ሀብቶችንና የግብዓቶች አቅርቦትና አስተዳደር አፈጻጸምን ማሻሻል፣ በበጀት አጠቃቀም እና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ከተቆጣጣሪ አካላት በሚቀርቡ የኦዲት ግኝቶች ላይ ወቅታዊ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድን ይጨምራል፡፡

**ውጤት፦ ውጤታማ የሀብት አጠቃቀም**

### 4.1.4 የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል

**መግለጫ**

የቴክኖሎጂ ልማት አጠቃቀምን ማሳደግ ማለት ለአገልግሎት አሰጣጥ፣ ለህግ ማስከበር ስራዎች፣ ለገቢ አሰባሰቡ ውጤታማነት እና ሌሎች የተቋሙን የአሠራር ስርዓቶች የሚደግፉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የመግዛት፣ የማልማት፣ የማስተዳደር፣ የመጠቀም እና የማሻሻል ስራዎችን የሚያካትት ነው፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

የቀረጥና ታክስ ገቢ አስተዳደርን ሙሉ በሙሉ በዲጂታል ቴክኖሎጂ ለመቀየር የሚያስችሉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች ማለትም አዲስ የዳታ ማዕከል መገንባት፣ የመጠባበቂያ ዳታ ማዕከል መገንባት፣ ለመረጃ ደህንነት የሚረዱ ፖሊሲዎችን በስራ ላይ ማዋል፣ ያሉትን የመረጃ መሰብሰቢያና ማደራጃ ሶፍትዌሮችን ማሻሻል፣ ተጨማሪ የመረጃ ቋቶች መመስረት፣ በስራ ላይ ያለውን የሲግታስ ስርዓት ኢ-ማሳወቅና ኢ-ክፍያ በያዘ መልኩ ሙሉ በሙሉ ወደ መረጃ መረብ ወደሆነ አዲስ ቴክኖሎጂ መተካት፣ የተከፋፈሉ ስርዓቶችን እርስ በእርስ እንዲናበቡና እንዲቀናጁ ማድረግ ይጠበቃል።

ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ማለትም የክልል እና ከተማ አስተዳደር ገቢ ሰብሳቢ ተቋማት፣ ኢትዮቴሌኮም፣ የኢንፎርማሽን ደህንነት መረብ አስተዳደር፣ ገንዘብ ሚኒስቴር፣ ትራንስፖርት ሚኒስቴር፣ ንግድ ሚኒስቴር፣ ብሄራዊ ባንክና ንግድ ባንኮች ጋር ለክፍያና ለመረጃ ልውውጥ የሚያገለግሉ ኢንተርፌሶች በተመሳሳይ ወጥ በሆነ መንገድ እንዲተዳደሩ ማድረግ፣ ግብር ከፋዩ በቀጥታ የሚያቀርባቸውን የአገልግሎት ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችሉ የመተግበሪያ ሶፍትዌሮች ማሻሻልና እንደአስፈላጊነቱ አዳዲስ በማልማት በስራ ላይ ማዋል፣ የታክስና የጉምሩክ የቴክኖሎጂ ስርዓቶች ሙሉ በሙሉ ለመረጃ ቅብብሎሽ ማስተሳሰር፣ በስራ ላይ የነበረውን የካርጎ ስካኒንግ ስርዓት በዘመናዊ ቴክንሎጂ መተካት፣ የካርጎ ትራኪንግ ስርዓትን ተግባራዊ ማድረግ፣ የጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት ማሻሻል፣ የአንድ መስኮት አገልግሎት ሁለተኛ ምዕራፍን ማጠናቀቅና ተግባራዊ ማድረግ፣ የጉምሩክ ዋጋ ዳታቤዝ(ECVS-G2) ሲስተምን ማሻሻል፣ የቢዝነስ ኢንተለጀንስ እና ዳታ አናሊቲክስ ስርዓት መዘርጋት፣ የጉምሩክ ዕቃዎች ዋጋ ዝርዝር ማስገቢያ(VDD) ማሻሻል፣ ለትራንስፖርት ሚኒስቴር የሚረዳ ከVDD ጋር የሚሰራ የተሽከርካሪ ማረጋገጫ ስርዓት(VVS) ስርዓት ማሻሻል ይጠቀሳሉ።

በተጨማሪም አሁን በስራ ላይ ያለውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ስርዓት ሙሉ በሙሉ በኢ-ኢንቮይስ ስርዓት መቀየር፣ የእጅ በእጅ ደረሰኝ መከታተያ ስርዓት ማሻሻል፣ ያሉትን የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች መከታተያ (FD) ማሻሻል፣ የገበያ ዋጋ ማስገቢያ ስርዓት ማሻሻል፣ በስራ ላይ ያለውን ዳታዌር ሃውስ በአዲስ አሰራርና ቴክኖሎጂ መቀየር፣ የጣት አሻራ ስርዓት ከብሔራዊ መታወቂያ ጋር ማስተሳሰር፣ የጥሪ ማዕከል ስርዓትን የማሻሻል ስራዎች ይሰራሉ።

የኮርፖሬት ስራዎችን ወረቀጥ አልባ ለማድረግ የሚያግዙ የኢንተርፐራይዝ ሪሶርስ ፕላኒንግ ማለትም የሰው ሃብት አስተዳደር፣ የግዥ አስተዳደር ስርዓት፣ የፔይሮል ሲስተሙን ከኢፊሚስ ሲስተም ጋር ማስተሳሰር፣ የንብረት አስተዳደር እና ጠቅላላ አገልግሎት ከኢፊሚስ ሲስተም ጋር ማስተሳሰር፣ የተሽከርካሪ መከታተያ እና የመሳሰሉትን ያካትታል።

**ውጤት፦ በቴክኖሎጂ የተደገፉ ውጤታማ አሠራሮች**

### 4.1.5 የአጋርነት እና የህዝብ ግንኙነት አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል

**መግለጫ**

የሀገር ውስጥ አጋር አካላት ትብብር ማሻሻል ማለት ተቋሙ በህግ የተሰጠውን ስልጣንና ኃላፊነት ለመወጣት ቁልፍ ሚና ካላቸው የባለድርሻ አካላት ማለትም ከተቆጣጣሪ አካላት፣ ከክልልና ከከተማ አስተዳደር፣ ከፌዴራል ተቋማት፣ ከንግድና ሙያ ማህበራት ጋር ቅንጅት በመፍጠር አገልግሎቱን በማሳለጥ፣ ንግድና ኢንቨስትመንትን በማበረታታት፣ የጉምሩክና ታክስ ማጭበርበር እንዲሁም ኮንትሮባንድ መከላከልን ያጠቃልላል፡፡ የውጭ ሀገራትና ድርጅቶች አጋርነት ማጠናከር ማለት ተቋሙ ተልኮውን ለማሳካት እንዲያስችለው ከውጭ ሀገራት፣ ዓለም ዓቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ጋር የቴክኒክ ድጋፍ እና ተሞክሮ ማግኘት የሚያስችል ትብብር መፍጠርን የሚያካትት ነው፡፡ የገቢውን ዘርፍ ስራዎች በህዝብ ግንኙነት ተግባራት የማጀብ ስራዎች የሚከናወኑበት ዋና ተግባር ነው፡፡

### ዝርዝር ተግባራት

ከአገር ውስጥ ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅት የሚፈጥረባቸው ስትራቴጂክ ጉዳዮችን እና ቅንጅቱ የሚፈጠርባቸውን አካላት መለየት እና በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የስምምነት ሰነድ በመፈራረም ተግባራዊ ማድረግን ያጠቃልላል፡፡ የውጭ አገራት አጋር አካላት ድጋፍና ትብብር አንጻር ተቋሙ ተልኮውን ለማሳካት እንዲያስችለው ትብብር መፍጠር አስፈላጊ የሆነባቸውን የውጭ ሀገራት፣ ዓለም ዓቀፋዊና አህጉራዊ ድርጅቶችን፣ የቴክኒክ ድጋፍ ዓይነቶችን የመለየት፣ ትብብር በመፍጠር የጉምሩክ እና የታክስ የሁለትዮሽ እና የብዝዮሽ ስምምነት የመፈራረም፣ በአህጉራዊ እና በዓለም ዓቀፍ መድረኮች ላይ በመሳተፍ ለተቋሙ ጥቅም በሚያስገኙ ጉዳዮች ላይ መደራደር እና በተፈጠሩ ግንኙነቶች የተገኙ የቴክኒክ ድጋፎች ውጤታማ መሆናቸውን ማረጋገጥ የሚጠይቅ ነው፡፡

### ውጤት፦ የተፈጠረ ውጤታማ ግንኙነት፣ የተገኘ የቴክኒክ ድጋፍ

## 4.1.6 ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልሎች የሚደረገውን ድጋፍና ክትትል ማሻሻል

### መግለጫ

ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልሎች የሚደረገውን ድጋፍና ክትትል ማሻሻል ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ለጉምሩክ ኮሚሽን በዕቅድ ዝግጅት፣ በግምገማ፣ በሪፖርት፣ በመስክ ምልከታ፣ በግብረ መልስ አሰጣጥ እና በመሳሰሉት ያልተቋረጠ እና ተከታታይነት ያላቸው ድጋፎችን በማድረግ ውጤታማ የሆነ ተቋማዊ ትስስር በመፍጠር የገቢ አሰባሰቡ እንዲሳካ ማድረግ ነው፡፡

ሀገራዊ የታክስ አስተዳደር ስርዓት ማጣጣም ማለት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ተልዕኮ መነሻ በማድረግ ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ በብቃት ለመሰብሰብ፣ ኢንቨስትመንትን ለመደገፍና ለማበረታታት፣ ፍትሃዊ የንግድ ውድድርን በማጐልበት፣ በፌደራልና በክልሎች/ከተማ መስተዳድሮች ጋር ጠንካራ ኢኮኖሚያዊ ትስስር በመፍጠር በሀገር ደረጃ የተጣጣመ የታክስ አስተዳደር ስርዓት መፍጠርን ያካትታል፡፡

### ዝርዝር ተግባራት

የጉምሩክ ኮሚሽን ዕቅድን በመገምገምና የማስተካከያ ግብረ መልስ በመስጠት እንዲሁም አብሮ በመስራት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ዕቅድ ጋር የተናበበ እና የተጣጣመ እንዲሆን ማድረግ፣ የየሩብ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶችን መገምገም እና መስተካከል ባለባቸው ጉዳዮች ዙሪያ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ግብረ መልስ መስጠት እና በግብረ መልሱ መሰረት መስተካከላቸውን በግብረ መልስ ግብረ መልስ ወይም በአካላዊ ምልከታ ማረጋገጥ እና በመጨረሻም በየሩብ ዓመቱ አፈጻጸሞችን በጋራ መገምገምን ያጠቃልላል፡፡

የታክስ አስተዳደር ተግባራትን በፌደራል እና በክልሎች/ከተማ መስተዳደሮች በሁሉም ዕኩል ተፈጻሚ እንዲሆኑ የሚያስችል የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፣ የክልሎችን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት ያደረገ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት ቀርጾ መተግበር፡፡ በሀገር ደረጃ የታክስ አስተዳደሩ በመረጃ ቴክኖሎጂ በማስደገፍ ጠንካራ የመረጃ ቅብብሎሽና አጠቃቀም ስርዓት መዘርጋት፣ በክልል በሚገኙ የፌደራል ገቢ ሰብሳቢ ቅ/ጽ/ቤቶችና በክልል የገቢ ባለስልጣናት መካከል በህግ ማስከበር፣ በግብር ከፋዮች ትምህርትና ድጋፍ፣ በአቅም ግንባታና በሌሎች የታክስ ጉዳዩች የጋራ ስምሪት ማድረግና የገቢ አሰባሰቡን ማሻሻል፣ ከክልል የገቢ ሰብሳቢና የፋይናንስ ዘርፍ ተቋማት ጋር ቋሚ የግንኙነት ስርዓት (ማለትም የምክክር መድረኮችን) በመዘርጋት የታክስ ፖሊሲና አስተዳደር አፈጻጸሞችን በጋራ መገምገም፣ መፍትሄ ማስቀመጥና አፈጻጸማቸውን መከታተል፣ የጋራ ገቢዎች እና በዊዝሆልዲንግ ስርዓት የሚሰበሰቡ ግብርና ታክሶች በወቅቱ ወደ ገቢው ባለቤቶች መተላለፋቸውን ማረጋገጥ እና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ለማጠናከር የሚረዱ ወጥ የሆኑ የስልጠና ካሪኩለሞችን ማዘጋጀት ናቸው፡፡

**ውጤት፦ የተጣጣመ ሀገራዊ የታክስ አስተዳደር፣ ውጤታማ የሆነ ተጠሪ ተቋም**

### 4.1.7 የስነ-ምግባርና ፀረ ሙስና የክትትል ስራዎችን ማሻሻል

**መግለጫ**

የስነ-ምግባርና ፀረ ሙስና የክትትል ስራዎችን ማሻሻል ማለት የስጋት ስራ አመራርን ማጠናከር ማለት ሲሆን በተቋም ደረጃ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶችን አስቀድሞ በመለየት፣ የስጋት መጠኑን በመቀነስ ተቋማዊ ጤንነትን ማረጋገጥ ነው፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

ይህን ተግባር ለማሳካት የሚከናወኑ ስራዎች የስጋት መከላከያ ስትራቴጂ ወቅታዊ ማድረግ፣ ተቋማዊ ስጋቶችን በየጊዜው ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች አንጻር መለየት፣ መተንተን፣ ደረጃ ማውጣት፣ በተቋም ደረጃ የተለዩ ስጋቶችን ለመቀነስ ኃላፊነት የሚወስዱ ባለቤቶችን መለየት፣ የስጋት ስትራቴጂውን መተግበር እና ውጤታማነቱን ማረጋገጥን የሚያጠቃልል ሲሆን ከዚህ አኳያ በብልሹ አሰራር ዙሪያ ጥቆማ የሚቀርብባቸውን ጉዳዮች እንዲስተካከሉ ማድረግ፣ ለብልሹ አሰራር የተጋለጡ አሰራሮች በጥናት በመለየት የሚሻሻሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት እና የሃብት ምዝገባ ማካሄድን የሚጨምር ነው፡፡

**ውጤት፡- የቀነሰ የስጋት ተጋላጭነት**

### 4.1.8 የሴቶች ማህበራዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ማሻሻል

**መግለጫ**

የሴቶች ማህበራዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ማሻሻል ማለት በዓለም ዓቀፍ ህጎች እና መንግስት በሴቶችና በወጣቶች፣ በህጻናት፣ በአካል ጉዳተኞች፣ በኤች. አይ. ቪ. ኤድስ፣ በጤና፣ በስርዓተ ጾታ ዙሪያ ያወጣቸውን የተለያዩ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና መመሪያዎችን በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተሟላ ሁኔታ እንዲተገበሩ ማድረግ ነው።

**ዝርዝር ተግባራት**

በዚህ ዋና ተግባር ስር ሴቶች፣ ወጣቶች፣ ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞችን እና የኤች. አይ. ቪ ኤደስ ጉዳዮችን በተመለከተ መንግስት ያወጣቸውን ፖሊሲ እና ስትራቴጂዎችን ትኩረት ሰጥቶ በዕቅድ ውስጥ አካቶ መተግበርን፣ የሴቶች አመራር ሰጪነት እና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥን፣ የህጻናት ማቆያ አገልግሎቶችን በማስፋት የሴት ተጠቃሚዎችን ማሳደግ፣ የሴቶችን አቅም በስልጠና ማጎልበት እና ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የሆነ የስራ ቦታ መፍጠርን የሚያጠቃልል ነው።

**ውጤት፦ ያደገ የባለብዙ ዘርፍ ስራዎች ውጤታማነት**

### 4.1.9 የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎችን ማሻሻል

**መግለጫ**

የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎችን ማሻሻል ማለት የገቢው ዘርፍ ለልማት የሚያስፈልገውን ገቢ ከመሰብሰብ ባሻገር የበጎ አድራጎትና ማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች ማለትም አካባቢ ጥበቃ፣ የአቅመ ደካማ ማህበረሰብ ቤቶችን በመገንባት፣ ደም በመለገስ፣ ችግኝ በመትከል፣ ወላጅ የሌላቸውን ህጻናት በማሳደግ የማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችሉ ስራዎች የሚያከናውነበት ነው።

**ዝርዝር ተግባራት**

ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ቤተሰብ ተማሪዎችን ትምህርታቸውን እነዲከታተሉ በገንዘብ መደገፍ፣ የአቅመ ደካማ ማህበረሰብ መኖሪያ ቤቶችን መገንባት፣ ደም መለገስ፣ ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናትን መንከባከብ፣ በኤች አይ ቪ ኤደስ የተጎዱ የህብረሰተብ ክፍሎችን ማገዝ እና የመሳሰሉትን ስራዎች መስራትን እንዲሁም የአረንጓዴ ልማት እና የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች ማከናወንን፣ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ለሚጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ማድረግን ያካትታል።

**ውጤት፦ ውጤታማ የበጎ አድራጎት ስራዎች**

## 4.2 ግብ-2 ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ስርዓትን ማጎልበት

ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስ አስተዳደር ስርዓትን ማጎልበት ማለት የአገልግሎት አሰጣጡን ግልጽ፣ ቀላል፣ ቀልጣፋ፣ ተገማች፣ ወጪ ቆጣቢ እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ እና ዓለም ዓቀፍ ደረጃቸውን ከጠበቁ አሠራሮች ጋር በማጣጣም ተቋማዊ ለውጥ ማምጣትን የሚጠይቅ ነው፡፡ ለአገልግሎት አሰጣጥ ማነቆ የሆኑ የአሰራር ስርዓት ማሻሻያዎችን የማድረግ፣ የመረጃ አስተዳደር ስርዓትን የመዘርጋት እና ውጤታማነቱ የሚረጋገጥበት ተግባር ጭምር ነው፡፡

### 4.2.1 የገቢ አሰባሰብ አሰራር ልዕቀትን ለማምጣት የህግ ማዕቀፎችን እና አሰራሮችን ማሻሻል

**መግለጫ**

ቀጣይነት ያለው የህግና የአሰራር ስርዓት ማሻሻል ማለት የታክስና የጉምሩክ የህግ ማዕቀፎች እና የአሠራር ስርዓቶችን በመቅረጽና በማሻሻል የላቀ አገልግሎት ለመስጠት፣ የህግ ተገዥነት ለማረጋገጥ እና የገቢ አሰባሰቡን ውጤታማ ማድረግን የሚያካትት ነው፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ፣ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ አዋጅ፣ የጉምሩክ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎችን መቅረጽና በማሻሻል በሚመለከተው አካል ማጸደቅን፤ የኢ-ኮሜርስ ንግድ ስርዓትን ለማሳለጥ የሚያስችል የታክስና የጉምሩክ አሰራር ስርዓት፣ የታክስና የጉምሩክ ኦፕሬሽናል አሰራሮችን ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ አድርጎ ማሻሻልና መቅረጽ፣ የህግ ተገዥነት አሰራሮች የንግድ ማጭበርበርን ለመከላከል በሚያስችል መልኩ ማሻሻልና መቅረጽን እንዲሁም ተግባራዊ የተደረጉ የህግ፣ መመሪያና አሰራሮች ውጤታማነት በጥናት በመለየት የማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብን የሚያጠቃልል ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ለፍትህ አካላት የሚቀርቡ የፍትሃብሄር ጉዳዮች የመርታት አቅም ማሳደግን፣ ለአቤቱታ የሚቀርቡ የፍትሃ ብሄር ጉዳዮች የመዝገብ ምጣኔ መቀነስን፣ በስጋት ስራ አመራር መርህ መሰረት ከተለዩ ግብር ከፋዮች የግኝት ምጣኔ ማሳደግን በተጨማሪነት የሚያካተት ነው፡፡

**ውጤት፡- የላቀ የአሰራር ስርዓት ፣ ያደገ የተገልጋይ እርካታ**

### 4.2.2 የታክስና ጉምሩክ መረጃ አስተዳደርና አጠቃቀም ውጤታማነት ማሻሻል

**መግለጫ**

የታክስና ጉምሩክ መረጃ አስተዳደርና አጠቃቀም ውጤታማነት ማሻሻል ማለት ለታክስና ጉምሩክ አስተዳደሩ አስፈላጊ የሆኑ የመረጃ ምንጮችን መለየት፣ መረጃ መሰብሰብ፣ ማጥራትና

ማደራጀት፣ መተንተን፣ ማሰራጨትና ጥቅም ላይ ማዋልን፣ ለቀረጥና ታክስ ውሳኔዎች የተሰራጩ መረጃዎች ውጤታማነት ማረጋገጥን፣ የመረጃ አስተዳደር ፖሊሲ እና አጠቃቀም ስርዓት በመዘርጋት የመረጃ ደህንነት ማረጋገጥን የሚያጠቃልል ነው።

**ዝርዝር ተግባራት**

የመረጃ አስተዳደር ፖሊሲ ስራ ላይ ማዋልን፣ የተቋሙን የመረጃ ምንጭ ማስፋትና የጥራት ደረጃውን ማሳደግን፣ የመረጃ ልውውጡን በቴክኖሎጂ ማስደገፍን፣ ለቀረጥና ታክስ ውሳኔ አገልግሎት ላይ የሚውሉ መረጃዎችን ውጤታማነት እያሳደጉ መሄድን፣ ቀጠናዊና ዓለም ዓቀፋዊ የመረጃ ትስስር መፍጠርን፣ የኢንተለጀንስ መረጃዎችን መጋራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣ የመረጃ ደህንነትና ጥራት ማስጠበቅ፣ ትልልቅ መረጃዎችን ለመተንተን የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት፣ የመረጃ ማከማቻ ማዕከል መገንባት እና የተቋሙን የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርዓት በአርተፊሺያል ኢንተለጀንስ ማስደገፍን፣ የሀገር ውስጥ ታክስና ጉምሩክ መረጃ ቅብብሎሽን ማሳደግን፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አጠቃቀም እና ተደራሽነት ውጤታማ እንዲሆን ማድረግን፣ የግዥና ሽያጭ መረጃ ማደራጀትን እንዲሁም የገበያ ዋጋ መረጃ መሰብሰብን ያጠቃልላል።

**ውጤት፡- የላቀ የመረጃ አያያዝ ስርዓት እና አጠቃቀም**

### 4.2.3 የኤሌክትሮኒክ ታክስ(E-Tax) አጠቃቀምን ማሻሻል

**መግለጫ**

የኤሌክትሮኒክ ታክስ(E-Tax) አጠቃቀምን ማሻሻል ማለት ግብር ከፋዮች ወደ ገቢው ተቋም በአካል መምጣት ሳይጠበቅባቸው የበይነ መረብ ስርዓትን ተጠቅመው በኦላይን ግብርና ታክሳቸውን አሳውቀው የሚከፍሉበት ስርዓት ነው።

**ዝርዝር ተግባራት**

ግብር ከፋዮችን የመለየት፣ ስልጠና የመስጠት፣ ቴክኖሎጂውን ለመጠቀም የሚያስችል የይለፍ ቃል የመስጠት፣ በስርዓቱ አሳውቀው እንዲከፍሉ የመከታተል፣ ስርዓቱን በማይጠቀሙት ላይ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድን የሚያጠቃልል ነው።

**ውጤት፡- የላቀ የኢ-ታክስ አጠቃቀም**

### 4.2.4 የግብር ከፋዮች አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ማርጋገጥ

**መግለጫ**

አገልግሎት አሰጣጥን ከማሳለጥ አንጻር ለተገልጋዩ በቀጥታ /Online/ አገልግሎት የሚያገኝበት ስርዓትን ማሻሻል፣ የአገልግሎት ተደራሽነትን ማስፋት፣ ዘመናዊ የቅሬታና አቤቱታ አፈታት ስርዓት መዘርጋትና ማሻሻል፣ የአገልግሎት መስጫ ጊዜ ጥናት (Time Release Study) ማካሄድ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ስምምነት ሰነድ በየጊዜው ወቅታዊ ማድረግ፣

የመረጃ አቅርቦት ማዕከሎችን (Contact Center) አፈጻጸም ማሻሻል፣ የደንበኞች አቀባበልና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋት፣ ለተገልጋዩ እንደየ ባህሪው እና ደረጃው ልዩ አገልግሎት ማግኘት የሚችልበት የአገልግሎት ስርዓት መዘርጋት፣ ዓለም ዓቀፍ የአገልግሎት አሰጣጥ ልህቀት ዕውቅና ማግኘት እና የተገልጋይ እርካታ ማረጋገጥን የሚያጠቃልል ነው።

**ዝርዝር ተግባራት**

የአገልግሎት አሰጣጡን ማሻሻል፣ ተገልጋዮች በተቀመጠው ቻርተር መሰረት አገልግሎት መስጠት፣ ለቅሬታ ወቀታዊ ምላሽ መስጠት፣ ለታክስ ተመላሽ ፈጣን ምላሽ መስጠት፣ ለሚቀረቡ ሌሎች የአገልግሎት ጥያቄዎች ፈጣንና ቀልጣፋ ምላሽ መስጠት፣ የተገልጋዩን የእርካታ ደረጃ ማረጋገጥ፣ የተገልጋዮች የአገልግሎት የእርካታ ደረጃቸውን ለማወቅ ዳሰሳዊ ጥናት ማካሄድን ያጠቃልላል።

**ውጤት፡- ያደገ የአገልግሎት አሰጣጥ፣**

## 4.3 ግብ-3 የታክስና የጉምሩክ ህግ ተገዥነት ማረጋገጥ

የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነትን የሚወስኑ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ቢኖሩም የገቢ ሰብሳቢው ተቋም የማስፈጸም ብቃት ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል። ስለዚህ ተቋሙ በአደረጃጀቱና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀሙ ብቃት ያለው የሰው ኃይል በመጠቀምና ዓለም ዓቀፍ ተሞክሮዎችን በመቀመር ውጤታማ የህግ ተገዥነት ሥራ መሥራት ይጠበቅበታል። የህግ ተገዥነትን ማረጋገጥ ታክስን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህል ለማዳበር፣ የንግድ ፍትሀዊነትን ለማስፈን፣ የህብረተሰቡን ደህንነት ለመጠበቅና ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን የታክስ ገቢ በብቃት እንዲሰበሰብ ያስችላል። በመሆኑም የታክስ ከፋዮች ትምህርት ለማጠናከር፣ የስጋት ስራ አመራር አፈጻጸምን ለማሳደግ፣ የታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድ መከላከል አፈጻጸምን ለማሻሻል እና አስተማሪ የሆኑ ህጋዊ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋትና ማሳደግን ታሳቢ ያደረገ ነው።

### 4.3.1 የታክስ ማስታወቅና ክፍያ አቀራረብን ማጠናከር

**መግለጫ**

የታክስ ማስታወቅና ክፍያ አቀራረብን ማጠናከር ማለት ታክስ ከፋዮች በሁሉም የታክስ ዓይነቶች በታክስ ህጉ መሰረት የንግድ እንቅስቃሴያቸው በሚያሳየው የሂሳብ ሰነዳቸው መሰረት የሚጠበቅባቸውን የታክስ ግዴታ በፈቃደኝነት በወቅቱ አሳውቀው ትክክለኛውን ግብርና ታክስ እንዲከፍሉ ማድረግ ነው።

**ዝርዝር ተግባራት**

በሁሉም የታክስ ዓይነቶች በአማካይ ግብራቸውን በወቅቱ የሚያሳውቁ ግብር ከፋዮች ድርሻ ማሳደግን፣ በወቅቱ የንግድ ትርፍ ግብራቸውን የሚያሳውቁ የግብር ከፋዮች ድርሻ ማሳደግን፣

በወቅቱ የተጨማሪ እሴት ታክሳቸውን የሚያሳውቁ የግብር ከፋዮች ድርሻ ማሳደግን፣ በወቅቱ የኤክሳይዝ ታክሳቸውን የሚያሳውቁ የግብር ከፋዮች ድርሻ ማሳደግን፣ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች ግብራቸውን በወቅቱ አሳውቀው የሚከፍሉ ግብር ከፋዮች ድርሻ ማሳደግን፣ በወቅቱ አሳወቀው የንግድ ትርፍ ግብራቸውን የሚከፍሉ የግብር ከፋዮች ምጣኔ ማሳደግን፣ በወቅቱ አሳውቀው የተጨማሪ እሴት ታክሳቸውን የሚከፍሉ ታክስ ከፋዮችን ምጣኔ ማሳደግን፣ በወቅቱ አሳውቀው የኤክሳይዝ ታክስቸውን የሚከፍሉ ታክስ ከፋዮችን ምጣኔ ማሳደግን እና የስሴት ስራዎችን ውጤታማ ማድረግን የሚያጠቃለል ነው።

**ውጤት፦ ያደገ የህግ ተገዥነት**

### 4.3.2 የታክስ ከፋዮች ትምህርት፣ የኢንተለጀንስ ክትትል እና የኦዲት ስራዎችን ማጠናከር

**መግለጫ**

የታክስ ከፋዮች ትምህርት፣ የኢንተለጀንስ ክትትል እና የኦዲት ስራዎችን ማጠናከር ማለት ታክስ ከፋዮችን እንደየ ስጋት ባህርያቸው በመለየት ለህግ ተገዥ የሆኑትን ማበረታታትና የላቀ አገልግሎት በመስጠት፣ ለህግ ተገዥ ያልሆኑትን የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት በመዘርጋት ሊያደርሱ የሚችሉትን ጉዳት በመከላከል የህግ ተገዥነትን በማሳደግ የገቢ አሰባሰቡን ውጤታማ ማድረግ ነው።

**ዝርዝር ተግባራት**

የታክስ ህግ ተገዥነት አፈጻጸምን ለማሻሻል የትምህርት ስትራቴጂ ማሻሻል እና መተግበርን፣ ትምህርቱ ያመጣውን ፋይዳ በመገምገም ቀጣይነት ያለው ማሻሻያ ማድረግን፣ ለታክስ ህጉ ተገዥ የሆኑትን በመለየት ዕውቅናና ሽልማት መስጠትን፣ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች በፈቃደኝነት ግብራቸውን በወቅቱ የሚከፍሉ ግብር ከፋዮች ድርሻ ማሳደግን፣ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች በፈቃደኝነት የተሰበሰበ ግብር ከጠቅላላ የግብር ገቢ ድርሻ ማሳደግን እና የኦዲት ስትራቴጂ በማሻሻልና በመተግበር የኦዲት ውጤታማነት ማረጋገጥን የሚያጠቃልል ነው።

የስጋት ስራ አመራር ስትራቴጂ ማሻሻልና በተሟላ ሁኔታ መተግበር፣ የስጋት ፕሮፋይል ማደራጀትና ወቅታዊ ማድረግ፣ የስጋት መመዘኛ መስፈርቶች ልየታ ሥርዓት ማሻሻል፣ ስጋቶችን መለየትና መተንተን፣ የስጋት ደረጃ ማውጣትና በስትራቴጂው መሰረት ማስተናገድ፣ የስርዓቱ ውጤታማነት በመገምገምና የማስተካከያ ዕርምጃ በመውሰድ የአገልግሎት አሰጣጥና የቁጥጥር ሚዛናዊነት በጠበቀ መልኩ መመራቱን ማረጋገጥን ያካትታል።

**ውጤት፦ ያደገ በፈቃደኝነት የተከፈለ የገቢ ድርሻ፣ ያደገ የህግ ተገዥነት ደረጃ**

### 4.3.3 የታክስ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድ መከላከል አፈጻጸምን ማሻሻል

**መግለጫ**

የታክስ ማጭበርበር እና ኮንትሮባንድ መከላከል አፈጻጸምን ለማሻሻል የታክስና ጉምሩክ ህግና የአስተዳደር ሥርዓት የማይፈቅድ ህገወጥ ተግባራት ላይ ከተሰማሩ አካላት ግንዛቤያቸውን በማሳደግ ወደ ህጋዊ መስመር መመለስ የሚችሉት ወደ ታክስ መረቡ እንዲገቡ ማገዝ፣ ከጥፋታቸው መታረም ያልቻሉትን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም፣ ከአጋር አካላት ጋር በመቀናጀት አስተዳደራዊና ህጋዊ ዕርምጃ በመውሰድ ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡና ሌሎችም እንዲማሩበት ማድረግ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድን የሚጨምሩ ሥራዎች ማከናወን ነው፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

በታክስ ማጭበርበር፣ በኮንትሮባንድና በተለያዩ ህገወጥ ተግባራት ላይ የተሰማሩትን ቀረጥና ታክስ ከፋዮች በማስተማር እንዲመለሱ ማድረግ፣ በኢንተለጀንስ ክትትል፣ በድንገተኛ ፍተሻ፣ በኢንቨስትጌሽን ኦዲት እና በወንጀል ምርመራ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ እንደየጥፋት ደረጃቸው አስተማሪ የሆነ ህጋዊ ዕርምጃ እንዲወሰድባቸው በማድረግ የህግ ተገዥነት የሚረጋገጥበት ስራዎች ማከናወንን ያካትታል፡፡

ኮንትሮባንድና ንግድ ማጭበርበር ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ስጋት በማይሆኑበት ደረጃ ለመቀነስ ተቋማዊ የመከላከል አቅምን ማጠናከር፣ ከፌዴራል ተቋማት፣ ከክልሎች አደረጃጀቶች፣ ከጎረቤት ሀገራት እና አለም አቀፍ የህግ ማስከበር ተቋማት ጋር ቅንጅት መፍጠር፣ በኮንትሮባንድ አስከፊነትና ጉዳት ዙሪያ የህዝብ ንቅናቄ መፍጠር፣ የኮንትሮባንድ ፍሰት ባለበት አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ ሕጋዊ የኢኮኖሚ አማራጭ እንዲኖረው ማድረግ እና የኮንትሮባንድ መከላከል ሥራውን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ማስደገፍ ያስፈልጋል፡፡

**ውጤት፡- የቀነሰ የጉምሩክና ታክስ ማጭበርበር እና ኮንትሮባንድ**

## 4.4 ግብ-4 ዘላቂ የመንግስት ገቢ ዕድገትን ማረጋገጥ

### 4.4.1 ዘላቂ ገቢ ዕድገት ማረጋገጥ

ከቀረጥና ታክስ የሚሰበሰበውን ገቢ በብቃት ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን በማጎልበት፣ ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስ አስተዳደር ስርዓትን በማጎልበት እና የታክስና የጉምሩክ ህግ ተገዥነት በማረጋገጥ ከቀጥታ እና ቀጥታ ካልሆኑ ታክሶች እንዲሁም ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች የሚሰበሰበውን የገቢ መጠን ማሳደግ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በፈቃደኝነት ከሚከፈለው ገቢ በተጨማሪ የገቢ ፊዚካል ስራዎች ውጤት ከሆኑት ከውዝፍ ዕዳ እና ከተወረሱና ከተያዙ ንብረቶች ሽያጭ የሚገኝ ገቢን ማሳደግን የሚያጠቃልል ነው፡፡

**ውጤት፡- ያደገ ገቢ**

ሰንጠረዥ 6: የሃገር ውስጥ ታክስ የ2016 በጀት ዓመት የገቢ ዕቅድ

| ተ.ቁ | ቅርንጫፍ | የ2016 የገቢ ዕቅድ |
|---|---|---|

| | | |
|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 226,089,116,077.62 |
| 2 | መካከለኛ - 1 | 32,941,139,899.45 |
| 3 | መካከለኛ - 2 | 22,285,564,624.98 |
| 4 | ምስራቅ | 3,579,967,605.06 |
| 5 | ምዕራብ | 4,385,735,582.22 |
| 6 | ሰሜን ምዕራብ | 1,308,749,702.53 |
| 7 | አዳማ | 3,852,562,336.99 |
| 8 | ባህር ዳር | 10,800,343,209.88 |
| 9 | ድሬዳዋ | 4,718,180,046.24 |
| 10 | ሀዋሳ | 3,453,688,551.21 |
| 11 | ጅማ | 1,817,187,300.20 |
| 12 | ኮምቦልቻ | 2,020,629,035.86 |
| 13 | መቀሌ | 2,077,106,897.94 |
| **ድምር** | | **319,329,970,870.18** |

ሰንጠረዥ 7: የወጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ የ2016 በጀት ዓመት የገቢ ዕቅድ

| ተ.ቁ. | የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ስም | የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ |
|---|---|---|
| 1 | መቀሌ | 1,358,230,407.00 |
| 2 | ሞጆ | 61,582,060,399.00 |
| 3 | አዳማ | 22,621,434,789.97 |
| 4 | አ/አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ | 15,432,084,702.17 |
| 5 | ድሬዳዋ | 21,042,790,537.85 |
| 6 | አ/አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ | 66,082,060,399.00 |
| 7 | ሰመራ | 5,278,576,226.24 |
| 8 | ጅግጅጋ | 4,025,415,382.81 |
| 9 | ጅማ | 186,261,618.65 |
| 10 | ባሕር ዳር | 2,806,393,311.38 |
| 11 | አዋሽ | 372,972,326.01 |
| 12 | ኮምቦልቻ | 4,156,226,332.95 |
| 13 | ሞያሌ | 3,686,122,214.66 |
| 14 | ሀዋሳ | 1,299,957,904.24 |
| 15 | ጋላፊ | 70,000,000.00 |
| **ድምር** | | **210,000,586,551.93** |

ሰንጠረዥ 8: የሃገር ውስጥና የወጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ የ2016 በጀት ዓመት የገቢ ዕቅድ

| ተ.ቁ. | የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ስም | የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ |
|---|---|---|
| 1 | ሞጆ | 61,582,060,399.00 |
| 2 | አዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ | 15,432,084,702.17 |
| 3 | አዳማ | 26,473,997,126.96 |

| ተ.ቁ. | የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ስም | የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ |
|---|---|---|
| 4 | ድሬዳዋ | 25,760,970,584.09 |
| 5 | ምዕራብ አዲስ አበባ | 4,385,735,582.22 |
| 6 | አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ | 66,082,060,399.00 |
| 7 | ሰመራ | 5,278,576,226.24 |
| 8 | ጅግጅጋ | 4,025,415,382.81 |
| 9 | መቀሌ | 3,435,337,304.94 |
| 10 | ጅማ | 2,003,448,918.85 |
| 11 | ምሥራቅ አዲስ አበባ | 3,579,967,605.06 |
| 12 | ሀዋሳ | 4,753,646,455.45 |
| 13 | ሰሜን ምዕራብ | 1,308,749,702.53 |
| 14 | መካከለኛ ግብር ከፋዮች-2 | 22,285,564,624.98 |
| 15 | አዋሽ | 372,972,326.01 |
| 16 | ኮምቦልቻ | 6,176,855,368.81 |
| 17 | ሞያሌ | 3,686,122,214.66 |
| 18 | ከፍተኛ ግብር ከፋዮች | 226,089,116,077.62 |
| 19 | ባሕር ዳር | 13,606,736,521.26 |
| 20 | መካከለኛ ግብር ከፋዮች-1 | 32,941,139,899.45 |
| 21 | ጋላፊ | 70,000,000.00 |
| **ድምር** | | **529,330,557,422.11** |

## 4.5 ለ2016 በጀት ዓመት የተቀመጡ ግቦች፣ ዒላማዎች እና የድርጊት መርሃ-ግብር

### 4.5.1 ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሃብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን ማጎልበት

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2015 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2016 በጀት ዓመት ግብ(መድረሻ) | በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 1 | ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት (ክብደት = 15) | | | | | | | | |
| 1.1 | የዕቅድ ዝግጅት፣ የክትትልና ግምገማ እና የስታቲስቲክስ መረጃ አስተዳደር አሰራር ማሻሻል (ክብደት = 1) | | | | | | | | |
| 1.1.1 | ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ ዕቅድና ሪፖርት ሰነድ ማዘጋጀት | 0.4 | በቁጥር | 10 | 11 | 5 | 2 | 2 | 2 |
| 1.1.2 | የክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት | 0.3 | በቁጥር | 2 | 2 | 1 | 1 | | |
| 1.1.3 | የዘርፉን መረጃ አያያዝ በቴክኖሎጂ በመደገፍ ማደራጀት | 0.3 | በመቶኛ | 25 | 50 | 25 | 30 | 40 | 50 |
| 1.2 | የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል (ክብደት=2) | | | | | | | | |
| 1.2.1 | ግልጽነት የሰፈነበት የሰው ኃይል ስምሪት ማካሄድ | 0.2 | በመቶኛ | 88.5 | 97.5 | 97.5 | 97.5 | 97.5 | 97.5 |
| 1.2.2 | ለአመራር እና ለሰራተኞች የሚሰጡ ሥልጠናዎችን ማሳደግ | 1 | በቁጥር | 6,974 | 6,000 | 788 | 2,034 | 1,965 | 1,213 |
| 1.2.3 | የውስጥ የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት | 0.1 | በቁጥር | 1 | 1 | | 1 | | |
| 1.2.4 | የሰራተኛ እርካታን በማሳደግ ፍልሰትን መቀነስ | 0.5 | በመቶኛ | 3.7 | 3.5 | | | | 3.5 |
| 1.2.5 | የሰራተኛ ዕርካታ ማሳደግ | 0.2 | በመቶኛ | 46 | 52 | | | | 52 |
| 1.3 | የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል (ክብደት=3) | | | | | | | | |
| 1.3.1 | የተመደበ በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል (ድርሻ) | 0.5 | በመቶኛ | 97 | 100 | 24.41 | 47.75 | 76.07 | 100.00 |
| 1.3.2 | የኦዲት ግኝት ማስተካከያ አፈጻጸም | 1 | በመቶኛ | 71.5 | 85 | | | | 85 |
| 1.3.3 | የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ክፍያን ድርሻ ማሳደግ | 0.5 | በመቶኛ | 72 | 90 | 90 | 90 | 90 | 90 |
| 1.3.4 | የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዢን ድርሻ ማሳደግ | 0.5 | በመቶኛ | 48 | 62.5 | 62.5 | 62.5 | 62.5 | 62.5 |
| 1.3.5 | የንብረት አያያዝ እና የጥገና ወጪዎችን መቀነስ | 0.5 | በሚሊዮን በብር | 191.5 | 174.02 | | | | 174.01 |
| 1.4 | የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል (ክብደት=2) | | | | | | | | |
| 1.4.1 | መረጃ ቋት ማደራጀት | 0.4 | በመቶኛ | 50 | 60 | 50 | 50 | 50 | 60 |
| 1.4.2 | በተቋሙ ወረቀት አልባ አሰራርን መተግበር | 0.3 | በመቶኛ | 50 | 55 | 50 | 50 | 50 | 55 |
| 1.4.3 | በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ኦቶሜት ማድረግ | 0.3 | በመቶኛ | 90 | 93 | 90 | 91 | 92 | 93 |
| 1.4.4 | የተገልጋዮችን እርካታ ደረጃ ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 86 | 88 | | | | 88 |
| 1.5 | የአጋርነት እና የህዝብ ግንኙነት አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል (ክብደት = 1) | | | | | | | | |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2015 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2016 በጀት ዓመት ግብ(መድረሻ) | በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 1.5.1 | የሀገር ውስጥ አጋር አካላት አጋርነትና ትብብር ማሻሻል | 0.4 | በመቶኛ | 78 | 83 | 83 | 83 | 83 | 83 |
| 1.5.2 | የውጭ አገራትና ድርጅቶች አጋርነትና ትብብር ማሻሻል | 0.3 | በመቶኛ | 85 | 88.5 | 88.5 | 88.5 | 88.5 | 88.5 |
| 1.5.3 | መረጃዎችን በተለያዩ የተግባቦት ዘዴዎች ተደራሽ ማድረግ | 0.3 | በመቶኛ | 86 | 90.5 | 90.5 | 90.5 | 90.5 | 90.5 |
| **1.6** | **ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልሎች የሚደረገውን ድጋፍና ክትትል ማሻሻል (ክብደት=2)** | | | | | | | | |
| 1.6.1 | የተጠሪ ተቋማት ዕቅድን ከዘርፍ ዕቅድ ጋር ማናበብና ማጣጣም | 0.25 | በቁጥር | 2 | 1 | 1 | | | |
| 1.6.2 | የየሩብ ዓመት የተጠሪ ተቋማት ሪፖርት መገምገም | 0.25 | በቁጥር | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 1.6.3 | የክልሎችን ዕቅድ ከዘርፍ ዕቅድ ጋር ማናበብና ማጣጣም | 0.5 | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | | | |
| 1.6.4 | በየሩብ ዓመት ከክልሎች ጋር የዘርፍ አፈጻጸም በጋራ መገምገም | 0.5 | በቁጥር | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 1.6.5 | ለክልሎች ወቅታዊ የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት | 0.2 | በቁጥር | 1,560 | 800 | 214 | 200 | 180 | 206 |
| 1.6.6 | የተጣጣመ ሀገራዊ የታክስ አስተዳደር አፈጻጸም ውጤታማነት | 0.3 | ኢንዴክስ | 89 | 90 | | 90 | | 90 |
| **1.7** | **የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና የክትትል ሥራዎችን ማሻሻል (ክብደት=1)** | | | | | | | | |
| 1.7.1 | በብልሹ አሰራር ዙሪያ ጥቆማ ከተደረገባቸው ውስጥ ማስተካከያ የተደረገባቸው | 0.25 | በመቶኛ | 90 | 93.5 | | | | 93.5 |
| 1.7.2 | ለብልሹ አሰራር የተጋለጡ አሰራሮች በጥናት በመለየት የማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብ | 0.25 | በቁጥር | 37 | 45 | 9 | 10 | 11 | 15 |
| 1.7.3 | የሀብት ምዝገባ ያካሄዱ አመራሮች እና ባለሞያዎች ድርሻ ማሳደግ (በዲጂታል) | 0.5 | በመቶኛ | 53 | 72.5 | 72.5 | 72.5 | 72.5 | 72.5 |
| **1.8** | **የሴቶችና ማሕበራዊ ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነትን ማሻሻል (ክብደት=1)** | | | | | | | | |
| 1.8.1 | የህጻናት ማቆያ አገልግሎት ተጠቃሚ ሴት ሰራተኞች ብዛት ማሳደግ | 0.25 | በቁጥር | 398 | 502 | 418 | 436 | 458 | 502 |
| 1.8.2 | ወደ አመራር የመጡ ሴት ሰራተኞች ብዛት ማሳደግ | 0.25 | በቁጥር | 30 | 37.5 | 33.14 | 34.76 | 35.89 | 37.5 |
| 1.8.3 | ሥልጠና ያገኙ ሴት ሰራተኞች ድርሻ ማሳደግ | 0.25 | በመቶኛ | 2,524 | 4,152 | 713 | 1,133 | 1,213 | 1,093 |
| 1.8.4 | ለአካል ጉዳተኛ ሰራተኞችና ተገልጋዮች ምቹ የስራ ሁኔታና ቦታ መፍጠር | 0.25 | በመቶኛ | 85 | 91.5 | 91.5 | 91.5 | 91.5 | 91.5 |
| **1.9** | **የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎችን ማሻሻል (ክብደት=2)** | | | | | | | | |
| 1.9.1 | የአረንጓዴ አሻራ ተግባራትን ማካሄድ/ችግኞችን መትከል | 0.5 | በቁጥር | 180,000 | 35,000 | 35,000 | | | |
| 1.9.2 | የአቅመ ደካማ ማህበረሰቦች የመኖሪያ ቤቶች መገንባት | 0.15 | በቁጥር | 35 | 16 | 16 | | | |
| 1.9.3 | የአቅመ ደካማ ማህበረሰቦች የመኖሪያ ቤቶች መገንባት | 0.15 | በሚሊዮን | 30 | 11 | 11 | | | |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2015 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2016 በጀት ዓመት ግብ(መድረሻ) | በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| | | | ብር | | | | | | |
| 1.9.4 | የአቅመ ደካማ ቤተሰብ ተማሪዎች ድጋፍ | 0.15 | በቁጥር | 1,000 | 1,500 | 1,500 | | | |
| 1.9.5 | የአቅመ ደካማ ቤተሰብ ተማሪዎች ድጋፍ | 0.15 | በሚሊዮን ብር | 3 | 3.5 | 3.5 | | | |
| 1.9.6 | ለተለያዩ ማህበራዊ ቀውሶች የተደረገ ድጋፍ | 0.3 | በሚሊዮን ብር | 1,175 | 1,339 | 335 | 335 | 335 | 335 |
| 1.9.7 | የተደረገ ደም ልገሳ (ድርሻ ከሰራተኛ ብዛት) | 0.3 | በመቶኛ | 2.2 | 2.4 | 0.6 | 0.6 | 0.6 | 0.6 |
| 1.9.8 | ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናትን መደገፍ | 0.3 | በቁጥር | 218 | 227 | 211 | 214 | 221 | 227 |

## 4.5.2 ቁልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የቀረጥና ታክስ አስተዳደር ስርዓትን ማጎልበት

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2015 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2016 በጀት ዓመት ግብ(መድረሻ) | በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| **2** | **ቁልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የቀረጥና ታክስ አስተዳደር ስርዓትን ማጎልበት (ክብደት = 25)** | | | | | | | | |
| **2.1** | **የገቢ አሰባሰብ አሰራር ልህቀትን ለማምጣት የህግ ማዕቀፎችን እና አሰራሮችን ማሻሻል (ክብደት=6)** | | | | | | | | |
| 2.1.1 | ለፍትህ አካላት የሚቀርቡ የፍትሃብሔር ጉዳዮች በመዝገብ የመርታት አቅምን ማሳደግ | 2 | በመቶኛ | 87.3 | 91 | 89.13 | 89.76 | 90.39 | 91 |
| 2.1.2 | በስጋት ከተለዩ ግብር ከፋዮች የግኝት ምጣኔን ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 92.3 | 93 | | | | 93 |
| 2.1.3 | የአስመጪዎች ፕሮፋይል በየጊዜው በማሻሻል የስጋት ስራ አመራር ውጤታማነት (Targeting) ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 76.96 | 87.72 | 87.72 | 87.72 | 87.72 | 87.72 |
| 2.1.4 | የቢዝነስ አመቺነትን ለማሻሻል በዝቅተኛና መካከለኛ ስጋት ደረጃ የሚስተናገዱትን የስጋት ሰነዶች መጨመር | 1 | በመቶኛ | 77 | 82 | 82 | 82 | 82 | 82 |
| 2.1.5 | የተቀረጹና የተሻሻሉ የህግና የአሰራር ስርዓቶች | 1 | በቁጥር | 14 | 17 | | 5 | 4 | 8 |
| **2.2** | **የታክስ መረጃ አስተዳደር ውጤታማነቱን ማረጋገጥ (ክብደት = 5)** | | | | | | | | |
| 2.2.1 | የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ በመጠቀም Z-Report የሚልኩ ድርጅቶች ምጣኔን ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 94.8 | 96 | 96 | 96 | 96 | 96 |
| 2.2.2 | የግዥና ሽያጭ የታክስ መረጃ ጥራት ቁጥጥር የተደረገባቸው መረጃዎች ብዛት | 1 | በመቶኛ | 94.8 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 2.2.3 | የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተደራሽነትን ማስፋት | 0.8 | በመቶኛ | 84 | 85 | 85 | 85 | 85 | 85 |
| 2.2.4 | የሽያጭ መረጃዎች የተሰበሰበባቸው ድርጅቶች ብዛት | 0.2 | በቁጥር | 6,327 | 6,655 | 4,974 | 5,289 | 5,657 | 6,655 |
| 2.2.5 | የግዥ መረጃዎች የተሰበሰበባቸው ድርጅቶች ብዛት | 0.5 | በቁጥር | 25,848 | 33,700 | 25,638 | 28,642 | 31,508 | 33,700 |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2015 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2016 በጀት ዓመት ግብ(መድረሻ) | በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 2.2.6 | የተሰበሰበ የገቢያ መረጃዎች ብዛት | 1 | በቁጥር | 2,848 | 3,902 | 691 | 1,018 | 1,104 | 1,089 |
| 2.2.7 | ደረሰኝ በሚቆርጡና በማይቆርጡ የተደረገ የቁጥጥር ስራ በድርጅቶች ብዛት | 0.5 | በቁጥር | 38,214 | 46,599 | 10,646 | 12,014 | 12,105 | 11,834 |
| **2.3** | **የኤሌክትሮኒክ ታክስ (E-Tax) አጠቃቀምን ማሻሻል (ክብደት = 4)** | | | | | | | | |
| 2.3.1 | በኤሌክትሮኒክ ታክስ የሚያሳውቁ የግብር ከፋዮች ድርሻን ማሳደግ | 2 | በመቶኛ | 93 | 98 | 94 | 95 | 97 | 98 |
| 2.3.2 | በኤሌክትሮኒክ የታክስ ክፍያ ሥርዓት የታቀፉ ግብር ከፋዮች ድርሻን ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 53 | 66 | 54 | 57 | 62 | 66 |
| 2.3.3 | በኤሌክትሮኒክ የታክስ ክፍያ ሥርዓት የተሰበሰበ የታክስ መጠን ከአጠቃላይ ታክስ ያለውን ድርሻ ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 28.66 | 35 | 29 | 31 | 32 | 35 |
| **2.4** | **የግብር ከፋዮች አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ማረጋገጥ (ክብደት = 10)** | | | | | | | | |
| 2.4.1 | በስታንዳርዱ በተቀመጠው ጊዜ መሰረት የተሰጠ የምዝገባ አገልግሎት ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 96 | 98 | 98 | 98 | 98 | 98 |
| 2.4.2 | ምላሽ ያገኙ የታክስ ተመላሽ ጥያቄዎች ብዛት | 0.5 | በመቶኛ | 96 | 97 | 97 | 97 | 97 | 97 |
| 2.4.3 | በስታንዳርዱ በተቀመጠው ጊዜ መሰረት የተሰጠ የተመላሽ አገልግሎት ማሳደግ | 0.5 | በመቶኛ | 98.74 | 99 | 99 | 99 | 99 | 99 |
| 2.4.4 | ምላሽ ያገኙ የታክስ የአገልግሎት ኦዲት ጥያቄዎች ብዛት | 1 | በመቶኛ | 98 | 99 | 99 | 99 | 99 | 99 |
| 2.4.5 | በስታንዳርዱ በተቀመጠው ጊዜ መሰረት የተሰጠ የአገልግሎት ኦዲት አገልግሎት ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 96 | 97 | 97 | 97 | 97 | 97 |
| 2.4.6 | ምላሽ ያገኙ የታክስ ክሊራንስ ጥያቄዎች ብዛት | 1 | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 2.4.7 | በስታንዳርዱ በተቀመጠው ጊዜ መሰረት የተሰጠ የክሊራንስ አገልግሎት ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 80 | 94 | 83 | 85 | 90 | 94 |
| 2.4.8 | ምላሽ ያገኙ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ ጥያቄዎች ብዛት | 1 | በመቶኛ | 97 | 98 | 98 | 98 | 98 | 98 |
| 2.4.9 | በስታንዳርዱ በተቀመጠው ጊዜ መሰረት የተሰጠ የታክስ ቅሬታ ውሳኔ አገልግሎት ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 98 | 99 | 99 | 99 | 99 | 99 |
| 2.4.10 | በስታንዳርዱ መሰረት የተስተናገዱ የጉምሩክ ታክስ መረጃና ማብራርያ ጥያቄዎች እድገት | 0.5 | በመቶኛ | 97 | 98 | 98 | 98 | 98 | 98 |
| 2.4.11 | በስታንዳርዱ መሰረት ቀርበው የተስተናገዱ አጠቃላይ ቅሬታ | 0.5 | በመቶኛ | 97 | 99 | 99 | 99 | 99 | 99 |
| 2.4.10 | በስታንዳርድ በተቀመጠው ጊዜ መሠረት የተሰጠ የጉምሩክ አገልግሎት ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 96.31 | 98 | 98 | 98 | 98 | 98 |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2015 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2016 በጀት ዓመት ግብ(መድረሻ) | በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| **2.5** | **የጉምሩክ ስነስርዓት አፈጻጸም ማሻሻል(ክብደት=5)** | | | | | | | | |
| 2.5.1 | የልዩ መብት የተፈቀደላቸው ተጠቃሚዎች ፕሮግራም ማስፋት | 2 | በቁጥር | 193 | 275 | | | 275 | |
| 2.5.2 | የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ አፈጻጸም ማስደግ | 1 | በመቶኛ | 88.5 | 90 | 90 | 90 | 90 | 90 |
| 2.5.3 | የጉምሩክ አቤቱታ ውሳኔ አፈጻጸም ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 96 | 98 | 98 | 98 | 98 | 98 |
| 2.5.4 | የዋጋና ታሪፍ ጥያቄ ምላሽ አፈጻጸም ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 99.33 | 99.50 | 99.50 | 99.50 | 99.50 | 99.50 |

## 4.5.3 የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነት ማረጋገጥ

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2015 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2016 በጀት ዓመት ግብ(መድረሻ) | በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| **3** | **የታክስና ቀረጥ ከፋዮች ህግ ተገዥነት ማሻሻል (ክብደት = 20)** | | | | | | | | |
| **3.1** | **የታክስ ማስታወቅና ክፍያ አቀራረብን ማጠናከር (ክብደት = 5)** | | | | | | | | |
| 3.1.1 | በሁሉም የታክስ ዓይነቶች በአማካይ ግብራቸውን በወቅቱ የሚያሳውቁ ግብር ከፋዮችን ማሳደግ | 1 | በቁጥር | 63,620 | 65,000 | 56,688 | 85,545 | 56,688 | 65,000 |
| 3.1.2 | በወቅቱ የንግድ ትርፍ ግብራቸውን የሚያሳውቁ ግብር ከፋዮችን ማሳደግ | 0.8 | በመቶኛ | 85 | 90 | 87 | 88 | 89 | 90 |
| 3.1.3 | በወቅቱ የተጨማሪ እሴት ታክሳቸውን የሚያሳውቁ ግብር ከፋዮችን ማሳደግ | 0.6 | በመቶኛ | 81 | 85 | 82 | 83 | 84 | 85 |
| 3.1.4 | በወቅቱ የኤክሳይዝ ታክሳቸውን የሚያሳውቁ ግብር ከፋዮችን ማሳደግ | 0.5 | በመቶኛ | 92 | 96 | 93 | 94 | 95 | 96 |
| 3.1.5 | በሁሉም የታክስ ዓይነቶች ግብራቸውን በወቅቱ አሳውቀው የሚከፍሉ ግብር ከፋዮችን ማሳደግ | 0.3 | በቁጥር | 17,648 | 22,000 | 17,100 | 32,320 | 17,100 | 22,000 |
| 3.1.6 | በወቅቱ አሳወቀው የንግድ ትርፍ ግብራቸውን የሚከፍሉ የግብር ከፋዮችን ምጣኔ ማሳደግ | 0.1 | በመቶኛ | 40.5 | 45 | 42 | 43 | 44 | 45 |
| 3.1.7 | በወቅቱ አሳውቀው የተ/እ/ታክሳቸውን የሚከፍሉ ታክስ ከፋዮችን ምጣኔ ማሳደግ | 0.2 | በመቶኛ | 39.3 | 43 | 40 | 41 | 42 | 43 |
| 3.1.8 | በወቅቱ አሳውቀው የኤክሳይዝ ታክስቸውን የሚከፍሉ ታክስ ከፋዮችን ምጣኔ ማሳደግ | 0.2 | በመቶኛ | 66 | 72 | 67 | 68 | 70 | 72 |
| 3.1.9 | ከቀረቡ የታክስ ማስታወቂያዎች ስሌት የተሰራላቸውን ምጣኔን ማሳደግ | 0.5 | በመቶኛ | 99.98 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2015 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2016 በጀት ዓመት ግብ(መድረሻ) | በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 3.1.10 | በስሌት በልዩነት የተገኘ የገንዘብ መጠን | 0.5 | በቢሊዮን ብር | 31.1 | 30 | 6.57 | 8.03 | 7.17 | 8.23 |
| 3.1.11 | በአገልግሎት ኦዲት በልዩነት የተወሰነ የፍሬ ግብር መጠን(በቢሊዮን) | 0.3 | በብር | 2.23 | 3 | 0.75 | 0.75 | 0.75 | 0.75 |
| **3.2** | **የታክስ ከፋዮች ትምህርት፣ የኢንተለጀንስ ክትትል እና የኦዲት ሥራዎችን ማጠናከር (ክብደት = 10)** | | | | | | | | |
| 3.2.1 | ወደ ታክስ መረቡ የገቡ አዳዲስ ግብር ከፋዮች | 0.2 | በቁጥር | 56,432 | 67,309 | 59,151 | 61,870 | 64,590 | 67,309 |
| 3.2.2 | በታክስ ህጎች ላይ የሞጁላር ትምህርት እና ስልጠና ያገኙ ግብር ከፋዮች ብዛት | 1 | በቁጥር | 13,704 | 18,774 | 3,895 | 4748 | 5,178 | 4,953 |
| 3.2.3 | በታክስ ህጎች ላይ ፍላጎትንና ወቅታዊ ሁኔታን ያገናዘበ ለግብር ከፋዮች የተሰጠ የአንድ ጊዜ ስልጠና ብዛት | 0.3 | በቁጥር | 13,237 | 18,128 | 3,314 | 5,076 | 4,994 | 4,744 |
| 3.2.4 | የታክስና የጉምሩክ ትምህርት ሽፋን ማሳደግ (3ቱንም ክፍሎች አጠናቀው ለ90 ሰዓታት ስልጥነው የተመረቁ ወይም ለምረቃ ዝግጁ የሆኑ ግብር ከፋዮች ብዛት | 0.2 | በቁጥር | 5,171 | 9,171 | | | | 9,171 |
| 3.2.5 | በሁሉም የታክስ ዓይነቶች በፈቃደኝነት የተሰበሰበ ግብር ከጠቅላላ የግብር ገቢ ድርሻ ማሳደግ | 5 | በመቶኛ | 80 | 87 | 84 | 90 | 84 | 87 |
| 3.2.6 | የህግ ተገዥነት ስትራቴጂ ትንታኔዎች/ጥናቶች አፈጻጸም ውጤማነት | 0.2 | ኢንዴክስ | 76 | 83 | | 80 | | 83 |
| 3.2.7 | የታክስ ኦዲትና የምርመራ ኦዲት ሽፋን | 0.3 | በመቶኛ | 30 | 31 | | | | 31 |
| 3.2.8 | የታክስ ኦዲት የተረገ ግብር ከፋዮች ብዛት | 0.3 | በቁጥር | 7,058 | 8,154 | 1,668 | 2,213 | 2,189 | 2084 |
| 3.2.9 | በታክስ ኦዲት በልዩነት የተሰወነ የፍሬ ግብር መጠን በቢሊዮን | 0.3 | ብር | 19.3 | 16.57 | 3.36 | 4.65 | 4.43 | 4.13 |
| 3.2.10 | የኦዲት ጥራት የማረጋገጥ ስራ የተሰራባቸው ኦዲት ብዛት | 0.1 | በቁጥር | 283 | 353 | 73 | 123 | 53 | 104 |
| 3.3.11 | የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ሽፋንን ማስፋት | 0.5 | በቁጥር | 2320 | 2772 | 680 | 730 | 696 | 666 |
| 3.2.12 | ኢንቨስትጌሽን ኦዲት የተደረጉ ግብር ከፋዮች ብዛት | 0.5 | በቁጥር | 544 | 690 | 122 | 184 | 180 | 204 |
| 3.2.13 | ኢንቨስትጌሽን ኦዲት በልዩነት የተወሰነ የገንዘብ መጠን በሚሊዮን | 0.2 | ብር | 5,405 | 5,740 | 995.42 | 1,577.75 | 1,481.04 | 1,685.79 |
| 3.2.14 | የቫት ደረሰኝ በማይቆርጡ ድርጅቶች ላይ የተደረገ ኦፕሬሽን ብዛት | 0.4 | በቁጥር | 568 | 820 | 143 | 237 | 235 | 205 |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2015 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2016 በጀት ዓመት ግብ(መድረሻ) | በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 3.2.15 | የቫት ደረሰኝ የማይቆርጡ ድርጅቶች ላይ የተወሰደ ኦፕሬሽን ውጤታማነት | 0.3 | በመቶኛ | 94 | 97 | 97 | 97 | 97 | 97 |
| 3.2.16 | ለምርመራ ኦዲት የተላለፉ የኢንተለጀንስ ጥናት ፋይል ብዛት | 0.1 | በቁጥር | 529 | 810 | 169 | 208 | 218 | 215 |
| 3.2.17 | በሃሰተኛ ደረሰኝ ምንጭ በመሆን የተሰማሩ ግለሰቦችና ደርጅቶች ላይ የተደረገ ኦፕሬሽን ብዛት | 0.1 | በቁጥር | 10 | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 3.3 | የንግድ ማጭበርበር እና ኮንትሮባንድ መከላከል አፈጻጸምን ማሻሻል (ክብደት = 5) | | | | | | | | |
| 3.3.1 | የኢንተለጀንስና የድንገተኛ ፍተሻ ውጤታማነት ማሳደግ | 2 | በመቶኛ | 63.10 | 73.05 | 73.05 | 73.05 | 73.05 | 73.05 |
| 3.2.2 | በኮንትሮባንድ ወንጀል የተሳተፉ ኮንትሮባንድስቶችን በቁጥጥር ስር የማዋል ምጣኔ | 3 | በመቶኛ | 90.35 | 93 | 93 | 93 | 93 | 93 |

## 4.5.4 የዘላቂ የመንግስት ገቢ ዕድገት ማረጋገጥ

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2015 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2016 በጀት ዓመት ግብ(መድረሻ) | በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 4 | ዘላቂ የመንግስት ገቢ ዕድገት ማረጋገጥ (ክብደት = 40) | | | | | | | | |
| 4.1 | ከቀረጥና ታክስ የሚሰበሰብ ገቢን ማሳደግ (ክብደት = 35) | | | | | | | | |
| 4.1.1 | የሀገር ውስጥ ታክስና የጉምሩክ ጥቅል (Gross) የፌደራል ገቢ ዕቅድ | 7 | በቢሊዮን ብር | 442.03 | 529.33 | 110.32 | 160.65 | 120.39 | 137.97 |
| 4.1.2 | የሀገር ውስጥ ታክስና የጉምሩክ የተጣራ (Net) የፌደራል ገቢ ዕቅድ | 6 | በቢሊዮን ብር | 348.59 | 446.38 | 94.91 | 130.22 | 99.23 | 122.02 |
| 4.1.3 | የሀገር ውስጥ ታክስ ጥቅል (Gross) የፌደራል ገቢ ዕቅድ | 4 | በቢሊዮን ብር | 264.34 | 319.33 | 60.38 | 107.08 | 66.19 | 85.68 |
| 4.1.4 | የጉምሩክ ጥቅል (Gross) የፌደራል ገቢ ዕቅድ | 3 | በቢሊዮን ብር | 177.68 | 210.00 | 49.94 | 53.58 | 54.19 | 52.29 |
| 4.1.5 | የጉምሩክ ታክስ ከሆኑ ገቢዎች የሚሰበሰብ ገቢ ማሳደግ | 2.5 | በቢሊዮን ብር | 168.55 | 200.49 | 47.95 | 51.06 | 51.67 | 49.81 |
| 4.1.6 | የጉምሩክ ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች የሚሰበሰብ ገቢ ማሳደግ | 0.5 | በቢሊዮን ብር | 9.14 | 9.51 | 1.99 | 2.52 | 2.53 | 2.47 |
| 4.1.7 | የሀገር ውስጥ ጥቅል ገቢ ከአጠቃላይ ገቢ | 2 | በመቶኛ | 60 | 60 | 55 | 67 | 55 | 62 |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2015 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2016 በጀት ዓመት ግብ(መድረሻ) | በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| | ያለው ድርሻ | | | | | | | | |
| 4.1.8 | የጉምሩክ ጥቅል ገቢ ከአጠቃላይ ገቢ ያለው ድርሻ | 1 | በመቶኛ | 40 | 40 | 45 | 33 | 45 | 38 |
| 4.1.9 | የሀገር ውስጥ ከቀጥታ ታክሶች የሚሰበሰብ ገቢ ማሳደግ | 2 | በቢሊዮን ብር | 137.56 | 154.57 | 21.16 | 65.59 | 23.80 | 44.02 |
| 4.1.10 | የሀገር ውስጥ ቀጥታ ካልሆኑ ታክሶች የሚሰበሰብ ገቢ ማሳደግ | 1.5 | በቢሊዮን ብር | 125.96 | 163.55 | 38.98 | 41.13 | 42.13 | 41.31 |
| 4.1.11 | የሀገር ውስጥ ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች የሚሰበሰብ ገቢ ማሳደግ | 0.5 | በቢሊዮን ብር | 0.82 | 1.21 | 248.52 | 361.93 | 264.76 | 336.20 |
| 4.1.12 | ከተሰበሰበው ገቢ የክልሎችን ድርሻ በወቅቱ ማስተላለፍ | 5 | በቢሊዮን ብር | 58.7 | 65.05 | 11.6 | 18.00 | 16.00 | 17.00 |
| **4.2** | **የታክስ ዕዳ አሰባሰብ አቅም ማጎልበት (ክብደት = 5)** | | | | | | | | |
| 4.2.1 | ከቆየ ዕዳ የሚሰበሰብ የዕዳ መጠንን ማሳደግ | 1 | በቢሊዮን ብር | 16.18 | 4.54 | 0.77 | 1.27 | 1.20 | 1.41 |
| 4.2.2 | ከአዲስ (60 ቀን) ካልሞላው ዕዳ የሚሰበሰብ የዕዳ መጠንን ማሳደግ | 4 | በቢሊዮን ብር | 37.67 | 36.98 | 8.67 | 9.59 | 9.30 | 9.34 |

## 5 ስጋቶችና የመፍትሄ ሀሳቦች

የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ በሚፈጸምበት ሂደት የተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ስጋቶች ሊያጋጥሙ እንደሚችሉ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ከተለዩት ስጋቶች ውስጥ ዓለማቀፋዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ፣ የህቡእ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ፣ የታክስ ህግ ተገዥነት ባህል ማነስ፣ ዝቅተኛ ቅንጅታዊ አሰራር፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት እና የሰው ሀይል ፍልሰት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህን ስጋቶችና ስጋቶቹን ለመቀነስ ሊወሰዱ የሚገባቸው የመፍትሄ አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ሰንጠረዥ 9: ስጋቶችና የመፍትሄ ሀሳቦች

| ስጋቶች | መግለጫ | የመፍትሄ እርምጃዎች |
|---|---|---|
| **የዓለም ፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ተለዋዋጭነት** | • የዓለም የፖለቲካ ሚዛን እና የኢኮኖሚ ሁኔታ መለዋወጥ (ለምሳሌ፡ የምዕራባውያን እና ምስራቃውያን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፉክክር፣ የዩክሬን ጦርነት) በሀገራችን ማክሮ ኢኮኖሚ እድገት ላይ የሚንጸባረቅ በመሆኑ በገቢ አሰባሰቡ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል መሆኑ፣ | • በዓለም ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተለዋዋጭነት ምክንያት በታክስ አስተዳደሩ ላይ የሚከሰቱ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፣ |
| **የህቡዕ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ** | • በህጋዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ሳይታቀፉ በታክስ ማጭበርበር፣ ኮንትሮባንድ፣ ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር፣ ህገወጥ ደረሰኝ እና በመሳሰሉት ተግባራት ላይ በመሳተፍ በመንግስት ገቢ፣ በህጋዊ ንግድ እና በሀገር ደህንነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ህቡዕ እንቅስቃሴዎች መኖራቸው ወደፊትም ችግሩ ሊቀጥል የሚችል መሆኑ፣ | • ህቡዕ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ለመከላከል የሚያስችል ስትራቴጂ ነድፎ መተግበር፣<br>• በጥሬ ገንዘብ ላይ የተመሰረተውን የንግድ ግብይት በባንክ ስርዓትን እንዲተካ ማድረግ፣<br>• በዋና ዋና የህቡዕ ኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ላይ የማያዳግም ህጋዊ እርምጃዎችን መውሰድ፣ |
| **የህግ ተገዥነት ባህል አነስተኛ መሆኑ፣** | • ከግብይት ዋጋ በታችና በላይ ማቅረብ፣ ዋጋ ማሸጋገር፣ በመንግስት የተሰጡ የቀረጥና ታክስ ማበረታቻዎችን አላግባብ መጠቀም፣ ያልተገባ ተመላሽ መጠየቅ፣ ገቢን በወቅቱ አለማሳወቅና አለመክፈል፣ አላግባብ ባዶ፣ ኪሳራና ተመላሽ ማሳወቅ ሊያጋጥም የሚችል መሆኑ፣ | • የህግ ተገዥነት ማሻሻያ ስትራቴጂ (Compliance Improvement Strategy) ቀርጾ መተግበር፣<br>• የተቋሙን የህግ ማስከበር አቅም ማጠናከር፣<br>• ህገወጥነትን በቅንጅት መከላከል፣ |
| **የቅንጅታዊ አሰራር ጉድለት** | • ከሀገር ውስጥና ከውጪ አጋር አካላት ጋር የሚደረግ ቅንጅታዊ አሰራር በሚጠበቀውና ውጠየት ሊያስገኝ በሚችል ደረጃ ተግባራዊ | • በህግ ማዕቀፍ የሚደገፍና ተጠያቂነትን የሚያከትል ጠንካራ የቅንጅት ስትራቴጂ ቀርጾ |

| ስጋቶች | መግለጫ | የመፍትሄ እርምጃዎች |
|---|---|---|
| | ሊደረግ አለመቻሉ፣ | መተግበር፣ |
| የውጭ ምንዛሪ እጥረት | • ሀገሪቱ ከውጭ ለምታስመጣቸው ዕቃዎች ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ሲያጋጥማት መቆየቱ፣ ለወደፊቱም እጥረቱ ሊቀጥል የሚችልበት ዕድል ሰፊ በመሆኑ በቀረጥና ታክስ አሰባሰብ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል መሆኑ፣ | • ኤክስፖርትን መደገፍ፣<br>• ካለ ውጭ ምንዛሬ ፈቃድ ዕቃዎች ወደ ሀገር ሊገቡ የሚችሉበትን አማራጭ ሥርዓት መዘርጋት፣<br>• የፋይናንስ ገበያው ለውጭ ባንኮች ክፍት ማድረግ፣ |
| የሰው ሀይል ፍልሰት | • የዋጋ ግሽበት እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የተሻለ ገቢ ከመፈለግ ጋር የተያያዘ ልምድና ሙያዊ ብቃት ያላቸው ሰራተኞች ፍልሰት መኖሩ፣ | • የኑሮ ደረጃውን ከግንዛቤ ያስገባ የሰራተኛ ማቆያ ሥርዓት (Retention Strategy) መዘርጋት፣ |

# 6 የዓመቱን ዕቅድ ለማሳካት የሚተገበሩ የዕቅድ ማስፈጸሚያዎች

## 6.1 ዕቅዱን ለማሳካት በልዩ ትኩረት የሚሰሩ ስራዎች

የተቋሙን የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ለማሳካት ትኩረት የሚደረግባቸው ዋና ዋና ተግባራት እንደሚከተለው ተለይተዋል፡፡

### ➲ ማስታወቅ እና ክፍያ ላይ የተጠናከረ ክትትል ማድረግ

ከማስታወቅ እና ከክፍያ አንጻር አራት ዋና ዋና ተግባራት ያሉ ሲሆን እነዚህም ያላሳወቁ ግብር ከፋዮችን መከታተል፣ ያሳወቁ ግብር ከፋዮች ላይ ማጣራት እና ክትትል ማካሄድ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ዊዝሆልዲንግ ኤጀንቶች ላይ ክትትል ማድረግ እና የግብር ዕፎይታ መብት አጠቃቀምን አግባብነት መከታተል ናቸው፡፡ እነዚህን በውጤታማነት ከመስራት አንጻር በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ወቅታዊ እና የጠራ የግብር ከፋይ መረጃ መያዝ ከፍተኛ ጥቅም አለው፡፡ በማስታወቅ እና በክፍያ ዙሪያ የሚሰሩ ስራዎች የበጀት ዓመቱን ገቢ እንዲሳካ ከማገዝ በተጨማሪ በዘላቂነት የህግ ተገዥነት ከማዳበር አኳያም ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡

የማስታወቅ እና ክፍያ ክትትል ስራን ውጤታማ ለማድረግ በመጀመሪያ ደረጃ ከግብር ከፋይ መረጃዎች በመነሳት በየወቅቱ እና በየግብር ዓይነቱ ማስታወቅ ያለባቸውን ግብር ከፋዮች (ነባር እና አዲስን ጨምሮ) መለየት እና ከነዚህ ውስጥ ከፍተኛ መጠን ያለው ገቢ (በየታክስ ዓይነቱ ከ70-80 በመቶ ገቢ የሚያስገኙ ግብር ከፋዮችን) በመለየት እንዲያሳውቁ እና ክፍያ እንዲፈጽሙ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ግብር ከፋዮች ግብራቸውን በሚያሳውቁበት ወቅት መረጃ ወደ ሲስተም ማስገባት እና የታክስ ስሌት በወቅቱ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር ወደ ሲስተም ያልገቡ እና ስሌት ያልተሰራላቸውን ማስታወቂያዎች እንዳይኖሩ ማድረግ ይገባል፡፡ ግብራቸውን ካሳወቁ ግብር ከፋዮች ውስጥ ባዶ፣ ኪሳራ እና አነስተኛ ግብር ያሳወቁ ግብር ከፋዮችን መከታተልም አስፈላጊ ነው፡፡ አነስተኛ ግብር ያሳወቁ የሚባሉት ግብር ከፋዮች ከዘርፋቸው አማካይ አንጻር በጣም ዝቅተኛ የሆነ መጠን ያሳወቁትን ነው፡፡ ከማስታወቅ ጋር በተያያዘ የተጨማሪ እሴት ታክስ ዊዝሆልዲንግ ኤጀንቶች በወቅቱ ማስታወቃቸውን እና ክፍያ መፈጸማቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተለይም ከፍተኛ መጠን ያለው ዊዝሆልዲንግ የሚሰበስቡ ተቋማት ላይ አተኩረን መስራት ያስፈልጋል፡፡

ያሳወቁ ግብር ከፋዮች ላይ ከሚደረገው የማጣራት እና ክትትል ስራ በተጨማሪ ያላሳወቁ ግብር ከፋዮችን በመከታተል እና ግብራቸውን አሳውቀው እንዲከፍሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር በዋና ዋና የታክስ ዓይነቶች (ንግድ ትርፍ፣ ተ.እ.ታ፣ ኤክሳይስ ታክስ እና የመሳሰሉት)

ሳያሳውቁ የቀሩትን በመለየት እና ከፍተኛ ግብር ሊገኝባቸው የሚችሉ ዘርፎች እና ተቋማትን ቅድሚያ በመስጠት የክትትል ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡

በመጨረሻም መንግስት የሰጠውን የግብር ዕፎይታ መብት አጠቃቀም አግባብነት መከታተል እና መብታቸውን አላግባብ የሚጠቀሙት ላይ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የግብር ዕፎይታ መረጃ አደራጅቶ መያዝ፣ መብታቸው ያለቀውን ለይቶ ክፍያ መፈጸም መጀመራቸውን ማረጋገጥ እና መብታቸውን አላግባብ የሚጠቀሙት ላይ እርምጃ መውሰድ ዋና ዋና ስራዎች ናቸው፡፡

### ➲ የታክስ ኦዲት ስራን አጠናክሮ መቀጠል

የኦዲት ስራ በዋናነት የግብር ከፋዩን የህግ ተገዥነት ደረጃ ለማሳደግ ቁልፍ ሚና ከሚጫወቱ ስራዎች አንዱ ሲሆን ከዕዳ ለሚገኘው ገቢም ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ ውጤታማ የኦዲት ስራ ከማከናወን አንጻር ሶስት ቁልፍ ተግባራት ላይ ማተኮር ይመከራል፡፡ እነዚህም የኦዲት አፈጻጸምን ማሻሻል፣ የስነምግባር ችግሮችን መቅረፍ እና የኦዲት ጥራትን ማረጋገጥ ናቸው፡፡

የኦዲት አፈጻጸምን ከማሻሻል አኳያ ትኩረት የሚሰጣቸው ስራዎች ውስጥ ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ያላቸውን ግብር ከፋዮች አጠቃላይ ኦዲት ማድረግ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ላላቸው የዴስክ እና ውስን ኦዲት ማካሄድ፣ የተ.እ. ታ፣ ኤክሳይስ ታክስ እና የንግድ ትርፍ ግብር የህግ ተገዥነት ክፍተት ባለባቸው ዘርፎች ላይ የውስን ኦዲት ማድረግ፣ ከግብር ከፋዮች ጋር የኦዲት ማጠቃለያ ኮንፈረንሶች ፍጥነት እና ውጤታማነት ማሻሻል እና የተገኙ ተሞክሮዎችን ቀምሮ ጥቅም ላይ ማዋል እና በኦዲት ውስጥ ያሉ ቀዳዳዎች (Audit Leakages) ለመድፈን የቁጥጥር እና ክትትል ስራዎችን ማጠናከር፣ ግድፈት በሚታይባቸው ኦዲተሮች እና ግብር ከፋዮች ላይ የዕርምት ዕርምጃ በመውሰድ በከፍተኛ ሁኔታ የኦዲት ጥራትን በማረጋገጥ ከቅሬታ የጸዳ ውሳኔ መወሰን ይጠበቃል፡፡

### ➲ የቅሬታ እና የግብር ይግባኝ አፈጻጸምን ማሻሻል

የግብር ከፋዮችን ቅሬታ በአፋጣኝ እና በፍትሀዊነት ምላሽ መስጠት አገልግሎት አሰጣጡን ከማሻሻሉም በተጨማሪ ለገቢ ስኬት አስተዋጽዎው የጎላ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገቡ ስራዎች መካከል በቅሬታ ላይ ያሉ ፋይሎችን በመለየት በግምታዊ ዋጋ 80 በመቶ ያህል የሚሸፍኑ ፋይሎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት፣ የቅሬታ ውሳኔዎችን በመተንተን ለኦዲት እና ትምህርት ክፍሎች ግብረመልስ መስጠት እና የቅሬታ ውሳኔዎችን ዝርዝር መረጃ በመያዝ ያሉበትን ደረጃ ለአመራሩ እና ለሚመለከታቸው ክፍሎች በየጊዜው ማሳወቅ ይገኙበታል፡፡

### ➲ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አጠቃቀም፣ ክትትል እና ቁጥጥርን ማጠናከር

በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አጠቃቀም ላይ በሚደረገው ክትትል እና ቁጥጥር ከተጨማሪ እሴት ታክስ የሚገኘው ገቢ ላይ ቁልፍ አስተዋጽዎ አለው፡፡ በመሆኑም ጠንካራ የክትትል እና ቁጥጥር ስራ በየደረጃው ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡ ይህን ከማሳካት አንጻርም ወቅታዊ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መረጃ ማደራጀት እና በስራ ላይ ያሉ እና የሌሉ ማሽኖችን መለየት፣ መረጃ የሚልኩ እና የማይልኩ ማሽኖችን መለየት እና አስፈላጊውን ትንተና እና ክትትል ማድረግ፣ በተመረጡ ግብር ከፋዮች ተቋማት በመገኘት የመሳሪያውን የአጠቃቀም ሁኔታ እና አዲስ ለሚያስገቡ ደንበኞች ሂደቱን በ3 ቀናት እንዲያጠናቅቁ ማድረግ በቁልፍ ስራነት ተወስዶ ሊሰራበት ይገባል፡፡

### ➡ የታክስ ዕዳ አሰባሰብን ማሻሻል

በሀገር ውስጥ የዕዳ አሰባሰብ ስራ በ2015 በጀት ዓመት ለ53.85 ቢሊዮን ብር በላይ ተሰብስቦ ከበጀት ዓመቱ በሀገር ውስጥ ከተገኘው ብር 264.35 ቢሊዮን 20.37 በመቶ ያህሉን ሸፍኗል፡፡ በ2016 በጀት ዓመት የገቢ ዕቅድን ከማሳካት አንጻር የዕዳ አሰባሰብ ስራ ቁልፍ ድርሻ አለው፡፡ የዕዳ ዕቅዱን ከማሳካት አንጻር የውሳኔ ማስታወቂያ የወጣባቸው ግብር ከፋዮች በ30 ቀናት ውስጥ እንዲከፍሉ ጥብቅ ክትትል ማድረግ፣ በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎች እና በተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች ክትትል ሊደረግባቸው የሚገቡ የዕዳ ፋይሎችን መለየት፣ በክፍያ ስምምነት ውስጥ ያሉት ግብር ከፋዮች በወቅቱ የሚጠበቅባቸውን ክፍያ እንዲከፍሉ ክትትል ማድረግ እና ያልከፈሉት ላይ በታክስ ህጉ መሠረት እርምጃ መውሰድ፣ የተ.እ.ታ ዊዝሆልዲንግ ኤጀንቶች ዕዳ ውስጥ ከፍተኛ መጠን (80 በመቶ) የሚይዙትን በመለየት ጥብቅ ክትትል ማድረግ፣ በቅድመ እግድ ላይ ያሉ ግብር ከፋዮች በ31ኛው ቀን የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው ማድረግ እና የተጠናከረ ክትትል ማድረግ (በስልክ፣ በአጭር የስልክ መልዕክት እና በአካል)፣ ለእግድ የሚያስፈልጉ የግብር ከፋይ ዝርዝር መረጃ (አድራሻ፣ ተንቀሳቃሽ እና ቋሚ ንብረት፣ ወዘተ) ማደራጀት ላይ አተኩሮ መስራት ያስፈልጋል፡፡

### ➡ ሌሎች ተጨማሪ ተግባራት

ከላይ የተጠቀሱትን ስራዎች ከመስራት ባሻገር የኢ-ማሳወቅ እና ኢ-ክፍያ ማስፋፋት፣ የሰራተኛውን እና ግብር ከፋዩን የስራ ቦታ ደህንነት ማረጋገጥ፣ የሰራተኛ ዕውቅናና ማበረታቻ ስራ ማካሄድ፣ ሀገራዊ የታክስ ንቅናቄን በስፋት መተግበር፣ ግብር ከፋዮችን ማስተማር፣ የመረጃ ጥራትን ማረጋገጥ እና የፌደራል ኦዲት ግኝት ማስተካከያዎችን በፍጥነት ማካሄድ ላይ በማተኮር መስራት ይጠበቃል፡፡

# 7 የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

## 7.1 የሪፖርት አቀራረብና የግንኙነት አግባብ

የተቋሙ የክትትል እና ግምገማ ስርዓት በሶስት ዋና ዋና ስራዎች አማካኝነት የሚተገበር ይሆናል፡፡ እነዚህም የአፈጻጸም ሪፖርት ማከናወን፣ የክትትል እና ግምገማ ስራዎች እና የግብረ መልስ ስርዓት ናቸው፡፡ ስለሆነም የአፈጻጸም ሪፖርቶችን ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት፣ ለፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር እንዲሁም ገቢ ነክ ሪፖርቶችን ለገንዘብ ሚኒስቴር ይልካል፡፡ በሌላ በኩል የተቋሙን ከፍተኛ አመራሮች ጨምሮ እና የተለያዩ ውስጣዊ አደረጃጀቶች የተቋሙን ሪፖርት ለስራቸው በግብዓትነት የሚጠቀሙት ይሆናል፡፡ ይህንን ታሳቢ በማድረግ የሚዘጋጁት ሪፖርቶች ወቅታዊ፣ ጥራቱን የጠበቀ እና የተሟላ መረጃ የያዙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህም እንዲረዳ የሪፖርት እና መረጃ አቀራርብ ስርዓት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- **የየቀኑን የገቢ አሰባሰብ ሪፖርት:** ቅርንጫፎች እና ጉምሩክ ኮሚሽን (በየቅርንጫፉ) በየቀኑ የሰበሰቡትን ጠቅላላ ገቢ ለስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዲይሬክቶሬት በቀጣዩ ቀን እስከ ጠዋቱ ስድስት ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ያሳውቃሉ፡፡ ዳይሬክቶሬቱም የተቋሙን ዕለታዊ የገቢ አፈጻጸም ሪፖርት በማጠቃለል ለተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች እና ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች በኢሜል እና አውትሉክ አድራሻቸው እስከ ቀኑ ስምንት ሰዓት ድረስ እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡
- **ወርሃዊ የገቢ አሰባሰብ ሪፖርት:** የሀገር ውስጥ ታክስ ቅርንጫፎች እና የጉምሩክ ኮሚሽን ወርሃዊ የገቢ አሰባሰብ ሪፖርት ወሩ ባለቀ በማግስቱ ያደረ ሂሳባቸውን አጠቃለው በአንድ ቀን ውስጥ ጥቅል ወይም በገቢ ዓይነት ያልተከፋፈለ አፈጻጸማቸውን ለስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ያሳውቃሉ፡፡ በተመሳሳይ በገቢ ዓይነት የተዘረዘረ ሪፖርታቸውን በአራተኛው ቀን ለስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት መላክ ይኖርባቸዋል፡፡ የስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬትም በገቢ ዓይነት የተጠናቀረ የገቢ ሪፖርት በአምስተኛው ቀን ለተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች እና ለገንዘብ ሚኒስቴር የሚልክ ይሆናል፡፡
- **የፊዚካል ስራዎች አፈጻጸምን በተመለከተ:** ከገቢ ሪፖርት ውጪ ያሉ እና በተቋሙ ዓመታዊ ዕቅዱ ላይ የተቀመጡ ግቦች አፈጻጸም ሪፖርት ከስራ ዘርፎች፣ ከቅርንጫፎች እና ከጉምሩክ ኮሚሽን ወሩ ባለቀ 7 ቀናት ውስጥ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ የስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የቀረቡለትን ሪፖርቶች በቀጣይ 3 ቀናት ውስጥ በማጠቃለል ለግብረ መልስ ለስራ ክፍሎች በ10ኛው ቀን ይልካል፡፡ የስራ ዘርፎች፣ ቅርንጫፎች እና ተጠሪ ተቋማት ያላቸውን አስተያየት በ2 ቀን ውስጥ እንዲሰጡ ከተደረገ በኋላ የተሰጠውን ግብረ መልስ በማካተት የመጨረሻው ሪፖርት ወሩ ባለቀ በ15 ቀናት ውስጥ ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት ይቀርባል፡፡

በተቋም ደረጃ በየሩብ ዓመቱ የሚዘጋጁ ሪፖርቶች ከተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች በተጨማሪ ለውጭ አካላት የሚላኩ ይሆናል፡፡ ለውጭ አካላት በየሩብ ዓመቱ የሚዘጋጁት ሪፖርቶች ወር በገባ በ15 ቀናት ውስጥ የሚዘጋጁ ሲሆን ሪፖርቶቹም የተቋሙን የአመራር ግብዓት በማካተት የሚዘጋጁ ናቸው፡፡

## 7.2 የክትትልና ድጋፍ ስራዎች

ሁሉም አካላት በተዋረድ በተዘጋጀው ዕቅድ መሠረት አፈጻጸማቸውን መከታተልና መገምገም የሚያስፈልጋቸው ሲሆን ክትትልና ግምገማው በስልክ ግንኙነት፣ በሪፖርት፣ በመስክ የሥራ ጉብኝት እና የጋራ የምክክር መድረክ በማዘጋጀት ይሆናል፡፡ በዋናነትም በየዳይሬክቶሬቶች እና በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የክትትልና የመስክ የሱፐርቪዥን ድጋፍ ሲደረግ በዕቅድ ዘመኑ የተቀመጡትን ዓላማዎች አፈጻጸም ቀጣይነት ለመከታተል ከምንጠቀምበት መንገድ አንዱ የክትትልና የሱፐርቪዥን ድጋፍ በመሆኑ በየሳምንቱ አርብ ዳይሬክቶሬቶች ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ጋር እንዲሁም በየሳምንቱ ቅዳሜ በዙም የቴክኖሎጂ ስርዓት በየዘርፉ ግምገማና ድጋፎች ያደርጋሉ፡፡

በመሆኑም በዕቅድ የተያዙ ዓላማዎችን አፈጻጸም በተመለከተ በየዳይሬክቶሬቶች እና በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በመስክ በአካል ተገኝቶ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በመስክ ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬቶች እና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን በመጎብኘት ስለአፈጻጸማቸው አግባብነት ካለቸው አመራሮችና ፈጻሚዎች ጋር ውይይት በማካሄድ እንዲሁም በአፈጻጸም ወቅት ላጋጠሙ ችግሮች በጋራ መፍትሄ በማስቀመጥ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

**ወርሃዊ የአፈጻጸም ግምገማ:** በተቋም ደረጃ በሚዘጋጀው ወርሃዊ ሪፖርት ላይ በመመስረት የአፈጻጸም ግምገማ የሚደረግ ሲሆን የአፈጻጸም ግምገማው በዋናነት በገቢ እና ከገቢ ጋር ተያያዥነት ባላቸው የፊዚካል ስራዎች አፈጻጸም ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡ ወርሃዊ የአፈጻጸም ግምገማው በዘርፍ ደረጃ የሚካሄድ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በአዲስ አበባ የሚገኙ ቅርንጫፎችን በማሳተፍ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

**የሩብ ዓመት የአፈጻጸም ግምገማ:** የሩብ ዓመት የአፈጻጸም ግምገማ በዓመት ውስጥ ባሉት 4 ሩብ ዓመቶች (የመጀመሪያው ሩብ ዓመት፣ የ6 ወራት፣ የ9 ወራት እና ዓመታዊ) ያለውን የተቋሙ ዝርዝር አፈጻጸም ግምገማ የሚዳሰስበት ነው፡፡ በዚህ አፈጻጸም ግምገማ ላይ ሁሉም የስራ ዘርፎች፣ ቅርንጫፎች፣ የስራ ክፍሎች እና ጉምሩክ ኮሚሽን አፈጻጸማቸውን ገምግመው የሚገኙ ይሆናል፡፡ የአፈጻጸም ግምገማው ከ2-3 ቀናት የሚወስድ እና በየስራ ዘርፉ ዝርዝር የአፈጻጸም ግምገማ የሚካሄድበት እና ለቀጣይ ስራ አቅጣጫ የሚቀመጥበት ነው፡፡

**የአፈጻጸም ደረጃ ማስቀመጥ:** የተዘጋጀውን ዓመታዊ ዕቅድ መሠረት በማድረግ ለስራ ዘርፎች፣ ቅርንጫፎች እና የስራ ክፍሎች በየሩብ ዓመቱ እና በዓመቱ ማጠቃለያ ላይ እንደየአፈጻጸማቸው የአፈጻጸም ደረጃ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

## 7.3 የግብረ- መልስ ሥርዓት

የግብረ መልስ ስርዓቱ በሁለት ደረጃዎች የሚፈጸም ይሆናል:: የመጀመሪያ ደረጃ በተቋሙ ተዘጋጅተው በተላኩ ዕቅዶች እና ሪፖርቶች ላይ ከውጫዊ አካላት በሚሰጡ ግብረ መልሶች ላይ በየደረጃው ማስተካከያ ወይም ማብራሪያ ማድረግ የሚጠበቅ ሲሆን በግብረ መልሱ መሠረት የተሻሻለ ሪፖርት ተዘጋጅቶ እንደገና ይላካል::

በሁለተኛ ደረጃ በዋናነት ተቋሙ የአፈጻጸም ክፍተቶችን በየጊዜው እየለየ ለዘርፎች፣ ቅርንጫፎች፣ የስራ ክፍሎች እና ለጉምሩክ ኮሚሽን ግብረ መልስ መሰጠት ይኖርበታል:: በሚሰጠው ግብረ መልስ መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ስለመወሰዱ ክትትል እና ድጋፍ የሚደረግ ይሆናል:: በተዘጋጀው የአፈጻጸም ሪፖርት ላይ በአስፈጻሚ አካላት፣ በተገልጋዮችና ከባለድርሻ አካላት በሚሰጡ አስተያየቶችና ከሚደረጉ ውይይቶች ግብረ መልስ በማሰባሰብ ለቀጣይ የማስተካከያ እርምጃና በዕቅድ ዝግጅት ወቅት በግብዓትነት በመጠቀም ይሆናል:: የሚሰጡት ግብረ መልሶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ማስተካከያ የማይወሰድባቸው ከሆነ ይህንኑ ያልፈጸመው አካል ተጠያቂ ይሆናል::

በዚህም መሠረት ከሚመለከታቸው አካላት የሚሠጡ ግብረ መልሶችን መሠረት በማድረግ የተደራጀ የዕርምጃ አወሳሰድ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ዕርምጃዎችን በመውሰድ የአፈጻጸም ሪፖርት ይቀርባል:: በዋና መስሪያ ቤት ደረጃ በዋና ዋና ስራዎች በደረጃ የተነጻጸረ፣ በዋና ዋና ስራዎች ተመክሮ በማቀያየር እና በቀጣይ መከናወን ባለባቸው ተግባሮችና የአፈጻጸም አቅጣጫዎች ዙሪያ ክቡር ሚኒስትሩ በየሶስት ወሩ፣ ሚኒስትር ዴኤታዎች በየወሩ የተደራጀ የጽሁፍ ግብረ መልስ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ዳይሬክቶሬቶች ይሰጣሉ::

ዳይሬክቶሬቶችና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችም በተዋረድ በተመሳሳይ መልኩ በየወሩ የሚደረጉ የአፈጻጸም ግምገማዎችን ተከትለው የጽሁፍ ግብረ መልስ በየወሩ፣ የስራ ሂደቶች ለቡድኖች በየአስራ አምስት ቀኑ ግብረ መልስ መስጠትና መረጃውንም መያዝ ይኖርባቸዋል:: በመጨረሻም የቡድን አስተባባሪዎች በየሳምንቱ የስራ ግምገማ ሲያደርጉ ለፈጻሚዎቻቸው ተከታታይነት ያለው የሳምንታዊ ተግባር አፈጻጸም አጫጭር ግብረ መልሶች መስጠትና መረጃውንም ለውጤት ተኮር የምዘና ስራዓት መያዝ ይኖርባቸዋል::